# ማ ው ጫ

I. መግቢያ ... 2
ክፍል አንድ ... 4
1. የልማት ዕቅዱ መነሻዎች፣መሠረታዊ አቅጣጫዎችና ዓላማዎች ... 4
1.1 የልማት ዕቅዱ መነሻዎች ... 4
1.2. የዕቅዱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች ... 5
1.3. የልማት ዕቅዱ ዓላማዎች ... 7
ክፍል ሁለት ... 8
2. የልማት ዕቅዱ የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ... 8
ክፍል ሶስት ... 9
3. የልማት ዕቅዱ የፋይናንስ ፍላጎትና የወጪ ግምት ... 9
ክፍል አራት ... 20
4. የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት ዕቅድ ... 20
4.1. ግብርና ልማት ... 20
4.2. የአካባቢ ጥበቃና መሬት አስተዳደርና መሬት አጠቃቀም ... 36
4.3. ኢንድስትሪ ልማት ... 39
4.4. ማዕድን ... 46
4.5. የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት ... 48
4.5.1. መንገድ ... 48
4.5.2. ኢነርጂ ... 49
4.5.3. ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ... 51
4.5.4. የመጠጥ ውሃና መስኖ ልማት ... 52
4.5.5. የትራንስፖርት አገልግሎት ... 54
4.5.6. ሥራና ከተማ ልማት ... 57
4.5.7. ባህልና ቱሪዝም ... 62
ክፍል አምስት ... 66
5. የማህበራዊ ዘርፍ ... 66
5.1. ትምህርት ... 66
5.2. ጤና ጥበቃ ... 72
5.3. ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ... 75
ክፍል ስድስት ... 78
6. አቅም ግንባታና መልካም አስተዳደር ... 78
6.1. አቅም ግንባታ ... 78
6.2. የፍትህ ዘርፍ ... 81
6.3. ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ... 85
6.4. ብዙሀን መገናኛ ... 88
6.5. ኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ... 89
ክፍል ሰባት ... 90
7. የባለብዙ ዘርፎች ዕቅድ ... 90
7.1. ሥርአተ ጾታና የህፃናት ጉዳይ ... 90
7.2. ሥነህዝብና ልማት ... 92
7.3. ወጣቶችና ስፖርት ... 93
ክፍል ስምንት ... 97
8. የክትትልና ግምገማ ስርዓት ... 97
9. ዕዝል ... 98
9.1. የዋና ዋና ሴክተሮች ዝርዝር ግቦች ... 98

# I. መግቢያ

ባለፉት አምስት ዓመታት አገራችን ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን በማረጋገጥ፤ ማሕበራዊ ልማትን በማፋጠን እና ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግሥትን እውን በማድረግ ረገድ በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ ለውጥና ድል አስመዝግባለች። በአገር ደረጃ ለተመዘገበው አጠቃላይ ፈጣን ልማትና መልካም አስተዳደር ስርዓት ግንባታ ክልላችን የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዳበረከተ መገንዘብ ይቻላል። በተለይም ክልሉ ሰፊ የግብርና ልማት የሚካሄድበት ክልል በመሆኑና ለኢኮኖሚው አጠቃላይ ዕድገት ካለው ከፍተኛ ድርሻ አኳያ ሲታይ የራሱ የሆነ ሚና እንዳለዉ መረዳት ይቻላል።

በተጠናቀቀው ስትራቴጂያዊ የዕቅድ ዘመን በክልሉ በሁሉም ዘርፎች አበረታች የእድገት ምልክቶች ታይተዋል። ከነዚህም ዉስጥ በማስፈጸም አቅም ግንባታ ዙሪያ የልማት ኃይሎች በተቀናጀ መንገድ ለልማትና መልካም አስተዳደር የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እያደገ መምጣቱ፣ በግብርናና ገጠር ልማት በተለይም በሰብል ልማት ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ መቻሉ፣ በከተማ ልማትና በኢንዱስትሪ ዘርፍ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት መስፋፋትና በኢንቨስትመንት ጅምር እንቅስቃሴ መኖሩ፣ ሥራ አጥነትን መቅረፍ የሚያስችሉ ዉጤቶች መታየት መጀመራቸው፣ የትምህርት የጤናና የውሀ የምእተ አመት ግቦችን ለማሳካት የተደረገዉ ጥረት፣ የትምህርት ጥራት ችግርን ለይቶ ለመፍታት የሚደረገው ዕንቅስቃሴ አበረታች መሆኑ፣ በጤናው ዘርፍ የመከላከል ፖሊሲውን በማስረጽና በመተግበር መሻሻል መታየቱ፣ በመልካም አስተዳደርና በዲሞክራሲ ተቋማት የሚታየዉ ጅምር ለዉጥ፣ ገቢ የመሰብሰብ አቅም እየተሻሻለ መምጣቱና ዜጎች በሠላም ወጥተው በሠላም የሚገቡበት የፀጥታ ሁኔታ መፍጠር መቻሉ . . . ወዘተ የመሳሰሉ ስኬቶች በተጠናቀቀው ስትራቴጂ ዕቅድ ዘመን የተመዘገቡ ስኬቶች ናቸው።

ከላይ የተገለጹት ስኬቶች እውን ሊሆኑ የቻሉት በየደረጃው ያለው አመራርና ፈጻሚ በወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ላይ ያላቸው ግንዛቤ በማደጉና የመፈጸም አቅማቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ በመሻሻሉ፣ የአመራሩ መሰረት እየሰፋ በመምጣቱ፣ አመራሩና ፈፃሚው የሚያደርገዉ ጥረት መጠናከርና የህዝቡና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እያደገ በመምጣቱ ነው። ይሁን እንጅ በክልሉ ውስጥ ልማትን ለማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የልማት ሀይሎችን አቅም በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ በመጠቀም፣ ሁሉም ዘርፎች ተናበውና ተመጋግበው በተዋሃደ መንገድ ለክልሉ ዕድገት በመስራትና መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት ረገድ ዕጥረት ይታያል።

የሃገሪቱን ብሎም የክልሉን አጠቃላይ ዕድገት ሊፈታተኑ የሚችሉ እንደ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን፣ የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ ችግር፣ የስራ አጥ ቁጥር መበራከት ወዘተ የመሳሰሉት አዝማሚያዎች ከፍተኛ ርብርብ የሚጠይቁ ናቸዉ። በመሆኑም በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ የአገሪቷን ፈጣን ልማት ለማስቀጠል እንዲቻል በክልላችን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዕድገትን የሚፈታተኑ አዝማሚያዎችን ለማስወገድ በማስፈጸም አቅም፣ በዲሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል።

ስለሆነም የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችና ውጤቶች ላይ በመመስረት የክልሉን ብሎም የአገሪቷን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የልማት ዕድገት ለማረጋገጥ ምላተ ህዝቡን በንቅናቄ ውስጥ በማስገባት ሊተገበር የሚችል አገራዊውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሠረት ያደረገ የቀጣይ 5 ዓመት ክልላዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቷል።

የልማት ዕቅዱ በዋናነት ስምንት ክፍሎችን ይዞ የተደራጀ ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የልማት ዕቅዱን መነሻዎችና መሠረታዊ አቅጣጫዎች የሚያብራራ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል የማክሮ ኢኮኖሚ አመላካቾችን ያሳያል። ሶስተኛው ክፍል የገቢ ፍላጎትንና የልማት ማስፈፀሚያ ወጪ ዕቅድን ይጠቁማል። አራተኛው ክፍል የኢኮኖሚ ዘርፎችን፣አምስተኛ ክፍል የማህበራዊ ዘርፎችን፣ ክፍል ስደስት የመልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ እንዲሁም ክፍል ሰባት የባለብዙ ዘርፎችን ዕቅድ ያካተተ ሲሆን ክፍል ስምንት የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን አካቷል።

# ክፍል አንድ

## 1. የልማት ዕቅዱ መነሻዎች፣መሠረታዊ አቅጣጫዎችና ዓላማዎች

### *1.1 የልማት ዕቅዱ መነሻዎች*

*በአገር ደረጃ ለቀጣይ 5 ዓመታት(2003-2007) የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቷል። የዕቅድ መነሻዎችም የአገሪቱ ራዕይ ፣ ባለፉት ዓመታት ተፈጻሚ በሆኑ ዕቅዶች የተመዘገቡ ውጤቶችና በአፈጻጸም ሂደት የተገኙ ተሞክሮዎች ናቸው። የአገሪቱ ራዕይ በ2012 በህዝብ ተሳትፎና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት፣ ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ነው። ስለሆነም በኢኮኖሚው መስክም በከፍተኛ ቴክኖሎጂና ምርታማነት ደረጃ ላይ የደረሰ ዘመናዊ ግብርና እንዲሁም የመሪነት ሚና መጫወት የሚችልበት ደረጃ ላይ የደረሰ ኢንዱስትሪ ያለው ኢኮኖሚ የገነባች ፣ ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት የተረጋገጠባት እና እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2012 የዜጎች የነፍስ መከፍ አመታዊ ገቢ መካከለኛ ዕድገት ያላቸው አገሮች ደረጃ ላይ የደረሰች አገር እንድትሆን ማስቻል ነው ። ባለፉት ዓመታት ተፈጻሚ የሆኑ ዕቅዶች የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከማሳካት አንጻርም የተቃኙ ስለነበር ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲመዘገብ ከማስቻላቸው በላይ የምዕተ ዓመቱን ግብና አገራዊ ራዕይ ለማሳካት በምንችልባት መንገድ ላይ እንዳለን አመላካች ናቸው ።*

*በክልላችንም ባለፉት የስትራቴጂያዊ የዕቅድ ዓመታት በግብርናና ገጠር ልማት፣ በማስፈፀም አቅም ግንባታ፣ በከተማ ልማት፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ በትምህርት፣ በጤናና እንዲሁም በኢንቨስትመንትና ሥራ አጥነትን በመቅረፍ ረገድ አበረታች ውጤቶች ታይተዋል። ከኢኮኖሚ ዕድገት አኳያም በየዓመቱ 11 በመቶ የሚደርስ ፈጣን ዕድገት እንደተመዘገበና ዕድገቱም አብዛኛውን የክልሉን ህዝብ ተጠቃሚ ያደረገ እንደነበር መረዳት ይቻላል። ከዚህ አንፃር የክልሉ የቀጣይ 5 ዓመታት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻዎች የአገራዊው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አቅጣጫዎች፣ የክልሉ ራዕይ እንዲሁም ባለፉት ዓመታት ዕቅዶች ትግበራ ወቅት በክልሉ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች ናቸው። ስለሆነም በቀጣይ 5 ዓመታት የኢኮኖሚውን ዕድገት ቀጣይነት ማረጋገጥና ድህነትን መቀነስ፣ የምግብ ዋስትና ችግርን ሙሉ በሙሉ መቅረፍ፣ በኢኮኖሚና ማህበራዊ ሴክተሮች የታዩ እንቅስቃዎችን በማጠናከር የምዕተ ዓመቱን ግቦች ማሳካት እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በመሥራት የክልሉን ብሎም የአገር አቀፉን ራዕይ በ2012 ማሳካት ነው።*

## 1.2. የዕቅዱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች

ባለፉት ዓመታት በክልሉ 3 የአምስት ዓመት የልማትና ዴሞክራሲ ግንባታ ዕቅዶች ተዘጋጅተው ተግባር ላይ የዋሉ ሲሆን በዚህም አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል። በተለይም ባለፉት ሰባት ዓመታት በአገሪቱ ለተመዘገበው እድገት የክልሉ ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ ይገመታል። ስለሆነም ከዚህ የተገኘውን የእድገት መነሳሳት በግብዓትነት በመጠቀም በ4ኛው አምስት ዓመት ኢኮኖሚውን ከማሳደግ አንፃር እመርታዊ ለውጥ እንደሚመዘገብ ይጠበቃል። ይህን እውን ከማድረግ አንፃር ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባቸው መሠረታዊ አቅጣጫዎች ፤

- ፈጣን፤ ቀጣይና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ፣
- የግብርናው ሴክተር ዋና የእድገት ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ፣
- የኢንዱስትሪው ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ማስቻል፣
- መሠረተ ልማትን ማስፋፋትና ጥራቱን ማረጋገጥ፣
- የማህበራዊ ልማትን ማፋጠንና ጥራትን ማረጋገጥ፣
- መልካም አስተዳደርን ማስፈንና አቅም ግንባታን ማሣደግ፣
- የሴቶችንና የወጣቶችን ብቃትና ተጠቃሚነት ማሣደግ፤ የሚሉት ሲሆኑ

እነዚህ መሠረታዊ አቅጣጫዎች በዋናነት በአገራዊው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የተወሰዱ ሲሆን የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት በማድረግ በአጭሩ እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

### 1. ፈጣን፤ ቀጣይና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ፤

እስካሁን በነበሩት ተከታታይ ዓመታት የተመዘገበውን እድገት በቀጣይ የዕቅዱ ዓመታት ለማስቀጠልና ህዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ለማድረግ ብሎም ሥር የሰደደ ድህነትን ለማስወገድና የምግብ ዋስትናን በአካባቢና በቤተሰብ ደረጃ ሙሉ በሙሉ ከማረጋገጥ አንፃር ሠፊና የተቀናጀ ሥራ በተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መስኮች ይከናወናል። በተለይም በክልሉ በግብርናው ዘርፍ ያለውን እምቅ ሀብት በላቀ ደረጃ ውጤት በማምጣት አጠቃላይ ኢኮኖሚው እንዲያድግ የማድረግ ሥራዎች ይከናወናሉ።

### 2. የግብርናው ዘርፍ ዋና የእድገት ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ

እስካሁን በአገር ደረጃ ከሚመረተው የሰብል ምርት ውስጥ ክልሉ ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሚሆነው እንዲሁም ከእንስሳት ምርት አኳያ ሠፊ አቅም ያለው እንደሆነ ያሳያል። ይህም ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ከማሣደግ ረገድ የተመዘገበው ለውጥ በቀጣይ ዓመታትም የበለጠ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል የሚያረጋግጥ ነው። በመሆኑም ያለፉ ተሞክሮዎችን በመውሰድና በጥቂት አርሶአደሮች የተጀመረውን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ወደ ሁሉም አርሶአደሮች ለማስፋት፤ የዝናብ ውሃን በአግባቡ ከመጠቀም ባሻገር ባህላዊና ዘመናዊ መስኖን በማስፋፋት፤ የተፈጥሮ ሀብትን በመንከባከብና የመሬት ለምነትን በማሻሻልና እያንዳንዱን የግብርና አካባቢ በላቀ ደረጃ በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ለማሣደግ ጥረት ይደረጋል። በተጨማሪ የግብይት

ሥርዓቱን ቀልጣፋና ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አሠራሮች ይዘረጋሉ። በዚህም ከፍጆታ አልፎ ለአለም ገበያ የሚቀርብና ለኢንዱስትሪው ጥሬ እቃ የሚሆን በቂ ምርት ማምረትና በአጠቃላይም የግብርናው ሴክተር ለሌሎች ዘርፎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል ሀብት ሊያመነጭ በሚያስችል ቁመና ላይ እንዲደርስ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል። በዋናነት አርሶ አደሩን በመደገፍና ዘመናዊ አሠራርን በሠፊው እንዲጠቀም በማድረግ እንዲሁም ኢንቨስተሩም በዘርፉ እንዲሠማራ በማድረግ እንደ ሆርቲካልቸርና የመሳሰሉትን ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውንና የኤክስፖርት ሰብሎች እንዲያመርት የማድረግ ሥራን በማከናወን የግብርናውን ምርት በእጥፍ ለማሣደግ የሚያስችሉ አሠራሮችን ለመተግበር ጥረት ይደረጋል።

### 3. የኢንዱስትሪው ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲጫዋት ማስቻል ፣

በኢኮኖሚ ፖሊሲው መሠረት የግል ባለሀብቱ የኢኮኖሚው ዋነኛ አንቀሳቃሽ ሞተር ነው። ከዚህ አንፃር ባለሀብቱ ኢንዱስትሪውን በማስፋፋት ረገድ ሚናውን እንዲጫወት የተለያዩ ድጋፎችና ማበረታቻዎች ይደረጋሉ። በዚህም የተለያዩ አግሮኢንዱስትሪዎችን እና የጥቃቅንና አነስተኛ እንዱስትሪዎችን የማቋቋምና የማጠናከር ስራ ትኩረት ይሰጠዋል። ከዚህ አንፃር ኢንዱስትሪው የሥራ እድል በመፍጠር፤ በቴክኖሎጂ ሽግግር፤ የግብርናውን ሴክተር በመደገፍ፤ የውጭ ምንዛሬ በማፍራት እንዲሁም ለከተሞች እድገት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ሚናውን እንዲወጣ ማድረግ በሚያስችል መልኩ ጥረቶች ይደረጋሉ።

### 4. መሠረተ ልማትን ማስፋፋትና ጥራቱን ማረጋገጥ፤

ክፍለ ኢኮኖሚዎችን ለመደገፍ እዲሁም በክፍለ ኢኮኖሚዎች መካከል እና በከተማና በገጠር ያለውን ትስስር ለማጠናከር በአጠቃላይም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገትን ከማሳለጥ አንፃር የመሠረተ ልማት አውታር ማስፋፋት ሚናው የጎላ ነው። ከዚህ አኳያ የገጠር መንገድና ሌሎች መሠረተ ልማቶች የማስፋፋት ሥራ በቀጣይ የእቅድ ዓመታት ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። በተለይም ቀበሌን ከቀበሌ፤ ወረዳን ከወረዳ በመንገድ የማገናኘት ሥራዎች ትኩረት ይሰጣቸዋል።

### 5. የማህበራዊ ልማትን ማፋጠንና ጥራቱን ማረጋገጥ

ኢኮኖሚው በሚፈለገው ደረጃ ብቁ፤ ተወዳዳሪ እና አምራች ዜጋ ከማፍራት አንፃር በሰው ሀይል ልማት ረገድ እየተደረገ ያለው ርብርብ በቀጣይም ተጠናክሮ ይከናወናል። በአሁኑ ወቅት የክልሉ የትምህርት ሽፋን እያደገ ያለ ቢሆንም አሁንም በርካታ በትምህርት እድሜ ክልል ያሉ ህፃናት በትምህርት ገበታ ላይ አይደሉም። በዚህ መሠረት ሁሉም በ1ኛ ደረጃ ትምህርት የእድሜ ክልል የሚገኙ ህፃናት በሙሉ ትምህርት ቤት እንዲገቡ በማድረግ የትምህርት ሽፋንን የማሣደግ እንዲሁም ተገቢነትንና ፍትሀዊነትን የማስጠበቅ ሥራ በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል። በእቅድ ዘመኑ ለትምህርት ጥራት ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል። በመሆኑም የትምህርት ተቋማትን ለማስፋፋት ፤ ለደረጃው የሚመጥኑ በቂ መምህራንን የማሟላት፤ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ የሚቀንሱ ችግሮችን የማቃለል ተግባራት ይከናወናሉ። በቴክኒክና ሙያ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ለማስፋፋትና ለማጠናከር በሚያስችላቸው አግባብ እንዲሰለጥኑ ይደረጋል። በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት በገጠር በምርት ተግባር ከተሰማራው ሀይል አመዛኙ ማንበብና መፃፍ የማይችል እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ስለሆነም ይህ

ሀይል ቴክኖሎጂ በቀላሉ በመቀበል ምርታማነትን እንዲያሳድግ ከማድረግ አንፃር ሚናውን እንዲወጣ እንዲሁም በማህበራዊና ሌሎች መስኮች ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችል ለተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ትኩረት ይሰጠዋል። ከዚህ በተጨማሪ የመሠረታዊ ጤና አገልግሎትን በማስፋፋትና የአገልግሎት ጥራትን የማስጠበቅ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ። ከዚህ በተጨማሪ የንፁህ መጠጥ ወሃና ሳኒቴሽን እንዲሁም ስርዓት ምግብ የቀጣይ ዓመታትም የትኩረት መስኮች ናቸው። ማህበራዊ ተቋማትን ከማስፋፋት አንፃር ሁሉም የልማት ሀይሎች ከመንግስት ጋር በተቀናጀ አግባብ ርብርብ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል።

### 6. መልካም አስተዳደርንና አቅም ግንባታን ማሣደግ

ልማትን ዕውን ከማድረግ አንፃር ቁልፍ የሚሆነው የሰው ሀይል ነው። ከዚህ አኳያ ይህን ብቁና ውጤታማ ለማድረግ በመንግስትና በግል ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ግልጽነትና ተጠያቂነት ከማስፈን አንፃር የማስፈፀም አቅም ግንባታን ማጠናከር ወሳኝ ነው። ስለሆነም ቀደም ሲል የተጀመረው የሲቪል ሰርቪስ ፕሮግራም ተጠናክሮ ይቀጥላል። በተጨማሪም የፍትህ ስርዓቱን ለማሻሻል እንዲሁም የዴሞክራሲያዊ ተቋማትን የማጠናከር ሥራ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። በተለይ በክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ በገጠርም ይሁን በከተማ ከመሬት ጋር ተያይዞ እየተነሳ ያለው ጉዳይ ትልቅ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ስለሆነ በዚህ ረገድ ያሉ ችግሮችን በመሠረታዊነት ለመፍታት ጥረቶች ይደረጋሉ።

### 7. የሴቶችንና የወጣቶችን ብቃትና ተጠቃሚነት ማሣደግ

የቀጣይ ዓመታት እቅድ ሊሳካ የሚችለው ያለንን የሰው ሀይል ወደ ልማት ማስገባት ሲቻል ነው። ከዚህ አኳያ ወጣቶችና ሴቶች በልማቱ ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ የማይታለፍ ጉዳይ ነው። ስለሆነም የወጣቶችና ሴቶችን አቅም የመገንባት፣ አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ማመቻቸት፤ የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን የማስፋፋት እንዲሁም የሥራ እድሎችን መፍጠር የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ፡

## 1.3. የልማት ዕቅዱ ዓላማዎች

የቀጣይ 5 ዓመት (2003-2007) ክልላዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. በየዓመቱ ቢያንስ የ 11 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ መታየት የጀመረውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በማስቀጠል የምግብ ዋስትና ችግርን ሙሉ በሙሉ መቅረፍ፣ ድህነትን መቀነስ እንዲሁም የምዕተ ዓመቱን ግቦች ማሳካት፣
2. በትምህርትና በጤና ሴክተሮች የአገልግሎት ሽፋንን ከማሳደግ በተጨማሪ ጥራቱን ማረጋገጥ፣
3. የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ማስፈንና ለአንድ አገራዊ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ምቹ መደላድል መፍጠር፣
4. በአገር ደረጃ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ለመፍጠርና የልማቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ክልላዊ ድርሻን መወጣት የሚሉት ዋናዋናዎቹ ናቸው።

# ክፍል ሁለት

## 2. የልማት ዕቅዱ የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ

በአገር ደረጃ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የማክሮ ኢኮኖሚ ዋነኛ ዓላማ የተመቻቸ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ በመፍጠር ፈጣን፣ ዘላቂ እና ፍትሃዊ ዕድገት ማስመዝገብ ነው። ከዚህ አንፃር የተረጋጋ የዋጋ እና የውጭ ምንዛሬ እንዲኖር በማድረግ ፣ የሀገር ውስጥ ቁጠባንና ኢንቨስትመንትን በማበረታታት እንዲሁም የውጭ ክፍያ ሚዛንን በማጥበብ ለኢኮኖሚው ዕድገት የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ይደረጋል። ይህን አገራዊ ዓላማ ከማሳካት አንፃር በክልል ደረጃ ሠፊ እንቅስቃሴ ማድረግን ይጠይቃል። ከዚህ አንፃር የአገር ውስጥ ቁጠባን በማዳበር በኢንቨስትመንትና በቁጠባ ያለውን ክፍተኛ ክፍተት ማጥበብ፣ የሚመረት ምርትን በከፍተኛ ደረጃ በመጨመርና የወጪ ንግድ እንዲያድግ ጥረት በማድረግ የዋጋ ግሽበትን መቀነስና የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ከፍ የማድረግ እንዲሁም የውጭ ክፍያ ሚዛን እንዲጠብ ከማድረግ አንፃር የተጠናከረ እንቅስቃሴ ይደረጋል።

ስለሆነም በቀጣይ 5 ዓመታት የክልሉ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ በአማካይ በ11 በመቶ እንደሚያድግ ይጠበቃል። በክፍለ ኢኮኖሚ ደረጃ ሲታይ ግብርናው በ8 በመቶ፣ ኢንዱስትሪው በ20.1 በመቶ እና የአገልግሎት ዘርፉ በ10.5 በመቶ እንደሚያድጉ ይጠበቃል። በዚህ የእድገት አማራጭ የግብርናው ዘርፍ ድርሻ እየቀነሰ ይሄዳል። ከሚጠበቀው መዋቅራዊ ለውጥ(Transformation) አኳያ የዕድገት ምንጩ ወደ ኢንዱስትሪው እያዘነበለ እንደሚሄድ ይጠበቃል። የአገልግሎት ዘርፉ ድርሻ ግን ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ሆኖ እንደሚቀጥል ይጠበቃል።

በከፍተኛው የዕድገት አማራጭ በቀጣይ 5 ዓመታት ክልላዊ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በየዓመቱ በአማካይ በ14.9 በመቶ እንደሚያድግ የሚጠበቅ ሲሆን የግብርናው ሴክተርም መሪነቱን እንደያዘ ሆኖ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በእጥፍ የሚያድግ ይሆናል ።

**ክልላዊ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት አማካይ ዕድገት በመነጨበት ክፍለ ኢኮኖሚ በመቶኛ /በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ/**

| ዘርፍ | አማካይ(2003-2007) |
|---|---|
| ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች | 8.0 |
| ኢንዱስትሪ | 20.1 |
| አገልግሎት | 10.5 |
| ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት | 11.0 |

**ክልላዊ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት አማካይ ዕድገት በመቶኛ/በከፍተኛው የዕድገት አማራጭ/**

| ዘርፍ | አማካይ(2003-2007) |
|---|---|
| ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች | 14.9 |
| ኢንዱስትሪ | 21.4 |
| አገልግሎት | 12.8 |
| ጠቅላላ ክልላዊ የአገር ውስጥ ምርት | 14.9 |

# ክፍል ሶስት

## 3. የልማት ዕቅዱ የፋይናንስ ፍላጎትና የወጪ ግምት

በመሠረታዊው የዕድገት አማራጭ/Base case scenario/ ጠቅላላ ገቢ ከመንግስት ግ/ቤትና ከውጭ ዕርዳታና ብድር እንደሚገኝ ታሳቢ የተደረገ ነው። ከመንግስት ግ/ቤት የሚገኝ ገቢም በክልሉ አቅም የሚሰበሰብ ገቢና ከፌደራል የሚገኝ ድጎማን ያካትታል። በክልሉ አቅም የሚሰበሰብ ገቢ በአመዛኙ የሚሸፈነው ከኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ከሚሰበሰብ የታክስ ገቢ ሲሆን በተወሰነ መልኩም ከልማት ድርጅቶችና የፋይናንስ ተቋማት ደቪደንድ እና ከመሳሰሉት የሚሰበሰብ ታክስ ያልሆነ ገቢንም ይጨምራል።

በአጠቃላይ እስካሁን ካለው አዝማሚያና ልማቱ ከሚጠይቀው አንፃር የክልሉ ገቢ በ2002 ከነበረበት 5.773 ቢሊዮን ብር በየዓመቱ በአማካይ በ21 በመቶ ዕድገት በማሳየት በ5 ዓመቱ መጨረሻ ብር 15.014 ቢሊዮን እንደሚደርስ ተገምቷል። ስለሆነም በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ኢኮኖሚው ሊያመነጭ ከሚችለው መጠንና ሊኖር ከሚችል እየዳበረ በሚሄድ ገቢ የመሰብሰብ አቅም አንፃር ሊገኝ የሚችል ገቢ ታሳቢ ተደርጓል። የውጭ ዕርዳታና ብድርም በአገር ደረጃ ሊገኝ ከሚችለው መጠንና ከአሁን በፊት ክልሉ የሚያገኘውን ድርሻ መነሻ በማድረግ ለመገመት ተሞክሯል። ቀሪውም ከፌደራል መንግስት ድጎማ እንደሚገኝ ታሳቢ ተደርጓል። ስለሆነም የልማት ዕቅዱን ዕውን ከማድረግ አንፃር በየዓመቱ እያደገ የሚሄድ የማስፈፀሚያ ሀብት የሚያስፈልግ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተጀመረውን የታክስ ሪፎርም በማጠናከር በክልሉ አቅም ሊሰበሰብ የሚገባውን ገቢ ለመሰብሰብ የሚደረግ ጥረትን አጠናክሮ መቀጠልን ይጠይቃል።

ወጪን በተመለከተም ከገቢው ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ በየዓመቱ እያደገ እንደሚሄድ ታሳቢ ተደርጓል። በዚህ መሠረት የካፒታል ወጪው በ2002 ከነበረበት 27 በመቶ ድርሻ በ5 ዓመቱ መጨረሻ ወደ 40 በመቶ እንደሚደርስ ይጠበቃል። ይህ በፌደራል ደረጃ የሚካሄዱ ትልልቅ ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን እንዲሁም የግል ኢንቨስትመንትን የሚያካትት ስላልሆነ በአጠቃላይ ለልማት (ለካፒታል ሥራዎች) የሚደረግ ወጪ ሠፊ እንደሆነ መገመት ይቻላል። በሌላ በኩል እንደ ግብርናና ምግብ ዋስትና፣ ትምህርት፣ ጤና፣ መንገድ እና ውሀ ያሉት ድህነት ተኮር ሴክተሮች(Pro-poor sectors) ልማትን ከማፋጠንና ድህነትን ከመቀነስ አንፃር ከፍተኛ ሚና ያላቸው ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ለእነዚህ ሴክተሮች የሚውለው ወጪ በ2002 ከነበረበት 60 በመቶ በ5 ዓመቱ መጨረሻ ወደ 70 በመቶ ከፍ እንደሚል ተገምቷል።

**በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ/Base case/ የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና የፊስካል ማዕቀፍ የክልሉ ገቢ ግምት /በቢሊዮን ብር/**

| ዝርዝር | የ2002 መነሻ | የቀጣይ 5 ዓመታት ግቦች | | | | | የ5 ዓመቱ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 | |
| ጠቅላላ ገቢ | 5.773 | 7.004 | 8.475 | 10.255 | 12.408 | 15.014 | 53.155 |
| ከመንግስት ግ/ቤት | 5.533 | 6.708 | 8.203 | 9.951 | 12.088 | 14.662 | 51.611 |
| በክልሉ ከሚሰበሰብ ገቢ | 0.905 | 1.208 | 2.200 | 3.100 | 3.900 | 5.000 | 15.408 |
| ታክስ ገቢ | 0.724 | 0.966 | 1.760 | 2.480 | 3.120 | 4.000 | 12.326 |
| ታክስ ያልሆነ ገቢ | 0.181 | 0.241 | 0.440 | 0.620 | 0.780 | 1.000 | 3.082 |
| የፌደራል ድጎማ | 4.628 | 5.500 | 6.003 | 6.851 | 8.188 | 9.662 | 36.203 |
| ከውጭ ዕርዳታና ብድር | 0.240 | 0.120 | 0.272 | 0.304 | 0.320 | 0.352 | 1.368 |

**በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ/Base case/ የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና የፊስካል ማዕቀፍ የክልሉ የወጪ ግምት/በቢሊዮን ብር/**

| ዝርዝር | የ2002 መነሻ | የቀጣይ 5 ዓመታት ግቦች | | | | | የ5 ዓመቱ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 | |
| ጠቅላላ ወጪ | 5.773 | 7.004 | 8.475 | 10.255 | 12.408 | 15.014 | 53.155 |
| መደበኛ ወጪ | 4.183 | 4.903 | 5.763 | 6.768 | 7.941 | 9.008 | 34.384 |
| ካፒታል ወጪ | 1.590 | 2.101 | 2.712 | 3.487 | 4.467 | 6.006 | 18.772 |
| ከጠቅላላ ወጪ ውስጥ የድህነት ተኮር ዘርፎች ወጪ | 3.464 | 4.342 | 5.424 | 6.768 | 8.437 | 10.510 | 35.482 |
| • ግብርናና ምግብ ዋስትና | 0.739 | 0.927 | 1.157 | 1.444 | 1.801 | 2.243 | 7.572 |
| • ትምህርት | 1.836 | 2.302 | 2.875 | 3.587 | 4.472 | 5.570 | 18.805 |
| • ጤና | 0.520 | 0.651 | 0.814 | 1.015 | 1.266 | 1.576 | 5.322 |
| • መንገድ | 0.213 | 0.267 | 0.334 | 0.417 | 0.520 | 0.647 | 2.186 |
| • ውሀ | 0.156 | 0.195 | 0.244 | 0.305 | 0.380 | 0.473 | 1.597 |

## የዋና ዋና ዘርፎች አመልካች

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ 2002 | መድረሻ 2007 |
|---|---|---|
| **1. የግብርና ዘርፍ ልማት ግቦች** | | |
| ዋና ዋና የሰብል ምርት(በሚሊዮን ኩንታል) | 61.91 | 152.42 |
| -ምርታማነት ኩንታል በሄክታር | 15.1 | 37.2 |
| የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብዛት (ሚሊዮን ቁጥር) | 3.2 | 3.6 |
| በልማታዊ ሴፍቲኔት የሚሳተፉ ቤቴሰቦች ብዛት (በሺህ ቁጥር) | 2,294.15 | 255.7 |
| የአፈርና ውኃ ጥበቃ ስራን በተዳፋት መሬት (ሺህ ሄክታር) | 538.8 | 2894.1 |
| የማሳ ላይ እርጥበትና አፈር ዕቀባ ስራ (ሚሊ. ሄክታር) | 2.1 | 4.1 |
| የደን ሽፋን (በ%) | 7.8 | 13.85 |
| የቦረቦር መሬት ማዳን (ሄክታር) | 25,940 | 182,080 |
| የኬሚካል ማዳበሪያ አቅርቦት (ሚሊዮን ኩንታል) | 2.2 | 5.3 |
| የምርጥ ዘር አቅርቦት (ሚለዮን ኩንታል) | 0.129 | 1.816 |
| የደጋና ቆላ ፍራፍሬ ችግኝ (ሚሊዮን) | 2.18 | 12.3 |
| በመስኖ የሚለማ መሬት (ሄክታር) | 444,620 | 950,000 |
| ከመስኖ የሚገኝ ምርት (በሚሊዮን ኩንታል) | 51.38 | 100 |
| የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋን (በ%) | 80 | 100 |
| ለገበያ የሚቀርብ ምርት በሚሊዮን ኩንታል | 39.7 | 63.1 |
| የህብረት ስራ ማህበራት አባልነት ሽፋን (%) | 72.8 | 100 |

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ 2002 | መድረሻ 2007 |
|---|---|---|
| **2. ኢንዱስትሪና የግል ኢንቨስትመንት ማስፋፋት** | | |
| ፍቃድ የተሰጣቸው ፕሮጀክቶች እስከ 2002 (በቁጥር) | 5,402 | 12,902 |
| የተመዘገበ ኢንቨስትመንት ካፒታል መጠን በቢሊዮን (ብር) | 72.9 | 189.2 |
| በተጨባጭ ወደ ኢኮኖሚው የገባ ኢንቨስትመንት ሀብት መጠን በቢሊዮን (ብር) | 5.9 | 26.02 |
| ወደ ተግባር የገባ የውጭ ባለሃብት (ጆይንት ቬንቸርን ጨምሮ )ፕሮጀክት (በቁጥር) | 78 | 258 |
| ወደ ተግባር የገባ የአገር ውስጥ ፕሮጀክት (በቁጥር) | 1,017 | 4,646 |
| የተቋቋመ መካከለኛ የኢንዱስትሪ ዞን ብዛት (በቁጥር) | 7 | 41 |
| የተቋቋመ ከፍተኛ የኢንዱስትሪ ዞን ብዛት (በቁጥር) | 0 | 6 |
| ተቋቋሙ ኢንዱስትሪዎች ብዛት (መካከለኛና ከፍተኛ) (በቁጥር) | 43 | 200 |
| በኢንዱስትሪው የተፈጠረ የሥራ ዕድል (በቁጥር) | 5,332 | 15,635 |
| ከኢንዱስትሪው የተገኘ የውጭ ምንዛሪ በሚሊዮን ( በብር ) | 160 | 1000 |
| ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ የተሸጋገሩ ( በቁጥር) | 36 | 1200 |
| የኢንዱስትሪዎች አማካይ የማምረት አቅም (%) | 46 | 75 |
| ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች በቁጥር | 54 | 300 |
| ከጥቃቅን ወደ አንስተኛ የተሸጋጋሩ ኢንተርፕራይዞች (በቁጥር) | 1,456 | 5,711 |
| የተቋቋመ የአግሮ ኢንዱስትሪዎች ብዛት (በቁጥር) | 19 | 359 |
| የተቋቋመ የአንዱስትሪ ድጋፍ ማዕከላት ብዛት (በቁጥር) | 4 | 5 |
| የተቋቋመ የአንዱስትሪ ክላስተር ብዛት (በቁጥር) | 0 | 268 |

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ 2002 | መድረሻ 2007 |
|---|---|---|
| የተቋቋመ የአክሲዮን ኩንባንያዎች ብዛት (በቁጥር) | 152 | 4,310 |
| **3. ጥቃቅንና አንስተኛ ኢንተርፕራይዝ** | | |
| ለአዲስና ነባር ተጠቃሚዎች የፋይናንስ እጥረትን ለመቅረፍ የሚሰጥ ብድር አገልግሎት በሚሊዮን (ብር) | 571 | 3,700 |
| ለአዲስና ነባር ተጠቃሚዎች የሚሰጥ የመስሪያና የመሸጫ ቦታ (ሄ/ር) | 1,598 | 3,233.5 |
| ለአዲስና ነባር ተጠቃሚዎች የሚሰጥ ስልጠናና የምክር አገልግሎት ( በቁጥር) | 360,984 | 1,25,0000 |
| ለአዲስና ነባር ተጠቃሚዎች የሚሰጥ የንግድ ልማት አገልግሎት (በቁጥር) | 125,374 | 150,000 |
| አዲስና ነባር ተጠቃሚዎች የገቢያ ችግሮችን ለመፍታት የሚደረግ  ጥረት (በቁጥር) | 109,582 | 250,000 |
| ለአዲስና ነባር ተጠቃሚዎች የሚደረግ የቴክኖሎጅ አቅርቦት (በቁጥር) | 73,298 | 482,788 |
| በሚፈጠሩ አዲስና ነባር ኢንተርፕራይዞች የሚፈጠር አዲስ የስራ እድል (በቁጥር) | 511,311 | 1,000,000 |
| የሚቋቋም ኢንተርፕራይዞች ብዛት (በቁጥር) | 200,789 | 208,685 |
| **4. የንግድ ዘርፍ ልማት** | | |
| የነጋዴ ብዛት በሺህ (በቁጥር) | 117.6 | 353.93 |
| የህገወጥ ነጋዴ ብዛት (%) | 13 | 5 |
| የህጋዊ ነጋዴ ብዛት በመቶኛ (%) | 87 | 95 |
| የተቋቋሙ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ብዛት ( በቁጥር) | 66 | 170 |
| በንግድና ዘርፍ ማህበራት የተደራጁ አባላት ብዛት (በቁጥር) | 4,745 | 151,632 |
| የተቋቋመ  የዘርፍ ማህበራት ብዛት (በቁጥር) | 683 | 933 |

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ 2002 | መድረሻ 2007 |
| --- | --- | --- |
| የተቋቋመ የዘ/ማህበራት ም/ቤቶች ብዛት (በቁጥር) | 99 | 200 |
| የተቋቋመ የአክሲዮን ኩንባንያዎች ብዛት (በቁጥር) | 152 | 4,310 |
| የኃ/የተ/የግል ማህበር ( በቁጥር) | 187 | 3,648 |
| ህብረት ሽርክና ማህበር (በቁጥር) | 228 | 4,452 |
| **5. ባህልና ቱሪዝም ልማት** | | |
| ደረጃቸው የተሻሻለ ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች ብዛት ( በቁጥር) | 8 | 8 |
| በአዲስ የተለዩና የለሙ መዳረሻዎች ( በቁጥር) | 0 | 11 |
| የተቋቋሙ የጥብቅ ሥፍራዎች ብዛት ( በቁጥር) | 4 | 11 |
| የውጭ አገር ቱሪስቶች ብዛት በሺ ( በቁጥር) | 86 | 167 |
| የአገር ውስጥ ቱሪስቶች ብዛት በሺህ ( በቁጥር) | 700 | 1,916 |
| የቱሪስት የቆይታ ጊዜ በቀን | 10 | 15 |
| ከቱሪዝም የተገኘ ገቢ በሚሊዮን (ብር) | 200 | 800 |
| በክልሉ ከተፈጠረው የሥራ ዕድል የቱሪዝም ድርሻ በመቶኛ | - | 10 |
| ደረጃ የተሰጣቸው የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ብዛት በመቶኛ | 10 | 1390 |
| የባህል ሙዚየም ብዛት ( በቁጥር) | 2 | 12 |
| የተፈጠሩ/የተገነቡ የኪነጥበብ ማዕከላት ( በቁጥር) | 11 | 100 |
| በቱሪዝም ልማት የሴቶች ተሳትፎ ( በቁጥር) | 5,000 | 9,103 |
| ደረጃ የወጣላቸው የኮንፈረንስ ቱሪዝም ከተሞች ( በቁጥር) | | |
| **6. መንገድ** | | |

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ 2002 | መድረሻ 2007 |
|---|---|---|
| 4000 ኪሎ ሜትር አዲስ መንገድ በመገንባት የመንገድ ኔትወርክ | 7617 | 11617 |
| የበጋ-ክረምት የተገናኙ ቀበሌዎች ብዛት | 725 | 21 ሺህ ኪሎ ሜትር/3429 ቀበሌዎች |
| የመንገድ ጥግግት ኪ.ሜ/1000 ካ.ኪ.ሜ | 48 | 74 |
| በጥሩ ሁኔታ የሚገኝ መንገድ መረብ በ% | 65 | 75 |
| የመንገድ ጥገና ሽፋን በ% | 90 | 95 |
| **7. ኢነርጂ** | | |
| በክልሉ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ሽፋን በ% | 22 | 75 |
| በክልሉ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ የሆኑ የገጠር ከተሞችንና መንደሮች ብዛት | 679 | 2,572 |
| የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ተጠቃሚ ሽፋንን በ% | 71 | 95 |
| የተለያዩ የኢነርጂ ምንጮች የሚጠቀሙ ተቋማት ብዛት | 122 | 342 |
| የባዮጋዝ ቴክኖሎጂን በማስፋፋት በቤተሰብ ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ | 100 | 3,600 |
| የባዮጋዝ ቴክኖሎጂን በማስፋፋት ተቋማትና የንግድ ድርጅቶችን ተጠቃሚ ማድረግ | 11 | 41 |
| **8.ቴሌኮሙኒኬሽን** | | |
| የክልሉ የመደበኛ ስልክ የአገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኞች ሽፋኑን ማሳደግ | 19 | 40 |
| በ5 ኪ/ሜትር ርቀት መሠረታዊ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሽፋን ማሳደግ በ% | 80 | 100 |
| የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ቀበሌዎችን ቁጥር ማሳደግ፣ | 2,743 | 3,429 |
| **9. ውሀ** | | |
| የገጠር መጠጥ ውሃ ሽፋን በ% | 60 | 100 |

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ<br>2002 | መድረሻ<br>2007 |
|---|---|---|
| የከተማ መጠጥ ውሃ ሽፋን በ% | 90 | 100 |
| አጠቃላይ የክልሉ መጠጥ ውሃ ሽፋን በ% | 64 | 100 |
| **10. መስኖና ድሬኔጅ** | | |
| የመስኖ ፕሮጀክት ጥናትና ዲዛይን በሄ/ር | 12,393 | 57,131 |
| የመስኖ ፕሮጀክት ግንባታ በሄ/ር | 32,726 | 245,641 |
| **11. ሥራና ከተማ ልማት** | | |
| በፕላን የሚመሩ ከተሞች ብዛት (በቁጥር) | 197 | 513 |
| የአካባቢ ልማት ፕላን ዝግጅት (በአካባቢ ቁጥር) | 20 | 92 |
| ቤቶች መገንባት በቁጥር | 20,050 | 50,050 |
| የስራ እድል መፍጠር (በሰው ቁጥር) | - | 25,000 |
| ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የመሸጫና የማምረቻ ቦታዎች ዝግጅት | - | 38 |
| የለማ ገበያ ማዕከል (Shade)(በቁጥር) | 11 | 38 |
| በከተማ በሚሰሩ የመኖሪያ ቤቶች የሴቶች ተጠቃሚነት (በመቶኛ) | 21.6 | 60 |
| የአካባቢ የግንባታ እቃዎች ምርምር ማዕከል ማቋቋም (በቁጥር) | 0 | 1 |
| የድንጋይ ንጣፍ መንገድ ግንባታ (በኪ.ሜ) | 38 | 343 |
| **12. ትምህርት** | | |
| **የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም** | | |
| ጥቅል ተሳትፎ ምጣኔ (በመቶኛ) | 98.4 | 110 |
| ንጥር ተሳትፎ ምጣኔ( በመቶኛ) | 89.4 | 99 |
| ንጥር ቅበላ ምጣኔ (በመቶኛ) | 100 | 100 |
| የ1ኛ ክፍል ማቋረጥ ምጣኔ( በመቶኛ) | 21.1 | 5 |
| የተማሪ ማቋረጥ ምጣኔ (1-8) (በመቶኛ) | 13.8 | 3 |

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ 2002 | መድረሻ 2007 |
|---|---|---|
| **የተማሪ መድገም ምጣኔ**(4-8) (በመቶኛ) | 5.65 | 3 |
| የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ | 1:50 | 1:50 |
| የተማሪ መምህር ጥምርታ | 1:50 | 1:50 |
| የተማሪ መጽሐፍ ጥምርታ | 1:2 | 1:1 |
| የሰለጠኑ መምህራን ድርሻ (1-4) (በመቶኛ) | 2.2 | 80 |
| የሰለጠኑ መምህራን ድርሻ(5-8) (በመቶኛ) | 66.4 | 100 |
| ጥቅል የፆታ ልዩነት (GPI) | 0.98 | 1 |
| የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም | | |
| ጥቅል ተሳትፎ መጠን(9-10) (በመቶኛ) | 38.4 | 60 |
| የተማሪ ቁጥር (11-12) | 67,595 | 120,000 |
| የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ(9-10) | 1:41 | 1:40 |
| የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ(11-12) | 1:54 | 1:40 |
| የተማሪ መምህር ጥምርታ(9-10) | 1:67 | 1:30 |
| የተማሪ መጽሐፍ ጥምርታ(9-12) | 1:1 | 1:1 |
| የሰለጠኑ መምህራን ድርሻ (9-10) (በመቶኛ) | 86.7 | 100 |
| የሰለጠኑ መምህራን ድርሻ(11-12) (በመቶኛ) | 96.4 | 100 |
| ጥቅል የፆታ ልዩነት GPI)(9-10) | 0.91 | 1 |
| የሴት ተማሪዎች ድርሻ(GPI)(11-12) (በመቶኛ) | 27.9 | 35 |
| **13. ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና** | | |
| ዓመታዊ የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ስልጠና የመቀበል አቅም | 84012 | 382188 |
| ዓመታዊ የግል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና የመቀበል አቅም | 30807 | 88126 |
| የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ብዛት | 62 | 130 |
| የግል ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ብዛት | 47 | 72 |

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ | መድረሻ |
|---|---|---|
| | 2002 | 2007 |
| የመንግስት የፖሊ ቴክኒክ ተቋማት ብዛት | 0 | 18 |
| **14. ጤና ጥበቃ** | | |
| የገጠር የሆስፒታል ብዛት | 10 | 44 |
| የሪፈራል  የሆስፒታል ብዛት | 3 | 6 |
| የጤና ጣቢያ ብዛት | 520 | 820 |
| የጤና ኬላ ብዛት | 2941 | 3978 |
| የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ብዛት | 6200 | 6908 |
| የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ብዛት | 462 | 1047 |
| በጤና ፓኬጅ የተመረቀ ቤተሰብ ብዛት | 68 | 100 |
| የመፀጃ ቤት ሽፋን ( በመቶኛ) | 86 | 100 |
| የእናቶች ሞት ምጣኔ በመቶ ሺ | 590 | 260 |
| የጨቅላ ህፃናት ሞት ምጣኔ በ1 ሺ | 39 | 15 |
| ከ1 ዓመት በታች የህፃናት ሞት ምጣኔ በ1 ሺ | 77 | 31 |
| ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ሞት ምጣኔ በ1 ሺ | 101 | 67 |
| የአዋላጅ ነርስ - በቁጥር | 289 | 1,289 |
| በሰለጠነ የጤና ባለሙያ  የታገዙ ወላጆች ምጣኔ ( በመቶኛ) | 25 | 65 |
| የፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስ መድሃኒት ተጠቃሚ- በቁጥር | 71,000 | 169,600 |
| የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ የማግኘት አቅም በመቶኛ /detection rate/ | 27 | 75 |
| የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ በመቶኛ | 32 | 75 |
| የኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭት መጠን በመቶኛ | 2.8 | 2 |
| በቤታቸው 2 አኀበር ያላቸው ቤተሰቦች ብዛት በመቶኛ | 90 | 100 |
| **15 . ወጣቶችና ስፖርት** | | |

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ 2002 | መድረሻ 2007 |
|---|---|---|
| በወጣቶች ማህበራት የታቀፉ ወጣቶች (በመቶኛ) | 1,388,386 (29%) | 3,681,092 (77%) |
| የወጣት ተኮር ማዕከላት (በቁጥር) | 217 | 1717 |
| ክልሉ ተወዳዳሪ የሚሆንባቸው የተመረጡ ስፖርቶች (በቁጥር) | 2 | 6 |
| በስፖርት ለሁሉም የሚሳተፍ ዜጋ (በመቶኛ) | - | 70 |
| **16. ብዙሃን መገናኛ** | | |
| የመደበኛ ሬዲዮ አገልግሎት ሽፋን/ተደራሽነት በመቶኛ፣ | 40 | 100 |
| የመደበኛ ሬዲዮ አገልግሎት ቋንቋ በቁጥር | 4 | 5 |
| የኤፍ ኤም ሬዲዮ አገልግሎት ሽፋን/ተደራሽነት በመቶኛ፣ | 2 | 75 |
| የቴሌቪዥን አግልግሎት ሽፋን | ETV | 100 |
| የቴሌቪዥን አግልግሎት የስርጭት ቋንቋ በቁጥር | 1 | 5 |
| የህትመት ሜዲያ ስርጭት ሽፋን/ ተደራሽነት | | |
| ➢ አማርኛ በቅጅ መጠን | 5000 | 10,000 |
| ➢ አዊኛ በቅጅ መጠን | 0 | 3,000 |
| ➢ ኽምጠኛ በቅጅ መጠን | 0 | 3,000 |
| ➢ ኦሮምኛ | 0 | 3,000 |
| ➢ እንግሊዝኛ በቅጅ መጠን | 0 | 1,000 |
| የህትመት ሚዲያ አገልግሎት በቋንቋ ዓይነት፣ | 1 | 5 |
| በሚዲያ የህብረተሰብ ርካታ በመቶኛ | 30 | 85 |
| ሬዲዮ ያለቸው ቤተሰቦች ብዛት በሚሊዮን | 0.72 | 2 |

# ክፍል አራት

## 4. የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት ዕቅድ

### *4.1. ግብርና ልማት*

**የትኩረት አቅጣዎች**

*የግብርናና ገጠር ልማት የፖሊሲ አቅጣጫ አርሶ አደሩ ዘመናዊ የግብርና ልማት ቴክኖሎጂዎችን በብቃት እንዲጠቀም በማስቻልና አዳዲስ የግብርና አሰራሮችን ተግባራዊ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ እንዲሁም የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሃብቱ በግብርና ልማት ዘርፍ የሚኖራቸውን ድርሻ ከፍ እንዲል በማድረግ ክልሉን ብሎም ሀገሪቱን ከድህነት ማውጣት ነው። በአለፉት አምስት ዓመታት ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በመከተል ኢኮኖሚው ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል። በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የኢንዱስትሪው ልማት ዘርፍ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ሚና መጫወት እንዲችል፣ የሕብረተሰቡ የምግብ ፍጆታ ለሟሟላት እና ለውጭ ምንዛሪ የሚያስፈልጉ ምርቶች ለማምረት ግብርና ልማት የመሪነቱን ሚና እንዲጫወት የግብርና ልማት ስትራቴጂ የሚቀጥል ይሆናል።*

*ባለፉት አምስት ዓመታት* (1998-2002) *ከተመዘገቡ የግብርና ልማት ዕቅድ የአፈፃፀም ውጤቶችና በአፈጻጸም ሂደት ከተገኙ መልካም ተሞክሮዎች በመነሳት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የአነስተኛ አርሶ አደር ምርታማነት ጉልበትን፣ መሬትን፣ የተሻሻሉ የግብርና ዘዴዎችንና አነስተኛ ካፒታል የሚጠይቁ አነስተኛ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በአጭር ጊዜ በከፍተኛ መጠን ማሳደግ እንደሚቻል በተግባር ማረጋገጥ ተችሏል። የግብርና ምርቶችን በጥሬ ዕቃነት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ፍላጎት በማደጉ ለግብርና ምርቶች ያለው ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል። በክልላችን ለግብርና ኢንቨስትመንት የሚውል ሰፊ መሬት ባይኖርም በተለይ በሰሜን ምዕራብ የክልሉ አካባቢዎች ከአሁን በፊት ለግብርና ኢንቨስትመንት የተሰጡ መሬቶችን ወጤታማ በማድረግና አዳዲስ ለኢንቨስትመንት የሚውል መሬት ያላቸው አካባቢዎችን በማጥናት በግል ባለሀብቱ በስፋት የሚውልበት ሁኔታም ይፈጠራል።*

**የአርሶ አደር ግብርና ልማት**

*አርሶ አደሩ ለዘመናት ይከተለው ከነበረው ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ የግብርና ዘዴ በገበያ በተለይም በዓለም ገበያ ወደሚመራ የአመራረት ዘዴ እንዲለወጥ በማድረግ ረገድ የተገኘው ውጤት ከፍተኛ በመሆኑ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታትም ይኸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል። በዚህ ረገድ የአነስተኛ አርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ቁልፍ ተግባር ይሆናል። የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ከማሳደግ አንጻር ሦስት መሠረታዊ አቅጣጫዎች ላይ ትኩረት ይደረጋል።*

**ሀ. በምርጥ አርሶ አደሮችና ሌሎች አርሶ አደሮች መካከል ያለውን የምርታማነት ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ ማጥበብ፤**

*የአነስተኛ አርሶ አደሩ አማካይ ምርታማነት ከምርጥ አርሶ አደሮች ምርታማነት ጋር ሲነፃፀር ከሁለት እስከ ሦስት እጥፍ የሚያንስበት ሁኔታ ስላለ በማስፋት ስትራቴጂ ትግበራ አማካኝነት አማካይ የአርሶ አደሩን ምርታማነት ወደ ምርጥ አርሶ አደሮች ምርታማነት ደረጃ የተጠጋ እንዲሆን በማድረግ ዋነኛው የግብርና ዕድገት ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ይሆናል። ይህን ለማድረግ የሚያስችል ሰፊ የገጠር ልማትን የሚደግፍ መዋቅር ተዘርግቶ በየጊዜው አቅሙ እየተጠናከረ የመጣ ሲሆን በማስፋት ስትራቴጂ መሠረት ምርትና ምርታማነት የበለጠ ለማሳደግ በሚያስችል ሁኔታ አርሶ አደሩን የሚደግፍ የመንግስት መዋቅር ቀጣይነት የማጠናከርና አርሶ አደሩ ያለው ለልማት መነሳሳት የተደራጀና ውጤታማ እንዲሆን የማድረግ ጉዳይ በሚቀጥሉት አምስት ዓመት መሠረታዊ የግብርና ዕድገት አቅጣጫዎች ይሆናሉ። ቀጣይነት ያለው የግብርና ዕድገት ለማረጋገጥ ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ማካሄድ የሚያስፈልግ በመሆኑ ዋናው ትኩረት በምርጥ አርሶ አደሮችና በሌሎች አርሶአደሮች መካከል በሄ/ር ያለውን የምርታማነት ልዩነት ማጥበብ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚሁ በተጓደኝ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ሰፋ ባለ መልኩ በሙከራ ደረጃ የመተግበርና ውጤታማነታቸው ሲረጋገጥ በማስፋት ስትራቴጂ ማዕቀፉ ለሁሉም አርሶ አደሮች እንዲደርስ የማድረግ ሥራም ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።*

**ለ. በህዝብ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ስራ ማካሄድ፤**

*የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ልማት ላይ በመመስረት የውሃ አጠቃቀም ማሻሻልና የመስኖ ሥራን በማስፋፋት የግብርናን ዕድገት የማፋጠንና ቀጣይነቱንም የማረጋገጥ አቅጣጫ ነው። ይህም በሚታረስና በማይታረስ መሬት ዙሪያ ሰፊ የአፈርና ውኃ ጥበቃ ስራ በመስራት፤ በማይታረስ መሬት ላይ አካባቢውን ከመጠበቅ አልፎ የህዝቡን ኑሮ በብቃት የሚደግፍ የአግሮ ፎረስተሪ ስራ በማካሄድ የከርሰ ምድርን ውኃ ማበልጸግና ለመስኖ ልማት ስራ መስፋፋት ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል። በአጠቃላይ የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ በማካሄድ የከርሰ ምድርና ገፀ ምድር ውሃን በማበልፀግ የውሃ አጠቃቀምን ማሻሻልና የመስኖ ሥራን ማስፋፋት በቀጣይ አምስት ዓመታት ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ይሆናል።*

*ከዚህ አኳያ ሁሉም አርሶ አደር እንደየአካባቢው የውሃ አቅም ሁኔታ አነስተኛ የውሃ ጉድጓድ በመቆፈርና፣ የገፀ ምድር ውሃን በማጎልበትና በመጥለፍ፣ የዝናብ ውሃን ከጣራና ከጎርፍ በማጠራቀምና በማሰባሰብ አነስተኛ ባህላዊ የወንዝ ጠለፋ በማካሄድ ወዘተ የአነስተኛ መስኖ ልማት ላይ በትኩረት ርብርብ እንዲአደርግ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል ።*

*ይህን ለማሳካት በዋነኛነት የአርሶ አደሩንና የደጋፊ የመንግስት መዋቅሮችን አቅም በመጠቀምና በቀጣይነትም በመገንባት የሚፈፀም ይሆናል።*

### ሐ. አርሶ አደሩን የተሻለ ዋጋ ወዳላቸው ምርቶች ማሸጋገር

አርሶ አደሩ ከምርቱ የሚያገኘው ገቢ እንዲያድግ የሚደረግበት ሦስተኛው መሠረታዊ አቅጣጫ ነው። አርሶ አደሩ መለስተኛ ዋጋ ያላቸውን ምርቶችን ከማምረት ደረጃ በደረጃ የተሻለ ዋጋ ወዳላቸው ምርቶች እንዲሸጋገር ይደረጋል። ይህም ከአካባቢ ስቴሻላይዜሽን ጋር ተሳስሮ አመታዊ የገበያና የመሠረተ ልማት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ደረጃ በደረጃ የሚፈፀም ይሆናል።

### ዓላማዎች

በሚቀጥለው አምስት ዓመት ግብርና ካለፈው አምስት ዓመት በተሻለ ፍጥነት እንዲያድግ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ አለ። ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለው የአርሶ አደር ምርታማነት በአጭር ጊዜ በከፍተኛ መጠን ማሻሻል እንደሚቻል በመረጋገጡ የአርሶ አደሩን ምርታማነት ገበያ መር በሆነ አቅጣጫ በፍጥነት በማሳደግ ፈጣን የግብርና ልማትን ማረጋገጥ ይቻላል። ለኢንዱስትሪ ልማት የሚሆን የጥሬ ዕቃዎች ፍላጐት በከፍተኛ መጠን እየጨመረ እንደመጣ ሁሉ የግብርና ምርቶች ገበያም ለልማቱ አመቺ በመሆኑና በዘርፉ የሚደረግ ኢንቨስትመንት በዓለም አቀፍ ደረጃ እያደገ በመሆኑ ሰፋፊ ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሬቶችን ጥቅም ላይ ለማዋል ምቹ ሁኔታ በመፈጠሩ የግሉ ዘርፍ በግብርና ልማት መስክ ከመቼውም የተሻለ ድርሻ ሊጫወት የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ስለሆነም በቀጣዮቹ አምስት ዓመታት /2003-2007/ ግብርና የኢኮኖሚው ዕድገት ዋነኛ ምንጭና የአርሶ አደሩ እርሻ ዋነኛው የግብርና ዕድገት ምንጭና መሠረት ሆነው እንዲቀጥሉ እንዲሁም የግሉ ዘርፍ በግብርና መስክ የሚኖረው ድርሻ ከፍተኛ እምርታን በማስመዝገብ አንድ መሠረታዊ የግብርና ዕድገት ምንጭ ሆኖ እንዲመጣ ማድረግ የዕቅዱ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

### ግቦች

የዘርፉን የሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ዕቅድ ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተጥለዋል።

### ሀ/ የሰብል ምርትና ምርታማነት

#### በመኸር ሰብል

በቀጣይ አምስት አመታት /2003-2007/ የመኸር ምርትን በ2001/2002 ምርት ዘመን ከለማው 4,102,176 ሄክታር መሬት (CSA,2002) የተገኘውን 61.91 ሚሊዮን ኩንታል ምርት በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ /2007/ ወደ 152.42 ሚሊዮን ኩንታል ማሳደግና በምርታማነት ረገድ አሁን ያለውን በአንድ ሄክታር የሚመረት ምርት ከ15.1 ኩንታል ወደ 37.16 ኩንታል ለማሳደግ ግብ ተጥሏል።

ከላይ የተቀመጠዉን የሰብል ምርት እድገት ግቦች ለማረጋገጥ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይከናወናሉ

- በ2002/03 በክልሉ ጥቁር አፈርን በማጠንፈፍ እየለማ ያለውን 95ሺ ሄክታር መሬት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ /2007/ ወደ 700ሺ ሄክታር ማድረስ፣
- በክልሉ አሲዳማ አፈርን ኖራን በመጠቀም ለማከም የሚደረገውን ጥረት በማጠናከር አሁን ካለበት /2002/ 1,224 ሄክታር መሬት አመታዊ አፈጻጸም በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ /2007/ አመታዊ አፈጻጸሙን ወደ 24,310 ሄክታር ማሳደግ፣
- በክልሉ በአርሶአደር ደረጃ እየተዘጋጀ ያለውን የተፈጥሮ ማዳበሪያ አሁን ካለበት 37 ሚሊዮን ሜትር ኩብ ወደ 72 ሜትር ኩብ ማሳደግ
- በክልሉ በልዩ ልዩ ፀረ ሰብል ተባዮች በየዓመቱ የሚባክነውን 24 በመቶ ምርት በመጨረሻው ዓመት ወደ 10 በመቶ ዝቅ ማድረግ
- በክልላችን በመንግስትና በሕብረተሰብ ችግኝ ጣቢያዎች የሚፈላውን የደጋና የቆላ የፍራፍሬ ችግኝ ከ2.18 ሚሊዮን ወደ 12.3 ሚሊዮን ማሳደግ

**በበልግ**

በሚቀጥሉት አምስት አመታት የበልግ ወቅትን በመጠቀም በ2002 በጀት ዓመት በልማት ላይ የዋለውን 249,949 ሄክታር መሬት በመጠቀምና ምርታማነቱን በማሳደግ የተመረተውን 3.41 ሚሊዮን ኩንታል በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 6.82 ሚሊዮን ኩንታል የማሳደግ ግብ ተጥሏል።

**በመስኖ ሰብል**

በቀጣዩ የስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን የተለያዩ የመስኖ ማልሚያ ዘዴዎችን በመጠቀም በመስኖ የሚለማ መሬትን በ2002 ከነበረው 444,620 ሄክታር ወደ 950ሺ ሄክታር በማሳደግ ከመስኖ ልማት የሚገኝ ምርትን ከ51.38 ሚሊዮን ኩንታል ወደ 100 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ ።

**ሐ/ የእንስሳት ሃብት ልማት**

በዚህ ንኡስ ዘርፍ በተለይም የእንስሳት ምርት ውጤቶች ዕቅድን አስመልክቶ

- የእንስሳት ተዋጽኦ ምርትን በሚመለከት በ2002 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት ዓመታዊ አፈጻጸም በቀጣዩ አምስት የመርሐ ግብር ዓመታት መጨረሻ /2007/ የሥጋ ምርትን ከ249,703 ቶን ወደ 749,109 ቶን፣ የወተት ምርትን ከ506,007 ቶን ወደ 1,518,021 ቶን፣ የእንቁላል ምርትን ከ26.88 ሚሊዮን ወደ 107.5 ሚሊዮን፣ ጥራቱን ጠብቆ ለመሀል አገር ገበያ የሚቀርበውን የቆዳና ሌጦ ምርትን ከ 4.5 ሚሊዮን ወደ 13.72 ሚሊዮን፣ የማር ምርትን ከ10,792.8 ቶን ወደ 32,378 ቶን፣ የሰም ምርትን ከ282.7 ቶን ወደ 848.1 ቶን እንዲሁም በተለያዩ የውኃ አካላት የዓሣ ጫጩት በመጨመርና የተሻሻሉ የዓሣ ማስገሪያ መሣሪያዎችን አቅርቦት በማሻሻል የዓሣ ምርትን አሁን ካለበት 6,880.8 ቶን አመታዊ የምርት መጠን ወደ 20,642.4 ቶን ለማሳደግ ታቅዷል።

- መኖ ልማትን በሚመለከት በቀጣይ አምስት ዓመታትም /2003-2007/ የመኖ ልማት አቅርቦትን የማሳደግ ሥራ በሠፊው የሚከናወን ተግባር ይሆናል። ለዚህም የሚከተሉት ግቦች ተጥለዋል።

- ***የግጦሽ መሬቶችን አጠቃቀም በማሻሻልና በተለያዩ ስልቶች መኖ በማልማት*** በ2001/02 ***ምርት ዘመን የተመረተውን*** 22.1 ***ሚሊዮን ቶን የደረቅ መኖ ምርት ወደ*** 74.6 ***ሚ/ቶን ማሳደግ፣***
- ***የተረፈ ሰብል ንጥረ ነገር ይዘት የማሻሻል ቴክኖሎጅ በመጠቀም በዩሪያ የማከም ተግባር*** በ2002 ***የነበረውን*** 4,919 ***ቶን አመታዊ አፈጻጸም በማሳደግ*** በ2007 ***ወደ*** 19,676 ***ቶን ማድረስ፣***
- ***ከልቅ ግጦሽ ነጻ የሆነና የተሻሻለ የግጦሽ መሬት*** በ2002 ከነበረው 227,360 ሄክታር በ2007 ***ወደ*** 909,440 ሄክታር ***ማድረስ፣***

- ***የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋንን*** ከ80 ***በመቶ ወደ*** 100% ***ማሳደግ እንዲሁም የእንስሳት ጤና የቆዳ ሽፋን አሁን ካለበት*** 88 ***በመቶ ወደ*** 100% ***ማሳደግ፣***
- ***ዝርያ ማሻሻልን በሚመለከት ለዳልጋ ከብት እየተሰጠ ያለውን ዓመታዊ የሰው ሰራሽ የማዳቀል አገልግሎት አሁን ካለበት*** 40,013 ***ወደ*** 192,536 ***ማሳደግ፣***
- ***የሚደልቡ የዳልጋ ከብቶች ብዛትን አስመልክቶ*** በ2002 ***ዓ/ም መጨረሻ በቁጥር ከነበረው*** 469,339 በ2007 ***ዓ/ም መጨረሻ ወደ*** 1,877,356 ***ከፍ ለማድረግ፣ የሚሞከቱ በጐችና ፍየሎችን ብዛት በቁጥር*** ከ1,590,430 ***ወደ*** 6,361,720 ***እና ለእርድ የሚቀርቡ ዶሮዎች ብዛትንም*** ከ12.5 ***ሚሊዮን ወደ*** 50 ***ሚሊዮን ለማሳደግ ግብ ተጥሏል።***

### ***መ/ የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም***

***በቀጣይ አምስት ዓመታት*** /2003-2007/ ***ለሚመረቱ ልዩ ልዩ ሰብሎች የአርሶአደሩን የግብርና ግብዓት ፍላጎት መሠረት ያደረገ የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት ትኩረት የተሰጠው ነው። በመሆኑም፤***

- ***የማዳበሪያ አቅርቦትን በተመለከተ*** በ2002/2003 ***ምርት ዘመን ከተደረሰበት*** 2.2 ***ሚሊዮን ኩንታል የኬሚካል ማዳበሪያ /ዩሪያና ዳፕ/*** በ2006/07 ***ወደ*** 5.3 ***ሚሊዮን ኩንታል አቅርቦቱን በማሳደግ ማሰራጨት፣***
- ***የምርጥ ዘር አቅርቦትን አስመልክቶ*** 2002/2003 ***ምርት ዘመን መጨረሻ ይቀርባል ተብሎ ከተገመተው (በልግና መስኖ ጨምሮ)*** 129000 ***ኩንታል ምርጥ ዘር*** በ2006/07 ***ወደ*** 1816608 ***ኩ/ል አቅርቦትን በማሳደግ ማሰራጨት፣***
- ***ለግብርና ግብዓቶችና ምርት ግብይት አገልግሎት ብድር አቅርቦት*** በ2002 ***ዓ.ም የነበረውን ብር*** 1.2 ***ቢሊዮን በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ወደ ብር*** 8 ***ቢሊዮን ማድረስ፣***
- ***ለግብዓትና ግብይት ከተሰጠ ብድር የተመለሰ የብድር መጠን በመቶኛ አሁን ካለበት*** 85 ***በመቶ ወደ*** 100% ***ማሳደግ፣***

### ***ሠ/ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና አያያዝ***

- ***የተቀናጀ የተፋሰስ ልማትን መሰረት ያደረገ የአፈርና የእርጥበት እቀባ ስራዎችን አሁን ካለበት*** 12,609 ***ንዑስ ተፋሰሶች ወደ*** 30,041 ***ከፍ በማድረግ ያሉትን ተፋሰሶች በሙሉ*** በ3 ***ዓመት ውስጥ*** 100 ***በመቶ ጥናታቸውን በማጠናቀቅ ወደ ልማት ማስገባት፣***

- ተዳፋትነት ያላቸውን መሬቶችን በመከለል ከንክኪ ነፃ በማድረግ ፣ የአፈርና የእርጥበት ዕቀባ እና የደንና ጥምር ደን ልማት በማካሄድ አሁን ካለበት 538,838 ሄክታር ውስጥ በቀጣይ ሶስት አመት 2,355,241 ሄክታር በተጨማሪ በመስራት ሊከለልና ሊጠበቅ የሚችለውን የተራቆተ መሬት 100 በመቶ ማጠናቀቅ፣
- በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የደንና አግሮፎረስትሪ ልማትና ጥበቃን በተጠናከረ መንገድ በማካሄድ አሁን ካለበት 7.85 በመቶ የደን ሽፋን ላይ 1.2 በመቶ በየዓመቱ በማሳደግ 13.85 በመቶ ማድረስና ለምርት መሰብሰብ ከደረሰ የመንግስትና የፕሮጀክት ደን ውስጥ 90 በመቶው ጥቅም ላይ በማዋል መልሶ መተካት፣
- በማሳ ላይ የአፈር ጥበቃና እርጥበት ዕቀባ ሥራ አሁን ካለበት 2.1 ሚሊዮን ሄክታር የማሳ ሽፋን በቀጣይ ሶስት አመታት ተጨማሪ 2 ሚሊዮን ሄክታር በመስራት በማሳ ላይ የአፈር ጥበቃና እርጥበት ዕቀባ ሥራን ወደ 4.1 ሚሊዮን ሄክታር በማድረስ ሙሉ በሙሉ ማጠናቀቅ።
- የቦረቦር መሬትን በፊዚካልና በሥነ ህይወታዊ ዘዴ የማዳንና የማልማት ሥራ አሁን ካለበት 25,940 ሄክታር በቀጣይ ሶስት አመታት 156,140 ሄክታር ተጨማሪ በመስራት የታከመ የቦረቦር መሬትን ወደ 182,080 ሄክታር ማድረስ።
- የተለያዩ የደን ምርት ውጤቶች በተመለከተ በ2002 ዓ.ም ተመርቶ ከነበረው 426,902 ሜ/ኩብ በ2006/2007 ወደ 1,140,318 ሜ/ኩብ ማድረስ፣
- የተፈጥሮ ዕጣንና ሙጫ ምርት በ2002 ዓ/ም ይገኛል ተብሎ የሚገመተውን 22,760 ኩንታል አመታዊ ምርት በመረሃ ግብሩ መጨረሻ ወደ 30ሺ ኩንታል በማሳደግ በአጠቃላይ በመርሐ ግብሩ 150ሺ ኩንታል በማምረት ለገበያ ማቅረብ፣
- አሁን ያለዉን 66 በመቶ የችግኝ መጽደቅ አቅምን በማጎልበት ወደ 80 በመቶ ማሳደግ፣

### ረ/ የግብርና ኤክስቴንሽን

በቀጣይ አምስት ዓመታት /2003-2007/ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በስፋት ተጠናክሮ እንዲሰጥ የሚደረግ ሲሆን፣

- የማስፋት ስትራቴጅውን በመጠቀም 3.6 ሚሊዮን የሚገመተውን የቤተሰብ ኃላፊ በተለያዩ የግብርና ፓኬጆች በማሳተፍ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ።
- በሁሉም ፓኬጆች የሴቶች ተሳትፎን 50 በመቶ ማድረስ።
- አሁን ያሉትን 2,401 ነባር የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ግንባታ ወደ 3,126 ማሳደግ፣ የውስጥ ቁሳቁስ የተሟላላቸውን 1,453 የማሰልጠኛ ተቋማት ወደ 3,126 እንዲሁም አሁን ያሉትን 1,192 ሠርቶ ማሳያ የተሟላላቸውን የማሰልጠኛ ተቋማት ወደ 3,126 ማሳደግ።

### ሰ/ ግብርና ምርምር

የግብርና ምርምር በተመለከተ በቀጣይ አምስት ዓመታት /2003-2007/ ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ እና ውጤታማነታቸው የተመሰከረላቸውን ቴክኖሎጂዎችን በማላመድና የመነሻ ቴክኖሎጂዎችን በማውጣት ለአርሶ አደሩ ማሰራጨት በስፋት ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን፣

**በሰብል ምርምር ቴክኖሎጅ አቅርቦት**

- የሰብል ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ጥራትን ሊጨምሩ የሚችሉ 96 የተሻሻሉ የሰብል ዝርያዎችን፣ የሰብል አመራረት ቴክኖሎዎችን እና የተባይ፣ በሽታና አረም ቁጥጥር ዘዴዎችን ማላመድና ማውጣት፣

**በእንስሳት ምርምር ቴክኖሎጅ አቅርቦት**

- በዳልጋ ከብት፣ በበግና ፍየል፣ በዶሮ ፣በንብ፣ በሀር ትል ልማት እና በዓሣ የምርምር ሥራዎች ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉና በገበያ ተፈላጊ የሆኑ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና የተሻሻሉ አሰራሮችን በማላመድና በማመንጨት 53 የሚሆኑ ቴክኖሎጅዎችን ማቅረብ ፣

**በደን ምርምር ቴክኖሎጅ አቅርቦት**

- የአፈር ክለትን ለመከላከል፣ የደን መጨፍጨፍና የመሬት መራቆትን ለመቀነስ በአጭር ጊዜ ለማገዶነት የሚውሉ የዛፍና የቁጥቋጦ ዝርያዎችን የመምረጥና የማላመድ፣ ሰብልን ከዛፎች ጋር በማላመድ የአፈር ለምነትን በመጠበቅ ምርታማነትን መጨመር፣ እንዲሁም ለተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ደን አያያዝና አጠቃቀም አስፈላጊ የሆኑ 45 ቴክኖሎጅዎችን ማላመድና ማውጣት፣

**በአፈርና ውኃ ምርምር የቴክኖሎጅ አቅርቦት**

- የአፈር ክለትን ለመከላከል፣ የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ፣ የተራቆቱ ሥፍራዎችን እንዲያገግሙ በማድረግ የሰብል ልማትን ለማሻሻል፣ የእንስሳት መኖ ለማምረት፣ የመስኖ ውኃንና መሬትን በአግባቡ ለመጠቀም ፣ የግብርና ምርት ማነቆዎችን ለይቶ በማወቅና የአመራረት ስልቶችን ለማስተካከል የተለያዩ 72 ቴክኖሎጅዎችን የማመንጨት ሥራ ይከናወናል።

**በግብርና ሜካናይዜሽን እና ምግብ ሳይንስ ቴክኖሎጅ አቅርቦት**

- የክልሉን የግብርና ሴክተር ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የአነስተኛና መካከለኛ አርሶአደሮችን የልማት አሰራር ዘመናዊ ለማድረግ እንዲሁም የግብርና ምርትን በማሰባሰብ፣ በማከማቸትና ፣ በማቀናበር ወቅት ያሉትን ብክነቶች ለመቀነስ የሚያስችሉ 50 ቴክኖሎጅዎችን ማውጣት፣

**የመነሻ ዘር ብዜት ማካሄድ**

- 7110 ኩንታል የሰብል ዘር ፣ 1.5 ሚሊዮን የስኳር ድንች ቁርጥራጭ ፣ 400 ሺ የድንች ዝርያ በቲሹ ካልቸር፣ 115 ሺ የፍራፍሬ ችግኞች በማባዛት ይሰራጫሉ።

**ሸ/ የህብረት ሥራ ማህበራት**

በቀጣይ አምስት ዓመታት /2003-2007/ የህብረት ሥራ ማህበራትን በማጠናከር ረገድ የሚከተሉት ግቦች ተጥለዋል።

- የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የቀበሌ ሽፋን 100% በማድረስ በግብዓትና በግብርና ምርት ግብይት የተሳለጠ አገልግሎት የሚሰጡ የገ/ሁለገብ ኅ/ሥራ ማኅበራትን በማቋቋም

የመሠረታዊ ማኅበራትን ቁጥር አሁን ካለበት 5,977 በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 9,171 ማድረስ፣ የዩኒዬኖችን ቁጥር ከ43 ወደ 62 ማሳደግ እና አንድ ፌደሬሽን ማቋቋም፣

- የቤተሰብ ኃላፊዎችን የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባልነት ሽፋን አሁን ካለበት 72.8 በመቶ በአምስት ዓመቱ መጨረሻ ወደ 100% ማድረስ፣
- የመሠረታዊ ማህበራትን ካፒታል አሁን ካለበት ብር 319.37 ሚሊዮን ወደ ብር 1.72 ቢሊዮን ማድረስ፣ የዩኔዬኖችን ካፒታል አሁን ካለበት ከብር 213.5 ሚሊዮን ወደ 1.15 ቢሊዮን ማድረስ፣ በጥቅሉ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ካፒታል አሁን ካለበት 532.87 ሚሊዮን ወደ ብር 2865.89 ሚሊዮን ማድረስ
- በኅብረት ሥራ ማህበራት የሴት የአባልነት ተሳትፎ በመቶኛ አሁን ካለበት 22 በመቶ ወደ 47 በመቶ ማሳደግ፣ የሴት አመራሮች ተሳትፎ አሁን ካለበት 15 በመቶ ወደ 25 በመቶ ማሳደግ፣
- በማህበራት የተቋቋሙ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ተቋማት ብዛት አሁን ካለበት 2 ወደ 11 ማሳደግ፣

**ቀ/ የግብርና ግብይት**

በቀጣይ አምስት አመታት ከላይ እንደሚመረት በዕቅድ ከተያዘው የስብል፣ የተፈጥሮ ሀብትና የእንሰሳት ምርት ውጤት ውስጥ ለገበያ/ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ/ የሚቀርበው እንደሚከተለው ግብ ተጥሏል፣

- በክልሉ ከሚመረተው የሰብል ምርት ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚቀርበውን በ2001/2002 ከነበረው 39,771,940 ኩንታል በ2006/2007 የምርት ዘመን ወደ 63,131,886 ኩንታል ማሳደግ
- ጥራታቸውንና የዓለም አቀፍ ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ ምርቶችን እና ለውጭ ገበያ የሚላኩ የምርት ዓይነቶችን ቁጥር በማሳደግ ለውጭ ገበያ የሚላከውን የሰብል ምርት ወደ 7,465,500 ኩንታል ማሳደግ፣
- 3,468,704 የቁም እንስሳትን ለአገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ ፣145,685 የቁም እንስሳትን ለውጭ ገበያ ማቅረብ፣ 839,504 ቶን የእንስሳት ምርት/ ስጋ፣ ወተት፣ እንቁላል ፣ ማር፣ አሳ ወዘተ/ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፣ 7,974.9/ በሺ ቁጥር/ የቆዳና ሌጦ ምርት ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፣ 933,060 ሜትር ኩብ የደን ምርት ውጤቶች ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፣ 29,400 ኩንታል የዕጣንና ሙጫ ምርት ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፣
- ክልላዊ ብራንድ የተፈጠረላቸው ምርቶችን ቁጥር ወደ 9 ዓይነት ማሳደግ፣
- የግብይት መሰረተ ልማቶችን ማስፋፋት: አንድ የነበረውን ዘመናዊ የእንሰሳት ገበያ ወደ 3 ማድረስ፣ አሁን ያሉትን 23 የመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ግብይት ማዕከላት ወደ 42 ማሳደግ፣ 15 ደረጃውን የጠበቀ የግብይት መጋዘን መገንባት

***በ/ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም***

*ሥር በሰደደ የምግብ ዋስትና መታጣት ችግር ውስጥ ያለውን ሕዝብ የምግብ ዋስትናውን የማረጋገጥ ሥራ በቀጣዮቹ ሶስት ዓመታት ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን የሚከተሉት ግቦች ተጥለዋል፣*

- *አሁን ያለውን* 2,294,150 *ስር በሰደደ የምግብ ዋስትና መታጣት ችግር ውስጥ የሚኖረውን ህዝብ በልማታዊ ሴፍቲኔት የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ በማድረግ በ*2007 *ወደ* 255,717 *ሕዝብ ዝቅ ማድረግ፣*
- *በልማታዊ ሴፍቲኔት የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ታቅፈው እስከ* 2002 *ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ያልተመረቁትን* 407,687 *የቤተሰብ ኃላፊዎች በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ በማድረግ ሙሉ በሙሉ በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ማስመረቅ፣*
- *በተለያዩ የአደጋ ክስተቶች የሚጋለጠውን ህዝብ ብዛት አሁን ከላለበት* 651,698 *ህዝብ ወደ* 269,934 *መቀነስ ፣*
- *ክልላዊ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ በመቋቋም የመጠባበቂያ ሀብት ብር* 30 *ሚሊዮን ማድረስ፣*

***ተ/ የግል ባለሀብት የግብርና እንቅስቃሴ***

*በግብርና ኢንቨስትመንት በግል ባለሀብት የሚለማ መሬት በማስፋፋት አሁን ካለበት* 196171.1 *ሄክታር በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ወደ* 295,707 *ሄክታር እንዲለማ በማድረግ* 13,517,392 *ኩንታል ምርት ማምረት*

## ***የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች***

***የሰብል ልማት***

*በቂ ርጥበት በሚያገኙ አካባቢዎች ዋናው ትኩረት የማስፋት ስትራቴጂውን መፈፀም ነው። አካባቢዎቹ ርጥበት በበቂ ሁኔታ የሚያገኙ በመሆኑ ምርጥ ልምዶችን የማስፋፋት ተግባር የዝናብ ውሃን በአግባቡ በመጠቀምና ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችንና የተሻሻሉ የግብርና የአሰራር ዘዴዎችን አማልቶ በመተግበር የሰብል ምርትና ምርታማነትን ወደ ላቀ ደረጅ ለማሸጋገር በሚያስችል አግባብ እንዲፈፀም ይደረጋል።*

*የማስፋት ስትራቴጂው አንኳር ጉዳይ በምርጥ አርሶ አደሮች ደረጃ ተፈትሸው ውጤታማ መሆናቸው የተረጋገጡ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችንና የግብርና የአሰራር ዘዴዎችን ወደ ሁሉም አርሶ አደሮች ማድረስ ነው። ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግም የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያስችል አቅጣጫ የመቀየስና አቅም የመገንባት ሥራዎች ይሰራሉ።*

*የማስፋት ስትራቴጂውን ከመተግበር አኳያ በቅድሚያ ምርጥ ልምዶች በየቴክኖሎጂው ዓይነት እንዲቀመሩ ይደረጋል። የምርጥ ልምድ መቀመር ሥራ አንዴ ተሰርቶ የሚቆም ባለመሆኑ በትግበራ ሂደት ከሚገኙ ምርጥ ተሞክሮዎች እየዳበረ የሚሄድ ይሆናል። በምርጥ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች ላይ ለባለሙያውና ለአርሶ አደሩ በቂ ክህሎት የሚያስጨብጥ የተግባር ሥልጠና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ*

*ጣቢያዎችና በምርጥ አርሶ አደር ማሳ ላይ በመመስረት ይሰጣል። ከቴክኖሎጂው ጋር ተያይዘው የሚታዩ የአመለካከት ችግሮችም ተነቅለው በመስተካከል አመለካከት እንዲተኩ ይደረጋል። በአመለካከትና በክህሎት ያሉ ችግሮች ከተቀረፉ በኋላ ምርጥ ቴክኖሎጂውን የመጠቀም እምነትና ፍላጎት ስለሚፈጥር ይህን የሚያሟላ የቴክኖሎጂ አቅርቦት እንዲረጋገጥ ይደረጋል። በዚህ ረገድ የቴክኖሎጂ ግብዓት አቅርቦት ስርዓታችንን ወጥ አድርጐ በመገንባት የማስፋት ስትራቴጂውን በሚያሳካ አግባብ እንዲስተካከል ይደረጋል። በማስፋት ስትራቴጂው አማካኝነት የሚመጣን ከፍተኛ የምርት ጭማሪ ተገቢውን ገበያ እንዲያገኝ የሚያስችል ግልጽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የግብይት ሥርዓት የመዘርጋት ሥራ ይፈፀማል።*

*በየደረጃው ያሉ ፈፃሚዎች የተፈጠረላቸውን አቅም በመጠቀም አርሶ አደሮችን የማሰልጠንና ምርጥ አርሶ አደሮች ማሣ ላይ ተመስርተው የልማት ቡድን አባላት በተግባር ምርጥ ልምዱን እንዲቀስሙ ያደርጋሉ። ልምዱም በሁሉም አርሶ አደሮች ደረጃ ተሟልቶ እንዲተገበር ተከታታይ የሙያ ድጋፍ በኤክስቴንሽን አደረጃጀቱ መሠረት ይሰጣል።*

*የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የአፈር ለምነትን የሚያሻሽሉ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች ይሰፋፋሉ። በዚህ ረገድ እያደገ ከመጣው የኬሚካል ማዳበሪያ አጠቃቀም ጐን ለጐን የተፈጥሮ ማዳበሪያ አጠቃቀም መጠንና የሚሸፍነው የመሬት ስፋት እንዲያድግ በቴክኖሎጂው ላይ ግንዛቤና ክህሎት የመፍጠር ሥራ በስፋት ይሠራል። በቂ ርጥበት ባለባቸው አካባቢዎች የሚገኘው የኮትቻ አፈር መሬት ተገቢውን ጥቅም መስጠት እንዲችል በዘመናዊ የማጠንፈፍ ዘዴ በስፋት እንዲለማ ይደረጋል። በጥቅል እየተካሄደ ያለውን የማዳበሪያ አጠቃቀም ደረጃ በደረጃ ለአካባቢያዊ ስነ-ምህዳር፣ የአፈር ዓይነትና በዋና ዋና ሰብሎች ተስማሚ በሚሆን መልኩ የአፈር ምርመራ መሠረት ወደ አደረገ አጠቃቀም የመለወጥ ሥራ ይሰራል። ጥቅም ላይ ከሚውለው ማዳበሪያ ውስጥ 90 በመቶ የሚሆነው በዚህ አግባብ ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ የማዳበሪያ ውጤታማነት የማሳደግ ሥራ ይሰራል። ከዚህ በተጨማሪ አርሶ አደሩ በቀላሉ ሊጠቀምባቸው የሚችላቸውን እንደ ህያው ማዳበሪያ የመሳሰሉ ተፈጥሯዊ ማዳበሪያዎች በማምረትና በማሰራጨት የማስፋት ሥራ ይከናወናል።*

*በቂ ርጥበት ባላቸው አካባቢዎች የሰብል ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አኳያ ሌላው ትኩረት ተሰጥቶ የሚከናወነው ተግባር የተሻሻሉ የግብርና የአሰራር ዘዴዎችን* (Agronomic practices) *አሟልቶ መፈፀም ይሆናል። በዚህ ረገድ ለአፈሩ አይነት ተስማሚ የሆነ ሰብልና ዘር በመምረጥ በቂ የማሳ ዝግጅት በወቅቱ ማድረግ እንዲሁም ትክክለኛውን የዘር ወቅት፣ ጥራትና መጠን ጠብቆ በዘመናዊ አዘራር ዘዴ በመጠቀም የመዝራት ሥራ ይሰራል። በተጨማሪም ተገቢውን የአረም ድግግሞሽ ጠብቆ በማረም፣ ተከታታይ የነፍሳት ተባይና በሽታ አሰሳ በማድረግ ክስተቱ ሲኖርም ፈጣን የመከላከል ርምጃ በመውሰድ የሰብል ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ይደረጋል። በተመሳሳይ የደረሰን ሰብል በአግባቡ በመሰብሰብና ለተባይ በማይጋለጥበት ቦታና ሁኔታ ማከማቸትና ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ጉዳይም ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።*

*በዚህ አካባቢ የዝናብ ውሃን በአግባቡ በመጠቀም ረገድ የሚኖረው ትኩረት እንደተጠበቀ ሆኖ በውሃ አጠቃቀማችን ላይ ለውጥ በማምጣት የመስኖ ሥራን ለማስፋፋት ርብርብ ይደረጋል። ከዚህ አኳያ በቀላሉ የከርሰ ምድር ውሃ ማውጣት በሚቻልባቸው አካባቢዎች አብዛኛው አርሶ አደር የእጅ ጉድጓድ በመቆፈር ለጓሮ አትክልትና ቋሚ ሰብል ልማት እንዲጠቀም የሚያደርግ ሰፊ ሥራ ይከናወናል። የወንዝ ጠለፋ ሥራውን በማጠናከር የአነስተኛ መስኖ ማስፋፋት ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ይፈፀማል። የውሃ ሃብታችን በስፋት ለመጠቀምና አጠቃቀሙንም ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች በስፋት ጥቅም ላይ የሚውሉ ይሆናል። በመስኖ ልማት ሁለት ጊዜ የማምረት ልምድ እንዲሰፋ ምርጥ ልምዶችን በመቀመር የማስፋፋት ሥራ ይሰራል። ከውሃ አጠቃቀማችን አኳያ ከጥቁር አፈር የተንጣፈፈ ውሃን ለደባል ሰብል ልማት የማዋል ተግባር ከጥቁር አፈር ልማት ጋር ተሳስሮ በስፋት እንዲፈፀም ይደረጋል።*

*የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ረገድ የቴክኖሎጂ ብዜት፣ አቅርቦትና ስርጭት ሥርዓት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች ብዜት፣ አቅርቦትና ስርጭት ሥርዓት ለቴክኖሎጂዎቹ የተፈጠረውን ተጨባጭ ፍላጐት በሚያሟላ መንገድ ከፌዴራል እስከ አነስተኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ተሟልቶ እንዲዘረጋ ይደረጋል። በዚህ ሰርዓት አማካኝነት ለቀጣይ አምስት ዓመታት የሚያስፈልጉ የማዳበሪያ፣ምርጥ ዘርና የአነስተኛ እርሻ መሳሪያዎች በጥራት በሚፈለጉበት ጊዜና በሚያስፈልገው መጠን እንዲቀርቡ ይደረጋል።*

*የርጥበት አጠር አካባቢዎች በተደጋጋሚ የርጥበት መታጣት ችግር የሚያጋጥማቸው መሆኑን ግምት ውስጥ ያስገባ ሥራ ባለፉት ዓመታት ሲከናወን ቆይቷል። ለአካባቢው ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች ተለይተው ውጤታማነታቸውም በተግባር ተረጋግጧል። በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ዋናው ትኩረት እነኚህ ተሞክረው ውጤታማ የሆኑ የአካባቢውን ችግር በዘላቂ ሊቀረፍ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች እንዲስፋፉ በማድረግ የሚከተሉት ተግባርት  በሰፊው እንዲከናወኑ ይደረጋል።*

*በርጥበት አጠር አካባቢዎች የሚለሙ ተፋሰሶች ከሚያስገኙት ውጤት አንዱ የሚሆነው የከርሰ ምድርና ገፀ-ምድር ውሃን ማበልፀግ ነው። በመሆኑም የታችኛው የተፋሰሱ ክፍል ከውጤቱ የመስኖና የደጋፊ መስኖ ልማት በማካሄዱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል። ይህን በመሥራት አካባቢው ያለበትን የርጥበት እጥረት በማቃለል ምርት የማሳደግና የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ተግባር እንዲሳካ ይደረጋል።*

*በእነኚህ አካባቢዎች የሚገኘውን ዝናብ በተለያዩ ቴክኖሎጂዎች አማካኝነት በመያዝና በመጠቀም ቢያንስ አንድ ጊዜ ምርት ማምረት ይቻላል፣ ስለሆነም ሰፊ የርጥበት ዕቀባ ሥራ በመስራት ቢያንስ አንድ ጊዜ በቂ ምርት ለማምረት እንዲቻል የሚያደርግ ሥራ ይፈፀማል። ይህን ለማሳካት በማሳ ውስጥና በማሳ ዙሪያ ውሃ የማስረጊያ ጉድጓዶች  በስፋት ይሰራሉ። የውሃ ማሰባሰቢያ ኩሬዎች ተገንብተው በመሬት ንጣፍ ፕላስቲክ /ጂኦሜምብሬን/ እንደሸፈኑ በማድረግ በሚታረስ መሬት ላይ ታይሬጂንግ በመስራት የውሃና የርጥበት ማቀብ ሥራዎችን በመስራትና ለሰብሉ ተመጣጣኝ ውሃ እንዲያገኝ በማመቻቸት በቂ ምርት እንዲመረት ይደረጋል። ከዚህ በተጨማሪ የጐርፍ ውሃ በመቀልበስና ወደማሳ በማስገባት በቂ ርጥበት እንዲኖርና ሰብሉ ምርታማ እንዲሆን ሰፊ ሥራ ይሰራል።*

**የእንስሳት ሀብትና መኖ ልማት**

በቂ ዕርጥበት ባላቸው አካባቢዎች የእንስሳት ሀብት ልማት ሥራም በማስፋት ስትራቴጂው ማዕቀፍ እንዲፈፀም ይደረጋል። ትኩረቱም የእንስሳት ማድለብና የወተት ሀብት ልማት ቴክኖሎጂ ማስፋፋት ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ የማር ምርት ቴክኖሎጂና የዶሮ ሀብት ልማት ቴክኖሎጂ ማስፋት ሥራም ይከናወናል። ለዚህ ስኬት በዝርያ ማሻሻል፣ በመኖ ልማትና እንስሳት ጤና አጠባበቅ ላይ ትኩረት ያደረገ እንቅስቃሴ ይደረጋል። በዝርያ ማሻሻል ረገድ የዳልጋ ከብት ማዳቀል ሥራን የማስፋት ሲሆን ይህንንም በሰው ሰራሽ ማዳቀል ዘዴ ላይ በማተኮር ማከናወን፣ የአካባቢ የተሻሉ ዝርያዎችን መርጦ የማሰራጨት ሥራ በስፋት እንዲካሄድ ማድረግ ትኩረት ይሰጠዋል። የተሻሻለውም ሆነ ነባሩ ዝርያ የተሻለ ምርታማ የሚሆነው በቂና የተመጣጠነ መኖ ሲያገኝ ስለሆነ የመኖ ልማት በጓሮ ዙሪያ፣ የግጦሽ መሬት በማሻሻልና ከደን ልማት ጋር የቅንጠባና አጭዶ ለመመገብ የሚውሉ የመኖ እጽዋት ለማልማት ትኩረት ይሰጣል።

ከመኖ ልማት አኳያ ሌላው ትኩረት የሚሰጠው አርሶ አደሩን በማሳመንና ክህሎቱን በማሳደግ ልቅ ግጧሽን ደረጃ በደረጃ የማስቀረት፣ ይህንንም የግጦሽ መሬትን ከማሻሻል ሥራ ጋር በማያያዝ ማከናወን ይሆናል። የእንስሳት ጤና አገልግሎትን በሚመለከት መከላከል ላይ ትኩረት በማድረግ በሽታ ከመከሰቱ በፊት ክትባት በስፋት የመስጠት፣ ለክትባት ክምችት ተጨማሪ አቅም የመፍጠር፣ የህምና አገልግሎቱን የሰው ሀይል በበቂ በማሰልጠን፣ ተቋማቱን በማስፋፋትና አገልግሎቱ በተንቀሳቃሽ ጭምር አጠናክሮ የማሰቀጠል ሥራ ይከናወናል።

በርጥበት አጠር አካባቢዎች የአነስተኛ እንስሳት ሀብት ልማት ከተፋሰስ ልማት ጋር ተሳስሮ በስፋት የሚሰራ ይሆናል። ከዚህ አኳያ የበግና ፍየል ሃብት ልማት በነኚህ አካባቢዎች ልዩ ትኩረት አገኝቶ የሚፈፀም ይሆናል። ለእንስሳቱ የመኖ ልማት ከተፋሰስ ልማት ጋር ተያይዞ የሚሰራ ሲሆን የተሻሻሉ የአገር ውስጥ ዝርያዎችን በመምረጥና ከውጭ ገብተው እንዲለሙ የተደረጉ ዝርያዎችን አባዝቶ በማሰራጨት የበግና ፍየል ምርታማነት እንዲያድግ ይደረጋል። በተመሳሳይ የእንስሳቱን ጤንነት ለመጠበቅ ሰፊ የክትባት አገልግሎት ይሰጣል፣ እንደሚጌንጅ ያሉ የውጭ ጥገኛ በሽታዎች ቁጥጥርም ይደረጋል። ለንቦች ቀሰም አገልግሎት የሚውሉ እጽዋት ልማት በተፋሰስ ልማት ሥራው ተካቶ የሚሰራ በመሆኑ ከዚሁ ጋር በማቆራኘት የንብ ሀብት ልማት ሥራ በስፋት ይካሄዳል። ዘመናዊ ቀፎዎችን በበቂ መጠን በማቅረብ በቤተሰብ ደረጃ፣ በተደራጁ ወጣቶችና ሴቶች አማካኝነት የማር ምርት በላቀ ደረጃ የማሳደግ ሥራ ይከናወናል። ከዚህ በተጨማሪ የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች ለአርሶ አደሩ እንዲቀርብና የዶሮ ፓኬጅ\ እንዲስፋፋ ብሎም የአርሶ አደሮች ገቢ እንዲያድግ ይደረጋል።

**የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና አያያዝ**

በቂ ርጥበት ባላቸው አካባቢዎች የግብርና ዕድገት ዘላቂነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ተግባራት ተጠናክረውና በማስፋት ስትራቴጂው ማዕቀፍ ይፈፀማሉ። በቀጣይ አምስት ዓመታት በዚህ አካባቢ የፊዚካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ የሚያስፈልጋቸው ቦታዎች በሙሉ የተሟላ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች በህብረተሰቡ የነቃና የተደራጀ ተሳትፎ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲሰራባቸው ይደረጋል። የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩይበልጥ ተጠናክሮ እንዲሰራ ይደረጋል።

በርጥበት አጠር አካባቢዎች የተፋሰሶች ልማት ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን፣ ተሰማሚ ፊዜካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ የተሰራባቸውና በስነ-ህይወታዊ የተፈጥሮ ሀብት ሥራ እንዲጠናከሩ የተደረጉ ተፋሰሶች በሚገርም ፍጥነት ያገገሙበት፣ ከተፋሰሱ ሥር ውሃ መመንጨት የጀመረበትና ለመስኖ ጥቅም ላይ ማዋል የተቻለባቸው ምርጥ ልምዶች በርጥበት አጠር አካባቢ ባሉ ሁሉም ተፋሰሶች እንዲሰፋፉ ይደረጋል።

ስለሆነም ፊዚካላዊ የተፈጥሮ ሀብት ሥራ የሚያስፈልጋቸው ተፋሰሶች ተለይተውና ዝርዝር ዕቅድ ተዘጋጅቶላቸው በቀጣይ ሦስት ዓመታት ሙሉ በሙሉ የፊዚካላዊ የተፈጥሮ ሀብት ሥራ እንዲሰራባቸው ይደረጋል። ፊዚካላዊ ሥራውን ለማጠናከር ፈርጀ ብዙ ጥቅም ያላቸው ስነ-ህይወታዊ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራዎችም ይከናወናሉ።

የተፋሰስ ልማት ስራው በየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የሚፈፀም ይሆናል። ከሰው እና እንስሳት ንክኪ በመጠበቅ በቀላሉ ሊለሙና ሊጠበቁ የሚችሉ ቦታዎች ተለይተው ህብረተሰቡን በማሳተፍ እንዲጠበቁና ጥቅም ላይ እንዲውሉ በሚያደርግ አግባብ ይፈፀማል። እንደተዳፋትነቱ መጠን፣ የአፈር ዓይነት፣ የሥነ-ምህዳር ሁኔታ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህ ረገድ የተለያዩና ተስማሚ የድንጋይና አፈር እርከኖች፣ የውሃ ማስረጊያ ስትራክቸሮች፣ የቦረቦር ማዳን ቴክኖሎጂዎች፣ ክትሮችና የመሳሰሉት ጥቅም ላይ ይውላሉ። የዳበሩ የርጥበት አጠባበቅ ቴክኖሎጂዎች ጥልቅ ትሬንች፣ ኩሬ፣ ክትር፣ ወዘተ/ ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲሰሩም ይደረጋል። ከዚህ በተጨማሪ ወደ ማሳ የጐርፍ ውሃ ለማስገባት የሚያስችሉ የጐርፍ መቀልበሻ ቦዮች እንዲሰሩ ይደረጋል።

ከላይ ተዘረዘሩት የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራዎች አረንጓዴ ነገር ለማየት ብቻ ተብለው የሚሰሩ ሳይሆኑ ይልቁንም ለህብረተሰቡ ተጨባጭ ጥቅም እንዲያስገኙ ታስበው የሚፈፀሙ ናቸው። ስለሆነም በተፋሰሱ ውስጥ የሚለሙ እጽዋት ለእንስሳት መኖ የሚውሉ የቅንጠባና ታጭደው ሊመገቡ የሚችሉ እንዲሆኑ ይደረጋል። የተራቆቱ መሬቶች መልሰው እንዲያገግሙ በሚደረገው ጥረት የባዮፊውል ተክሎች እንዲለሙ፣ የተፋሰስ ልማቱ ከፍራፍሬ ልማት ጋር እንዲተሳሰርም ይደረጋል። ከዚህ በተጨማሪ የማገዶና የጣውላ ፍላጐትን ለማሟላት በሚያስችል አግባብ የሚፈፀም ይሆናል።

የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ተግባር በዋነኛነት በጉልበት የሚሰራ በመሆኑ የህዝቡን ጉልበት በስፋትና በውጤታማነት መጠቀም በሚያስችል አግባብ እንዲፈፀም ይደረጋል። ህዝቡ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችለውንና የሚፈልገውን በሙሉ ፈቃደኝነት እንዲያበረክት በማድረግ እንዲሰራ ይደረጋል። በዚህ አካባቢ የሴፍቴኔት ፕሮግራም የጋራ ጥሪት ለመፍጠር ታቅዶ የሚፈፀም በመሆኑ ፕሮግራሙ የተነደፉ የተፋሰስ ልማት ስራዎችን በላቀ ውጤታማነት መፈፀም በሚያስችል አግባብ ይተገበራል።

የሚለማውና የሚጠበቀው የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትና ተጠቃሚ በዋነኛነት ህዝቡ ስለሆነ በየአካባቢ የሚለማው ተፋሰስ ቀዳሚ ባለቤትና ተጠቃሚ ህብረተሰቡ እንዲሆን ይደረጋል። በተለይም ወጣቶችና ሴቶች በተደራጀ አኳኋን ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ በልዩ ትኩረት ይፈፀማል።

**የግብርና ምርምርና የኤክስቴንሽን**

ምርጥ የቴክኖሎጂና የተሻሻሉ አሰራር ልምዶች እንዲስፋፉ የምርምር ኤክስቴንሽንና አርሶ አደር ትስስር አስፈላጊ በመሆኑ የቴክኖሎጂ ማላመድ፣ ብዜት፣ ስርጭትና አጠቃቀም ስርዓቱ የበለጠ እንዲጠናከር ይደረጋል። በየደረጃው ያሉ የምርምር ኤክስቴንሽንና አርሶ አደር ካውንስሎች የቴክኖሎጂ ችግር የሚለይባቸው ለመፍትሄውም በጋራ የሚሰራባቸውና የማስፋት ስትራቴጂውን ውጤታማነት በሚደግፍ አግባብ እንዲጠናከሩ ይደረጋል። ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን ከማስፋፋት ጐን ለጐን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የማውጣት፣የመሞከርና ውጤታማነታቸው ሲረጋገጥ በስፋት ወደ ምርት እንዲገቡ የማድረግ ሥራም ትኩረት ተሰቶት የሚሰራ ይሆናል። በዚህ ረገድ የግብርና ምርምር ሥራችን በሰብል፣ በእንስሳት፣ በተፈጥሮ ሀብት ልማትና በእርሻ ሜካናይዜሽን ላይ የሚያተኮር ሆኖ ቴክኖሎጂውን ለማቅረብ የሚከተለው ስትራቴጂ ያለቀላቸው ቴክኖሎጂዎች ከውጭ በዋነኛነት አስገብቶ በማላመድና በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በአገር ውስጥ ምርምር በማፍለቅ ይሆናል። ቴክኖሎጂዎችን ለማቅረብ የሚወሰደውን ጊዜ ለማሳጠር መስኖና ዘመናዊ ዘዴዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

የአካባቢን ሥነምህዳር መሠረት ባደረገ ስፔሻላይዜሽን ላይ በመመስረት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ምርቶች ምርታማነትና ጥራት እንዲያድግ ለአርሶ አደሩ በኤክስቴንሽን ስርዓቱና አደረጃጀቱ አማካኝነት በቂ ድጋፍ ይሰጣል። በዚህ ረገድ የቡና፣ ሰሊጥ፣ ጥጥ፣ ቅመማቅመም፣ አትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ላይ የበለጠ ትኩረት ይደረጋል። ለሰብሎቹ የተዘጋጁ ፓኬጆችና የተቀመሩ ምርጥ ልምዶች ተሟልተው እንዲፈፀሙና እንዲስፋፉ በማድረግ የሰብሎቹ ምርታማነትና ጥራት እንዲያድግና አርሶ አደሩም ከእነኝህና መሰል ምርቶች የሚያገኘው ገቢ እንዲያድግ ድጋፍ ይሰጣል።

**የምግብ ዋስትና ኘሮግራም**

የርጥበት አጠር አካባቢዎች የምግብ ዋስትና መታጣት ችግር የሚስተዋልባቸው በመሆኑ በተነፃጻሪ በአጭር ጊዜ ከዚህ ችግር እንዲላቀቁ ለማድረግ የሚያስችል ሥራ ይሰራል። በዚህ ረገድ ባለፉት ዓመታት ተቀርጾ ሲተገበር የቆየውና ውጤት ማምጣት የጀመረው የምግብ ዋስትና ኘሮግራም ይበልጥ በተጠናከረና እስካሁን የተገኙ ልምዶችን ቀምሮ በማስፋፋት ላይ ባተኮረ መልኩ እንዲፈፀም ይደረጋል። በኘሮግራሙ ሁሉን አቀፍና እርስ በእርሳቸው የሚመጋገብ ይዘት ያላቸው መሠረታዊ ክፍሎች አሉ። እነርሱም የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ፣ የሴፍቲኔት ኘሮግራም፣ የሰፈራ ኘሮግራምና ከግብርና ውጭ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ናቸው።

በዚህ መሠረት አሁን ያለውን የምግብ ዋስትና ችግር ያለበት ህብረተሰብ በቀጣይ ሶሰት አመት ውስጥ እንዲመረቁና ሙሉ በሙሉ የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ

የሴፍቲኔት ኘሮግራም ከቤተሰብ ጥሪት ግንባታ ስራ ጋር ተመጋግቦ የሚፈፀም ሲሆን የምግብ ዋስትና መታጣት ችግር መንስኤ የሆነው የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ችግር ለመፍታት በሚያስችል አግባብ የሚፈፀምና የህብረተሰብ ጥሪት (Community Asset) ለመገንባት የሚያስችል በመሆኑ ያለፉ የኘሮግራሙ ልምዶች ተቀምረው በመጭው አምስት ዓመታት ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚፈፀም ይሆናል፡፡ ኘሮግራሙ በሚካሄድባቸው ወረዳዎች የሚገኙ የኘሮግራሙ ተጠቃሚዎች በኘሮግራሙ የመጭው ሶስት ዓመት ዘመን ውስጥ ከኘሮግራሙ እንዲመረቁ ይደረጋል፡፡

ከሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች መካከል በቤተሰብ ጥረት ግንባታ የሚሳተፉትን በመለየት የቢዝነስ ኘላን ዝግጅት፣ ሥልጠና፣ ቴክኖሎጂ የማቅረብ፣ ብድርና የኤክስቴንሽን ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያበቃ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ በዚህ የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ የምግብ ዋስትና ስትራቴጂውን መሠረት ያደረጉ የፖኬጅ ጥንቅሮች ማለትም ለዝናብ አጠር አካባቢዎች ተስማሚ የሆኑ፣ በውሃ ማሰባሰብ፣ በአነስተኛ ርጥበትና መሬት ውጤታማ የሚደረጉ ሥራዎችን በመተግበር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፖኬጆች ልዩ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ መርሀ-ግብርና ዘመን በመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት በኘሮግራሙ የታቀፉ አርሶ አደሮች የምግብ ዋስትናቸውን አረጋግጠው ከኘሮግራሙ እንዲመረቁ ይደረጋል፡፡ ሌላኛውና በተፋጠነ ሁኔታ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ተነድፎ ሲተገበር የቆየው የምግብ ዋስትና ኘሮግራም አካል የሰፈራ ኘሮግራም ነው፡፡ የምግብ ዋስትና መታጣት ችግር ያለባቸው ቤተሰቦች በበቂ ዝግጅት ላይ በመመስረትና የሰፋሪዎቹን ሙሉ ፈቃደኝነት ባረጋገጠ አኳኋን ለም ወደሆኑ በክልል ውስጥ ወደሚገኙ አካባቢዎችና ሰፊ ጉልበት በሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ዙሪያ እንዲሰፍሩና ምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መሬት ጥበት ያለባቸውና መሬት የሌላቸው በተለይም ወጣቶችና ሴቶች አዋጭ በሆነ ከግብርና ውጭ ባሉ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች እንዲሳተፉ ሥራዎቹን በመለየትና ፖኬጅ በማዘጋጀት፣ ለሥራው የሚያስፈልግ ክህሎትና የንግድ ሥራ አመራር ሥልጠናዎች በመስጠት ተደራጅተው የብድር አገልግሎትና የገበያ አማራጭ ተመቻችቶላቸው የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ አስፈላጊው ድጋፍ ይሰጣቸዋል፡፡

በርጥበት አጠር አካባቢዎች ምርጥ ልምዶቹን በማስፋትና የምግብ  ምስትና ኘሮግራምን አሟልቶ በመፈፀም በቀጣይ አምስት አመታት ለምግብ እጥረት ተጋላጭነታችን ማስወገድ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ  ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት ከማከናወን በተጓዳኝ ለአደጋ ክስተት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠትና ለምላሽ የዝግጁነት አቅም መገንባት፣ ምላሽን በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን በማድረግ ለአደጋ ወቅታዊ ምላሽ መስጠት እንዲሁም የግብርናውን ብሎም አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እድገትን መደገፍ በአላማ ደረጃ ተወስደው የሚተገበሩ ይሆናል፡፡ የዝግጁነት አቅማችን በመገንባት ረገድ የመጠባበቂያ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ክምችቶችን መጠን የማሳደግ፣ የማከማቸት አቅማችንም ከሚያድገው ክምችት አኳያ የማሳደግ ይህንኑንም ስትራቴጂያዊ በሆኑ ቦታዎች የመገንባት ሥራን ባካተተ መልኩ የመጠባበቂያ አቅም ግንባታ ሁሉ አቀፍ አገልግሎት ሊሰጥ በሚችል አግባብ ይፈፀማል፡፡

***የግብርና ግብይት***

*አርሶ አደሩ ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ የአመራረት ሂደት ተላቆ በገበያ በተለይም በዓለም ገበያ እንደሚመራ የአመራረትና የአኗኗር ዘይቤ እንዲቀየር ለማድረግ የተጀመረው ጉዞ በሚቀጥለው አምስት የዕቅድ ዓመትም ተጠናክሮ ይቀጥላል። ከዚህ አንጻር ከተያዙት አቅጣጫዎች አንዱ አርሶ አደሩ መለስተኛ ዋጋ ያላቸው ምርቶችን ከማምረት ደረጃ በደረጃ የተሻለ ዋጋ ወዳላቸው ምርቶች ወደ ማምረት እንዲሸጋገር በማድረግ ከምርቱ የሚያገኘው ገቢ እንዲያድግ ማድረግ ነው። ይህንንም ለማሳካት የግብይት ሥርዓቱን በተዋናዮችና በባለድርሻ አካላት የነቃና የተደራጀ ተሳትፎ ከምርት እስከ ውጭ ንግድ ጫፍ ወጥና በተሟላ አኳኋን በመገንባት ለግብርና ምርት ግብይት አመቺ ሁኔታ የመፍጠር ሥራ በልዩ ትኩረት ይፈፀማል።*

*የግብርና ግብይት ሥርዓቱን ከማሻሻል አንጻር በቀጣዩ አምስት ዓመታት የሚከተሉት ዋና ዋና ሥራዎች ይከናወናሉ። በየደረጃው እስካሁን የተገኙ ምርጥ ልምዶች ተቀምረው እንዲስፋፉ ይደረጋል። የግብርና ምርቶችን ጥራት ቁጥጥርና የግብይት ሥርዓቱን ዝርጋታ የማጠናቀቅ ከክልል እስከ ቀበሌ ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት የገበያውን ስልጠትና ውጤታማነት ማረጋገጥ፣ የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላትን ማቋቋምና ማጠናከር የግብይት መሠረተ ልማቶችን የማሟላት፣ የገበያ ፕሮሞሽን ሥራዎችን በማጠናከር አዲስ ገበያዎችን ሰብሮ የመግባትና በነባሮችም ያለንን ድርሻ የማሳደግ ሥራዎችን ማከናወን፣የግብርና ግብይት መረጃ ስርዓትን በመዘርጋት መረጃ በወቅቱ ለተጠቃሚዎች ማድረስ፣ በግብርና ግብይት መስክ ተሣታፊ የሆኑ አካላትን አቅም የመገንባት እንዲሁም የግብርና ምርቶች ጥራትና ደረጃዎች የማረጋገጥና የማውጣት ሥራዎች ይከናወናሉ።*

*በገጠር የግብይት ስርዓት ሲታሰብ ያለ አርሶ አደሩ የህብረት ሥራ ማህበራት ሰፊ ተሳትፎ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ስለማይቻል የህብረት ሥራ ማህበራት በስፋት እንዲደራጁና ያሉትም እንዲጠናከሩ በማድረግ የግብይት ተሳትፏቸው እንዲያድግ የማድረግ ስራ ይሰራል። ለዚህም የህብረት ስራ ማህበራት ሁለገብ አቅም በአባላት ተሳትፎና በመንግሥት ድጋፍ እንዲጠናከር ይደረጋል።*

***አቅም ግንባታ***

*በአነስተኛ አርሶ አደር ደረጃ ምርትና ምርታማነትን ትርጉም ባለው ደረጃ ለማሣደግ በማስፋት ስትራቴጂ ማዕቀፍ የሚከናወኑ የተሻሻሉ የግብርና አሠራሮችን የመተግበር/ በሰብል ምርትና ምርታማነት፤ በእንስሳት ሃብት፣ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና አያያዝ/፣ የቴክኖሎጂ ብዜት፣ በግብርና ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት ተግባራትና የመሳሰሉትን ዝርዝር ተግባራት ከላይ ከፍ ብሎ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። እነኝህን ዝርዝር ተግባራት ውጤታማ በሆነ መንገድ በመፈፀም ረገድ የፈጻሚዎችን ብቃት መገንባት ወሣኝ ጉዳይ ነው። በመሆኑም አርሶ አደሩን የሚደግፈውን የግብርና መዋቅር በሰው ሃይል፣ በአሠራርና በአደረጃጀት በየደረጃው እንዲጠናከር ይደረጋል። አርሶ አደሩን በቅርበት በሙያ የሚደግፉ የልማት ጣቢያ ሠራተኞች ክህሎት የበለጠ እንዲገነባ የሥራ ተነሣሽነታቸው እንዲጐለብት ይደረጋል። በዚህ ረገድ ስርዓት ተበጅቶለት በአጫጭርና በረጅም ጊዜ ስልጠና አቅማቸው እንዲገነባ ይደረጋል።*

*የልማት ጣቢያ ሠራተኞችን ብቃት ከማሣደግ ጐን ለጐን በሚጎደሉና ባልተሟሉባቸው ቦታዎች በግብርና ማሰልጠኛ ኮሌጆች በግብርና ልማት፣ በእንስሳት ጤናና በህብረት ሥራ ዘርፎች የማሰልጠን ሥራ ይሰራል። በተመሳሳይ የአርሶ አደሩን የሥራ ተነሳሽነት እንዲጐለብት የግብርና ቴክኖሎጂዎችንና የተሻሻሉ የአሠራር ዘዴዎችን የመጠቀም ክህሎቱ በተግባር በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማትና በምርጥ አርሶ አደሩ ተግባር ዙሪያ እንዲያድግ ይደረጋል። የምርጥ አርሶ አደሩ ምርጥ ልምዶች ወደ ሁሉም አርሶ አደሮች በቀላሉ ሊተላለፍ የሚችልባቸው የአርሶ አደሩ የኤክስቴንሽን አደረጃጀቶች ማለትም የልማት ቡድኖች በሁሉም አካባቢዎች እንዲጠናከሩና ወሳኝ የምርጥ ልምድ ማስተላለፊያ አደረጃጀቶች እንዲሆኑ ይደረጋል። ለአርሶ አደሩ ክህሎት ለማስጨበጥ ከሚያግዙ ተቋማት አንዱ የሆኑት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት እንዲስፋፋ ያሉትም በውስጥ ቁሳቁስና በሰርቶ ማሳያ የበለጠ እንዲደራጁ ይደረጋል።*

***የግል ባለሀብት የግብርና ልማት***

*በግብርናና በገጠር ልማት ፖሊሲያችን የግል ባለሃብቱ በግብርና ልማት ስለሚሳተፍበት ግልጽ አቅጣጫ ተቀምጧል። ይህንኑ ለመፈጸም በተደረገ ጥረት በአበባ ዘርፍ ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል። ሰፋፊ ለእርሻ የሚውል መሬት ባለባቸው የሀገራችን ክፍሎች የመሠረተ ልማት ሳይስፋፋ በመቆየቱ የግል ባለሀብቱ የግብርና ኢንቨስትመንት ተሳትፎ ዝቅተኛ ሆኖ ቆይቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመሠረተ ልማት በመስፋፋቱ፣ ለኢንዱስትሪ የግብርና ጥሬ ዕቃ ፍላጎት እያደገ በመምጣቱና በአገር ውስጥ የግብርና ምርቶች ገበያ እየሰፋ በመምጣቱና በግብርና ለሚካሄድ ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ ይገኛል። ከዚህም በመነሳት የኢንቨስትመንት ፍላጎት መጨመርና ወደ ተግባር የመግባት እንቅስቃሴዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መሄድ ይስተዋላል። ይህ ሁኔታ በዚሁ መልክ እንደሚቀጥል ስለሚታሰብ በግብርና ዘርፍ የግሉ ኢንቨስትመንት ተሳትፎና የግሉ ዘርፍ በግብርና ልማት የሚኖረው ድርሻ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ በቀጣይ አምስት ዓመት መሠረታዊ አቅጣጫ ይሆናል።*

*በግሉ ዘርፍ በግብርና ልማት የሚካሄደው ኢንቨስትመንት ሰፋፊ መሬትና ውስን ጉልበት ባለባቸው አካባቢዎችና ለከተሞች ቅርብ በሆኑ በውስን መሬትና ሰፊ ጉልበት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን የግብርና ምርቶች ማምረት በሚቻልባቸው አካባቢዎች እንደየባህሪያቸው የሚካሄዱ ይሆናል።*

## *4.2. የአካባቢ ጥበቃና መሬት አስተዳደርና መሬት አጠቃቀም*

### *የትኩረት አቅጣጫዎች*

- *የመሬት አስተዳደርና የመሬት አጠቃቀም በኩል የመጀመሪያ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርን ማጠናቀቅ፣ ሁሉንም የመሬት ይዞታ የካደስተራያል ሰርቬይ ስራ ማከናውን፣ የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ መስጠት፣ የመሬት አጠቃቀም እቅደ ማዘጋጀትና ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣ የመሬት መረጃን ኮምፒተራይዝድ ማድረግ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት ናቸው፣*

- የአካባቢ ጥበቃና ዘላቂነትን ማረጋገጥ ረገድ በአካባቢ ጉዳይ ላይ የግንዛቤ ለዉጥ መፍጠር ሥራ፣ የአካባቢ ብክለትና ብክነት ላይ ክትትል፤ ምርመራና ቁጥጥር ማድረግ፣ አካባቢዊ አደጋዎችንና ጉዳቶችን በጥናት መለየት፣
- ከተቋሙ የማስፈፀም አቅም ግንባታ አኳያ የሰዉ ኃይል ልማት፣ አደረጃጀት፣ አሰራርና ቴክኖሎጅ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው።

***ዓላማ***

*የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በመስጠት፣ አስተማማኝ የመሬት መረጃ በማደራጀት፣ እያንዳንዱ መሬት የላቀ ውጤት ሊያበረክት በሚችልበት ሁኔታ የመሬት አጠቃቀምን ተግባራዊ በማድረግ የመሬት ባለቤትነት ስሜትን በማዳበርና ልማትና አካባቢ ተጣጥመው እንዲሄዱ በማድረግ የአካባቢ ዘላቂነትን ማረጋገጥ፣*

***ግቦች***

- *የመጀመሪያ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ከ*94.7% *ወደ* 100% *በማድረስ አርሶ አደሩ በይዞታው ላይ የባለቤትነት ስሜትን እንዲያዳብር ማስቻል፤*
- *የመሬት መረጃን ወደ ኮምፒወተር በማስገባት አሁን ካለበት* 753,800 *ይዞታዎች ወደ* 3.5 *ሚሊዮን በማድረስ፤ የመረጃ አገልግሎቱን ፈጣንና አስተማማኝ ማድረግ፤*
- *የካዳስትራል ሰርቬይ* 100% *በማካሄድና ካርታ በመስራት፣ የይዞታው ትክክለኛ መጠን በማወቅ የድንበር ውዝግቦችን በመቀነስ መልካም አስተዳደርን በገጠር ማስፈን፣*
- *የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር* 100% *በማድረስ አርሶአደሩ በይዞታው ላይ የባለቤትነት ስሜትን እንዲዳብር ማስቻል፤*
- *የመሬት ሀብት መረጃ ላይ በመመስረት የመሬት አጠቃቀም ጥናት ሽፋንን* 30% *ማድረስ፤*
- እስከ 2002 ደረስ ካለው ተጠንቶ በባንክ ካለው 425,182.4 ሄ/ር ለገጠር ግብርና ኢንቨስትመንት የሚውል መሬት በተጨማሪ 50,000 ሄ/ር መሬት በጥናት በመለየትና ለባለሀብቶች በማስረከብ በገጠር ግብርና ኢንቨስትመንት ለኢኮኖሚው እድገት የድርሻውን እንዲበረክት ማስቻል፤
- በግብርና ኢንቨስትመንት ለተሰማሩ 1272 ነባር ባለሀብቶች ውል ማደስ፣ 590 ባለሀብቶች አዲስ ውል መያዝና የባለሀብቶችን ዝርዝር መረጃ ኮምፒውተራይዝድ በማድረግ፤ የግብርና ኢንቨስትመንት እንድጠናከር ማገዝ፣
- በክልሉ የሚካሄዱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቶች ዘላቂና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ለ13840 ፕሮጀክቶች (ፕሮግራሞች) የይሁንታ ፈቃድ በመስጠት፣ 24250 የይሁንታ ፈቃድ ማደስ፤8500 የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀት፤

- 10130 ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ምርመራ፤ በ4220 ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ቁጥጥር በማካሄድና 30 ብክለት የደረሰባቸዉን ቦታዎችን በመለየት የአካባቢ ብክነት፣ ብክለትንና ተጽእኖን መቀነስ፤
- የአካባቢ ትምህርት በማዘጋጀትና መረጃ በመስጠት ለ10.9 ሚሊዮንለሚሆን ነዋሪ ህዝብ በድግግሞሽ ግንዛቤ በመፍጠር የአመለካከት ለዉጥ ማምጣት፤
- በአካባቢ ጥበቃና በመሬት አስተዳደር ፖሊሲዎች ዙሪያ የተለያዩ የህዝብ ግንኙነት ዘዴዎችን በመጠቀም 25 ሚሊዮን ህዝብ በቂ መረጃ እንዲያገኝን ግንዛቤው እንዲሻሻል ማድረግ።

### የአፈጻጸም ስልቶች

ከላይ የተዘረዘሩ ዓላማና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የአፈጻጸም ስልቶች ተነድፈዋል።

- በBPR ጥናት መሠረት በየደረጃው ያለውን አደረጃጀት በሰው ኃይል ከማሟላትና የአቅም ግንባታ ሥራን ከመሥራት ጎን ለጎን በወረዳዎች የመስክ ክትትል፣ ግምገማና የሙያ እገዛ እንዲኖርና የስራ ቅደም ተከተሎች፤ መመሪያዎችና የሥራ ማኑዋሎች በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ፣
- በክልልና በወረዳ ያሉ የውሣኔ ሰጭ አካላትን፣ ባለሙያዎችን፣ አርሶ አደሩን፣ሌሎች አጋር አካላትን በአካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተግባራት ግልፀኝነት እንዲኖራቸው ለማድረግና ቅንጅትን ለመፍጠር እንቅስቃሴውን ማጠናከር፣
- ግንዛቤን ለማሳደግ ከሚካሄዱት ስልጠናዎች፣አውደ ጥናቶችና የልምድ ልውውጥ በማካሄድ የመረጃ ልውውጥና ፈጣን ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ፣ የበራሪ ጽሁፎችን፣ ብሮሽሮችንና የመሳሰሉ ማቴሪያሎችን የማዘጋጀትና የማሠራጨት ሥራ ማከናወን፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን በስፋት ስራ ላይ ማዋል፤
- ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር ግንኙነትን በማጠናከርና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የበጀት ችግርን ማስወገድ፣
- የተጠኑ ጥናቶችን በማሰባሰብና አዳዲስ ጥናቶች በማካሄድ ያለውን የመረጃ ክፍተት ማስወገድና የመረጃ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ፍላጎት ማሟላት፣
- አሠራርን በማሻሻልና የመረጃ እጥረትን በማቃለል ለባለሃብቶችና አርሶ አደሮች የተሟላ አገልግሎት መስጠት፣
- ሥርአተ- ፆታን በሁሉም የአ/ጥ/መ/አስ/አጠ/ ስራዎች እነዲካተት ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግና ስልጠና መስጠት
- ከህብረተሰቡና ከአጋር መ/ቤቶች ጋር የጋራ ግንዛቤ በመፍጠርና በመንቀሳቀስ፣ የተፈጥሮ ሀብትን የመጠቀምና የመጠበቅ መብትና ግዴታዎችን እንዲረዳ ብሎም ተግባራዊ እንዲያደርግ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ከፍ እንዲል ማድረግ፣
- የህዝቡን ተሳትፎ ይበልጥ እንዲጎለብት ለማድረግ፤ ለቀበሌ መሬት አስተዳደር ኮሚቴና ለአገር ሽማግሌዎች ስልጠና በመስጠት ተግባራቸውን በብቃት እንዲወጡ ይደረጋል፤

- *ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ጠንካራ መዋቅራዊና የሪፖርት ግንኙነት ስርዓት እንዲኖር ማድረግ፤*
- *የመስክ ላይ እገዛዎች በየደረጃው በማያቋርጥ ሁኔታ በማካሄድና ግብረ-መልስ በመስጠት ላይ ያተኮረ ይሆናል፤*
- *በሁሉም እርከኖች፤ በየሩብ ዓመቱ እቅዱን መሰረት ያደረገ የስራ ላይ ምክክርና ግምገማ ይደረጋል፤*

## *4.3. ኢንድስትሪ ልማት*

**ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት**

*በኢንዱስትሪ መስክ ከማንኛውም ዘርፍ የፈጠነና የተሻለ ልማት በማረጋገጥ የኢንዱስትሪ ድርሻ ደረጃ በደረጃ የቀጣይ የክልሉ የልማት መሠረት የሚሆንበት፣ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት ለማቀለል የበኩሉን ድርሻ የሚወጣበት፣ ለግብርና ቀጣይ ዕድገት ከፍተኛ እስተዋጾ የሚያደርግበትና ሰፊ የስራ እድል የሚፈጠርበት መስክ ይደረጋል ፡፡ ዋነኛው የሥራ ዕድል ፈጣሪ የሚሆነው የአንስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ዘርፍ ግንባር ቀደም ትኩረት እንዲሆን በማድርግ እና ለመካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችም አስፈላጊውን ግምት በመስጠት ርብርብ ይደረጋል፡፡*

**የትኩረት አቅጣጫዎች**

*ክልላችን በአገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትስስር ውስጥ የሚኖረውን ድርሻ ከዚህ የሚገኘውን ጥቅም በማሳድግ የኢኮኖሚ ልማት የመጨረሻ ግብ በኢንዱስትሪ የበለጸገ ክልል መፍጠርን መሰረት ያደረገ ነው ፡፡ የተነደፈው የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅ በሀገሪቱና በክልሉ የኢንዱስትሪ ልማት ለማፋጠንና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ልማቱ የሚነሳባቸው መሰረታዊ መነሻዎች አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም የዘርፉ ልማት በዋነኛነት :-*

- *ጉልበትን በሰፊው ለሚጠቀሙ ፣*
- *ሰፊ ገበያ ላላቸው ፣*
- *የግብርና ምርቶችን በስፋት በግባትነት ለሚጠቀሙ ፣*
- *ኤክስፖርት መር ለሆኑ፣*
- *ገቢ ምርቶችን ለመተካት ለሚያስችሉ፣*
- *ለፈጣን የቴክኖለጂ ሽግግር ለሚያመቹ ፣*
- *የአገሪቱን የቴክኖለጂ አቅም ግምት ውስጥ ለአስገቡ ኢንዱስትሪዎች፣ ቅድሚያ ትኩረት ይሰጣል፡፡*

*በተጨማሪም የልማት ስትራቴጂው ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች መነሻ በማድረግ በዘርፉ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ የሚደርግላቸው ኢንዱስሪዎች እና ንዑስ ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው:-*

1. *የመካከለኛና ከፍተኛ የማኑፍክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣*
2. *የአነስተኛ ጥቃቅን ተቋማት ልማት፣*

3. *የኢንዱስትሪ ዞኖች ልማት፣*
4. *የኢንቨስትመንት ምልመላ፣ አገልገሎትና ድጋፍ፣*
5. *የንግድ ዘርፍ አገልግሎት ልማት ላይ ያተኩራል ፣*

***ዓላማዎች***

*ከላይ የተዘረዘሩትን መነሻዎችና የፖሊሲ አቅጣጫዎች መሰረት በማድርግ ዘርፉ በሚቀጥሉት አምስት አመታት የሚከተሉት ዋና ዋና የልማት ዓላማዎች ይኖሩታል።*

- *በክልሉ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ በማስቻል ምርትና ምርታማነትን ማሣደግ።*
- *በክልሉ ውስጥ ያለውን ጥሬ ዕቃና የሰው ጉልበት በሰፊው ለመጠቀም የሚያስችል አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች እንዲቋቋሙና ያሉትም እንዲስፋፉ ማድርግ ፣ በአጠቃላይ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ አዳዲስ ባለሃብቶችን ለማፍራት፤ የግብርናውን ልማት ለመደገፍና የስራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ በሚያስችል መንገድ የአንስተኛ ጥቃቅን ተቋሞችን ማልማት።*
- *የኢንድስትሪ ልማት ለማፋጠንና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የግል ልማትዊ ባለሃብቱን ተሣትፎ ማጎልበትና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት ፣*
- *ክፍለ ኢኮኖሚው የሥራ ዕድልን በመፍጠር ፣ ገቢ ምርቶችን በመተካት የውጭ ምንዛሪን የማዳን ፣ የውጭ ምንዛሪን በማስገኘትና በጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረውን ድርሻ በማሳደግ ደረጃ በደረጃ በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነቱን ሥፍራ እንዲይዝ ማስቻል ።*

***ግቦች***

*የንግድና ኢንዱስትሪ ዓላማዎችን ለማሳካት በመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች፣ በአንስተኛና ጥቃቅን ተቋማት፣ የግል ኢንስትመንትን በማስፋፋት፣ የልማት ድርጅቶችን እና የግሉን ዘርፍ ልማታዊንትን በማሳደግ ለቁጠባ ባህልን ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ኢንዱስትሪው በኢኮኖሚው ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲጫወትና መሰረቱን ለማጠናከር እንዲያስችል በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የሚደርስባቸው ግቦች ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል :-*

***የከፍተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ግቦች***

- *የተቋቋሙ የመካከለኛ ኢንዱስትሪ ዞኖች ብዛት አሁን ያሉት* 7 *ሲሆኑ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በተለያዩ ከተሞች የኢንዱስትሪ ዞኖች በማቋቋም በቁጥር* 35 *ማድረስ፣ እንዲሁም የተቋቋመ ከፍተኛ የኢንዱስትሪ ዞን ብዛት እሰከ አሁን ምንም ያልነበረ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በተለያዩ ከተሞች በቁጥር* 6 *ከፍተኛ የኢንዱስትሪ ዞንኖች እንዲቋቋሙ ማድርግ፣*
- *የተቋቋሙ ኢንዱስትሪዎች ብዛት (መካከለኛና ከፍተኛ) አሁን ያሉት* 43 *ሲሆኑ ተኩረት ለሚሰጣቸውና እሴት ለሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ በመስጠት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ* 200 *ማድረስ ።*
- *ከጥቃቅን ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የተሸጋገሩ በቁጥር* 44 *ሲሆኑ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ* 5,633 *ፕሮጀክቶች ከጥቃቅን ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲሸጋገሩ ማድርግ፣*

በተጨማሪም ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ የተሸጋገሩ በቁጥር 36 በቻ የነበሩ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 4,756 ማድረስ፣

- በክልሉ የተቋቋመ የአክሲዮን ኩንባንያዎች አሁን ካሉበት 152 በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ብዛታቸውን ወደ 4352 ማሳደገ፣
- የተቋቋሙ የኢንዱስትሪ ድጋፍ ማዕከላት ቁጥር ማሳደግና እንዲሁም የተቋቋመ የኢንዱስትሪ ክላስተር እስከ አሁን ያልነበረ ሲሆን ከ2003 ጀምሮ በየዓመቱ ቁጥራቸውን በመጨመር 2007 ዓ.ም መጨረሻ በቁጥር 268 ማድረስ ፣
- እስከ 2002 በጀት የተቋቋሙ የአግሮ ፕሮስሲይንግ ኢንዱስትሪዎች ቁጥር 19 ብቻ ሲሆኑ በ2007 ዓ.ም መጨረሻ በቁጥር 359 የአግሮ ፕሮስሲይንግ ኢንዱስትሪዎች እንዲኖሩ ማስቻል፣
- ማምርት ከጀመሩ ነባር ኢንዱስትሪዎች ውስጥ አሁን ያለውን 46 በመቶ የማምረት አቅማቸውን በየዓመቱ 5-10 በመቶ በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ 75% የማምረት ዕቅማቸውን ከፍ በማድርግ አሁን ያለውን 5,332 የስራ ዕድል ወደ 10,725 ማሳደግ፣
- የከልሉ የማምረቻና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎቸ የወጪ ምርትን መጠን በከፍተኛ መጠን መሳደግና በአይነትም ከ7 ወደ 25 ዓይነት ከፍ ማድረግ፣
- በክልል የሚገኙ የማምረቻና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ለክልሉ አጠቃላይ ምርት እድገት ያላቸውን ድርሻ በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ፣

**የጥቃቅንና አንስተኛ ኢንተርፕራይዝ ግቦች**

- በዕቅድ ዘመኑ በአንስተኛ ጥቃቅን ተቋማት የተጠናከረ ድጋፍ በማድረግ በዕድገት ተኮር መስኮች 208,685 አዲስ ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም ለ800 ሽህ ሰዎች/80% በቋሚና 20% በጊዜያዊ/ አዲስ የስራ ዕድል መፍጠር፣ ከዚህ ውስጥም 50% ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ነባር ኢንተርፕራይዞችን ቀጣይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ከ375,520 ነባር ኢንተርፕራይዞች ውስጥ 75%ቱን ቀጣይነታቸውን ማረጋገጥና 1.5%ቱን ወደ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሸጋገሩ በማስቻል ለ200 ሽህ ሰዎች የስራ ዕድል መፍጠር ፣
- በዕቅድ ዘመኑ አዲስ ለሚመሰረቱ ለጥቃቅን አንሰተኛ አንቀሳቃሾች/ኢንተርፕራይዞችን ብር 2 ቢሊዮን፣ ለነባር አንቀሰቀሾች ብር 1.7 ቢሊዮን የብድር አገልግሎት በድምሩ የብር 3.7 ቢሊዮን የብድር አገልግሎት ማቅረብ፣/ምንጭ:- አበዳሪ ተቋማት፣ ቤተሰብ ከመንግስት ዋስትና፣ ዕድር፣ ሀይማኖት ተቋማት፣ መያድ፣ ወዘተ
- በዕቅድ ዘመኑ በክልሉ አዲስ ለሚመሰረቱ የጥቃቅን አንሰተኛ አንቀሳቃሾች/ኢንተርፕራይዞችን የማልማት አቅማቸውን መሠረት በማድርግ 2,033.5 ሄ/ር የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ማቅረብ፣ እንዲሁም የነባር ኢንተርፕራይዞችን የማልማት አቅማቸውን መሰረት በማድርግ ለማስፋፋያ አገልግሎት 1,200 ሄ/ር የመስሪያና የመሸጫ ባታ ማቅረብ፣ በድምሩ 3,233.5 ሄ/ር መሬት

ለአዲስና ነባር ኢንተርፕራይዞች የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ማቅረብ፣ እንዲሁም በተለያዩ ከተሞች 9,120 ሼድ መገንባት፣

- ለ375,520 ለነባር ኢንተርፕራይዞች \450,000 ተጠቃሚዎች\ 208,685 አዲስ ኢንተርፕራይዞች \800,000 ተጠቃሚዎች\ በድምሩ 1,250,000 አዲስና ነባር ተጠቃሚዎች ጥራት ያለው የስራ አመራርና የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ለአንቀሳቃሾች በማቅረብ ምርትና መርታማነትን ማሳደግ፣
- ለ250,000 አዲስና ነባር ተጠቃሚዎች እሰከ ዕቅዱ ዘምን መጨረሻ ድረስ የጥሬ ዕቃ ፣ የቴክኖሎጅና የምርት እና አገልግሎት ገበያ ትስስር በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ፣
- በዕቅድ ዘመኑ ለዕድገትና ለቴክኖሎጅ ሽግግር የሚረዱ የተለያዩ የቴክኖሎጅ አቅርቦት በማድረግ 482,788 አዲስና ነባር ተጠቃሚዎች የተለያዩ የቴክኖሎጅ አቅርቦት እንዲያገኙ ማድረግ፣
- በዕቅድ ዘመኑ 237 የአንድ መዕከል አገልግሎት እንዲገነባ ማድርግ፣ የክላስተሪንግ ልማት በተመረጡ ከተሞች ማካሄድና ማስፋፋት፣
- ዕድገት ተኮር በሆኑ ፓኬጆች ላይ 20,000 በህብረት ሥራ ማህበራት፣ 72,000 በንግድ ማህበራት ማደራጀት፣
- 10 የንግድ ልማት አገልግሎት ሰጪ/BDS/ ኢንተርፕራይዞችን ማቋቋምና ለ32,487 የጥቃቅን አንስተኛ አንቀሳቀሽ ኢንተርፕራይዞች ወይም በነዚህ ውስጥ ለሚገኙ 150,000 አዲስና ነባር ተጠቃሚዎች የንግድ ልማት አገልግሎት እንዲያገኙ ማስቻል ፣

**ኢንቨስትመንት ምልመላ፣ አገልግሎትና ድጋፍ ግቦች**

በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የሀገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስትመንቶችን መሳብ፣ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድርግ ፈቃድ ከተሰጣቸው ፕሮጀክቶች መካከል ወደ ተግባር የሚሸጋገሩትን ድርሻ ማሳደግ፣ የኢንቨስትመንት ዓላማ ሲሆን ለዕቅድ ዘመኑ የሚከተሉት ግቦች ተቀምጠዋል

- የክልሉን የኢንቨስትመንት ፍሰት በአይነት በብዛት በካፒታል ለማሳደግ ለሚመለመሉና በራሳቸው ፍላጎት ተነሳስተው ኢንቨስት ለሚያደርጉ 7,500 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት ከዚህም 20% የሴቶች ድርሻ እንዲሆን ማድርግ፣
- በተጨባጭ ወደ ኢኮኖሚው የገባ ኢንቨስትመንት ሀብት መጠንን አሁን ከተደረሰበት 5.90 ቢሊዮን ብር ካፒታል ወደ 26.02 ቢሊዮን ብር ካፒታል ከፍ ማድርግ፣
- ወደ ተግባር የገባውን 1,017 የአገር ውስጥ ፕሮጀክት ቁጥር በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በቁጥር 4,646 ፕሮጀክቶች እንዲኖሩ ማድርግ እንዲሁም ወደ ተግባር የገባውን የውጭ ባለሃብት (ጆይንት ቬንቸርን ጨምሮ ) የፕሮጀክቱች ቁጥር አሁን ካለው 78 በክልሉ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ በሚደረጉ የተለያዩ ተግባሮች ጭምር በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በቁጥር 258 ማድረስ፣

- እስከ አሁን የተመዘገበውን 72.9 ቢሊዮን ብር ካፒታል በያዓመቱ በ20% በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 188.8 ቢሊዮን ማድርስ ከዚህም ውስጥ 10% የሴቶች ድርሻ እንዲሆን ማድርግ ፣
- ፈቃድ ከሚያወጡ 7,500 ፕሮጀክቶች ውስጥ 5% እሴት በሚጨምሩ የአግሮ ፕሮሰሲንግ /225/ ፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች /40/፣ ጨርቃ ጨርቅ/40/፣ ስኳር/10/፣ ኬሚካል /ማዳበሪያ/ /10/፣ የብረታ ብረት/10/፣ ሲሚንቶ የስሜቶ ውጤቶች /10/ እና የእርሻ መገልገያ መሳሪዎች ማምረቻ፣ ፕሮጀክቶች እንዲሆኑ በማድርግ ከነዚህ ውስጥ 10%ቱ የገጠር ኢንዱስትሪዎች እንዲሆኑ ዓልሞ መስራት ፣
- የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ለማሳደግ የተለያዩ ድጋፎችን በማድርግ እስከ 2002 በጀት ዓመት ድረስ መሬት ወስደው ወደ አፈጻጸም ያልገቡ ፕሮጀክቶችን በመደገፍ እስከ እቅድ ዘመኑ አጋማሽ 90%ቱን ወደ አፈጻጸም ማስገባት ፣ ፈቃድ ወስደው መሬት ባለማግኘታቸው ወደ ተግባር ያልገቡትን በመከታተልና በመደገፍ 20%ቱን ወደ አፈፃፀም በማስገባት 203,675 ስዎች የስራ ዕድል መፍጠር፣
- በዕቅድ ዘመኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከሚሰጣቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ 30%ቱን ወደ አፍጻጸም በማስገባት 225,000 ሰዎች የስራ ዕድል መፍጠር፣
- ፈቃድ ከሚውስዱ የኢንቨስትምንት ፕሮጀክቶች መካከል 20% በቱሪዝም ኢንቨስትመንት መስክ ሆኖ ከዚህ ውስጥ 2.5% በተመረጡ የዕድገት መስኮች እንዲሰማሩ ማድረግ ፣

**የንግድ ዘርፍ ልማት ግቦች**

- የምርትና የአገልግሎት ግብይትን በአገር ውስጥና በውጭ አገር በማጠናከር በ2002 ዓ.ም ያለውን 117,645 የንግድ ህብረተሰብ ቁጥር በየዓመቱ 15% በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 353,931 ማድርስ። ከዚህ ውስጥም 50% ግብይቱ ዘመናዊና ብቃት ያለው እንዲሆንና 40% ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድርግ፣
- የንግዱን ማህበረስብ በማህብር እንዲደራጁ በመደገፍና በማጠናከር የአባላቱን ብዛት አሁን ካለው 4.4% የነጋዴ ቁጥር በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 60% ማድርስ፣
- የሚቋቋሙ የንግድ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ቁጥር አሁን ካለበት 66 ወደ 166 ማሳደግ እና የንግድ ዘርፍ ማህበራት አባላትን ቁጥር አሁን ካለበት 562 በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 12,410 ማድረስ፣
- ፍታዊ ንግድ አሰራርን በማስፍን አምራቹን ነጋዴውንና ሸማቹን ህብርተሰብ ከምርት ልውውጥና ከአገልግሎት ንግድ ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል:-
    - ✓ አሁን ያለውን 75% ህጋዊ ንግድን በያዓመቱ 95% እነዲሆን ማድርግ፣
    - ✓ የንግድ ቁጥጥር በማድረግና ወደ ህጋዊነት በማምጣት በኩንትሮባንድ ንግድ ከክልሉ ሲወጡና ሲገቡ የሚያዙ ምርቶችን ዋጋ ግምት 50% ያህል በየዓመቱ መቀነስ ፣
- በክልሉ አሁን ያሉት 20 የውጪ ንግድ ተሳታፊዎች ቁጥር በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 100 በማድርስ ከወጭ ንግድ የሚገኘውን ገቢ መሳድግ ፣

**የማስፈፀሚያ ስትራተጂዎች**

ከላይ የተገለፁትን የልማት ዓላማዎችን ለማሳካት በቀጣዮች አምስት አመታት የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ትኩረት ይደረጋል።

**በመካከኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የማስፈፀሚያ ስትራተጂዎች**

- ፍላጎቱና ብቃቱ ያላቸውን ኢትዮጵያዊያን ባለሃብቶችን በብዛት በጥራት መፍጠር ፣
- ለኢንዱስትሪ ልማት የተመቸ ሆኔታን በመፍጠር የውጭ ባለሃብቶችን ተሣትፎ ማሳደግ፣
- የኪራይ ሰብሳቢነት አማራጮችን ደረጃ በደረጃ በመዝጋት፣ በክልሉ በተለይም የተማረው ወጣት በሥራ ፈጣሪነትና በኢንተርፕርነርሽፕ አስተሳሰብ እንዲቀረጽ በማድርግ በዘርፉ ለሚሠማሩ ተዋናያን ሁሉን አቀፍና ቀልጣፋ ድጋፍ በመስጠት በመስኩ የሚደረገው የኢንቨስትመንት መጠን ውጤታማነት ከፍተኛ እምርታ እንዲያስመዘግብ ማድርግ፣
- ለዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በበቂ መጠን ጥራት ለማቅረብ የከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ በኢንዱስትሪ ልማት የተቃኘና ይህንኑ እንዲያገለግል ማድርግ፣
- ዘመናዊ የሥራ አመራር ዘዴዎችና አስተሳሰቦች በዘርፍ እንዲስፋፉ ብሎም በራስ ጥረትና የውጭ ቴክኒካዊ ድጋፍ በመጠቀም እስካሁን የተጀመሩትን ሥራዎች በከፍተኛ መጠን ማጠናከርና ማሻሻል ።
- ዘርፉን በሰለጠነ የሰው ኃይል አቅረቦት ፣ በምርምርና በምክር የሚደገፍ ኢንስትትዮቶች እንዲፈጠሩና እንዲስፋፉ ዩኒቨርስቲዎችም በዚህ ረገድ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድርግ፣
- የውጭ ቴክኒካዊ ድጋፍና የውጭ ኢንቨስትመንት በዋነነት የሥራ አመራር ጥበብ ለውጥን የቴክኖሎጅ ሽግግርንና የሙያተኛ አቅም መፍጠርን በሚያረጋግጥ አኳኋን እንዲቃኝና በዚህ በኩል ዕሎችን ጥቅም ላይ ማዋል።
- ኢንቨስትመንት ወጪን ለመቀነስ የጋራ ኢንዱስትሪ መንደር ዞኖችን ማስፋፋትና ማቋቋም ፣
- የከተማ መሬትን ለኢንዱስትሪ ልማት በተማጣጣኝ ዋጋና ቀልጣፋና ልማታዊ በሆነ አኳኋን ለማቅረብ በኢንዱስትሪ መንደሮችና ቀጠናዎች የከተማ መሬት ባንክና ቀልጣፋ አስተዳደር እንዲኖር ማድርግ፣
- በኢንዱስትሪ ልማት መስክ ለሚሠሩ ባለሃብቶች በቂና ቀልጣፋ የባንክ ብድር አግልግሎት እንዲኖር ማድርግ በተለይ ትኩረት ለሚሰጣቸው የኤክስፖርትም ሆነ የኢንፖርት መተካት ኢንዱስትሪዎች በባንክ ብድር አቅርቦትም ሆነ ሌሎች ማትጊዎች ቅድሚያ እንዲያገኙ ማድርግ ።
- በክልሉ ውስጥ መነሻ ካፒታል ውይም እውቀቱና ዝንባሌው ያላቸውን ዜጎች እየተቀናጁና በመንግስት የተሟላ ድጋፍ እያገኙ ወደ ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ እንዲሰማሩ የተለየ የምልመላ፣ የማስተማር ሌሎች አስፍላጊ የሆኑ የድጋፍ ሥራዎች መስራት፣

- በክልሉ ልማት ላይ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ የሚታመንባቸውን የውጭ ኢንቨስተሮች በኢንዱስትሪ መስክ በተለይም ልዮ ትኩረት በሚሰጣቸው የኢንዱስትሪ መስኮች እንዲሰማሩ የተጠናከረ የውጭ ኢንቨስትመንት የመሳብ ሥራ መስራት፣
- የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን በመፍጠር ረገድም ሆነ የውጭ ኢንቨስትመንት በመሳብ ረገድ እስከ አሁን ያካበትናቸው ልምዶች ተገምግመው በውጤት ላይ ያተኮረና ወጤት ያስገኛሉ ተብለው በሚገመቱ የኢንቨስትመንት ምንጮች ላይ ያነጣጠረ ሥራ መስራት፣

**አንስተኛ ጥቃቅን ተቋሞች የማስፈፀሚያ ስትራተጂዎች**

- በአጠቃላይ ወጣቱ በተለይም የተማረው ወጣት አንስተኛና ጥቃቅን ተቋሞችን በማደረጀት የራሱን ሥራ እንዲፈጥር በሂደትም የክልሉን  የኢንዱስትሪ ልማት የሚያንቀሳቅሱ ኢንዱስትራሊስቶች እንዲፈጥር የማድርግ አስተሳሰብ እንዲኖረው ለማድርግ በትምህርት ተቋሞች በሚካሄድ ሥልጠና፣ በተለያዩ የማህበራት አደረጃጀቶች በሚካሄድ እንቅስቃሴዎና ሕብረተሰቡ ይህንኑ ጥረት እንዲደገፉ በማበረታታት መልኩ ሰፊ የአመለካከት ለውጥ ስራ ማካሄድ ፤
- የኢንትርፕርኔርሽፕ አስተሳሰብና ዕውቀት እንዲዳብርና ዘርፉ ስራ መፍጠሪያ ብቻ ሳይሆን የቴክኖሎጅ ሽግግር የዘመናዊ የሥራ አመራር ዘይቤ ማስፋፊያ ሆኖ ማድግ እንዳለበት ገንዛቤ እንዲኖር ማድርግ ፣
- ዘርፉ ከግብርና ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ጋር ተደጋግፎና ተመጋግቦ እንዲያድግ ማስችል፣
- በከተሞች የተዘረጋው የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት እንዲጠናከርና እንዲስፋፋ ከቴክኒክና ሙያ ማስለጥኛ ተቋማትና ከሌሎች የዘርፉ ደጋፊ አካላት  ጋር ቅንጅት መፍጠር የቴክኒክና ሙያ ማስለጠኛ ማዕከላት የአነስተኛና የጥቃቅን ተቋሞችን ልማት በቴክኖሎጅ ሽግግር የሚደግፍ የቴክኖሎጂ ማዕከላት ሁነው የተሟላ የቴክኖሎጂ ድጋፍ እንዲሰጡ ማስቻል፣
- የስራ አመራር ጥበብን በማሻሻል ከኤክስቴንሽን ሥርዓቱ ጋር  በመተባበር / በመቀናጀት እንዲሰሩ ማድርግ፣
- በዘርፉ የሚሰማሩ ተዋንያን የካፒታል እጥረት ችግራቸውን ለመቅረፍ የመነሻ ካፒታል በራሳቸውና በቤተሰብ ድጋፍ እንዲያጠራቅሙ ማስቻል፣ የአንስተኛ ብድር አገልግሎት በተሟላ መልኩ እንዲያገኙ  የክልሉ መንግስት ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በመቀናጀት መስራት፣ የኢንቨስትመንት ወጪን ለመቀነስ የከተማ አስተዳደሮች በቂ የመስሪያ ቦታ በመገንባት የገበያና የስራ ማዕከላትን በማደራጀት እንዲንቀሳቀሱ ማድርግ፣
- የመንግስት ግንባታዎች የፍጃታ ዕቃዎች፣ የቢሮ ዕቃዎች፣ የሆስፒታልና የትምህርት ተቋማት የምግብ አቅርቦቶች፣ የግብርና የእርሻ መሳሪያዎች በጥቃቅንና አንስተኛ ተቋማት እንዲቀርቡ በማስትባብር እንዲሁም የዘርፉ ተቋማት አደረጃጀቶች በማጠናከር የገበያ ድርሻ አቅማቸውን በማስፋትና በማጠናከር የገበያ ትስስር መፍጠር፣

- የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን የመቅዳት፣ የማካማቸት፣ የመምረጥና የማሸጋገር አቅም ለመፍጠር የሚያስቸል ሥርዓት በመዘርጋት በተለይም ከዩኒቨርሲቲዎችም ሆነ አግባብነት ካላቸው ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራት ላይ በጋራ በመስራት፣

### የማስፈፀሚያ ስትራተጂዎች

- ኢንቨስትመንት የማበረታታትና የማስፋፋት ተግባራት የሚቀናጁበትና የሚመሩበት ክልል አቀፍ ስርዓት እንዲዘጋጅ ማድርግና መትገበር ፣
- ኢንቨስተሮችና የኢንቨስትመንት አስፈጻሚ አካላት በኢንቨስትምንት ነክ ጉዳዮች ላይ የጋራ ግንዛቤ ለማዳበርና ችግሮችን ለመፍታት በየጊዜው የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን በይበልጥ ለመሳብና ለማበረታታት እንዲቻል የኢንቨስትምንት ሕጉን በየጊዜው እያዩ እንደሁኔታው ማሻሻል፣
- የክልሉን ኢንቨስትመንት ለማስተዋዎቅ የሚረዱ ወቅታዊና የተሟሉ መረጃዎችን በየጊዜው በማዘጋጀት በአገር ውስጥና በውጭ አገር በሚገኙ ኤምባሲዎቻችን በኩል ማሰራጨት፣
- በሚዘጋጁ ኢንቨስትመንት ነክ ኢግዚቢሽኖች፣ ወርክሾፖች፣ ወዘተ ላይ በመሳተፍ የክልሉን የኢንቨስትመንት ዕድሎችና ሁኔታዎች ማስተዋዎቅ፣
- የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ሰለሚገኙበት የአፈጻጸም ደረጃ እና ሰለሚያስፈልጓቸው የድጋፍ አይነቶች በመከታተልና መረጃ በመሰብሰብ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድርግ፣

## 4.4. ማዕድን

### የትኩረት አቅጣጫዎች

በክልሉ ውስጥ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ በርካታ የኢንዱስትሪ ማዕድናት፣ የከበሩ ማዕድናት፣ የኮንስትራክሽን ማዕድናት፣ የኢነርጂ ማዕድናት፣ ብረት ነግክ ማዕድናት፣ የማዕድን ውሃና የጂኦተርማል ክምችቶ እንዳሉ ጥናቶች ያሳያሉ። ይህን ሃብት በማልማት ለክልሉም ሆነ ለሀገሪቱ ሕዝቡ ጥቅም ለማዋል የተደረገው ጥረት ዝቅተኛ ነው። በመሆኑም በዚህ የዕቅድ አመታት ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት የግሉ ዘርፍ በማዕድናት ጥናትና ልማት እንዲሰማራ ለማስቻል ተገቢውን መረጃ ለተጠቃሚ የማዘጋጀትና የማቅረብ፣ ዝርዝር የምዕድን ጥናት ማካሄድ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። የማዕድን ልማት ለማስፋፋት የሥነ - ምድር ጥናቶች ገበያንና ግኝትን ማዕከል በማድረግ በተቀናጀ ሁኔታ እንዲካሄዱና ቀደም ብሎ የተደረጉ ጥናቶችን ወደ ልማት እንዲሸጋገሩ ማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። የግል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የማዕድን ፍለጋ ሥራውን እንዲፋጠን በማድረግ በሀገርና በአለም አቀፍ ደረጃ ተፈላጊነት ያላቸውን የተለያዩ ማዕድናትን በማምረት የግል ኢንቨስትመንትን ማበረታታት ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

### ዓላማዎች

የአፈር ለምነትን የሚጨምሩ ማዕድናትን በማጥናትና ክምችታቸውን መገምገም፣ ለመስኖና ለመጠጥ የሚውሉ የከርሰ ምድር ውሃ ጥራትና መጠኑን በማጥናት ለጥቅም እንዲውል ማመቻቸት፣

ለኮንስትራክሽን ዘርፍና ለኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆኑ የውጪ ምንዛሬ የሚያስገኙ የሥነ ምድር ጥሬ ዕቃዎች ፍለጋና ጥናት በማካሄድ ወደ ምርት እንዲሸጋገሩ ማድረግ፣ ከማዕድን የሚገኘውን ልዩ ልዩ ገቢ በአግባቡ በማሳባሰብ የክልሉን ገቢ ማሳደግ፣ የባህላዊ ማዕድናት ምርትና ግብይት አሰራርን በማጠናከር አምራቾችና መንግስት ተጠቃሚ ማድረግ፣

***ግቦች***

- የሥነ-ምድርና የማዕድን ሃብት ጥናት ሽፋንን አሁን ከተደረሰበት 14 % በ2007 መጨረሻ 39 % ማድርስ፣
- በማዕድን ልማት ዘርፍ ተደራጅተው በህጋዊ መንገድ የሚያመርቱ ባለሃብቶችን በ2002 ካለበት 130 በ2007 መጨረሻ 300 ማድረስ፣
- በግል ወይም በማህበር ተደራጅተው በባህላዊ መንገድ ማዕድን የሚያመርቱ አምራቾችን ተሳትፎ አሁን ከተደረሰበት 4500 ወደ 8000 ማሳደግ፣
- የማዕድን ሃብትን በአግባቡ በማልማት፣ በማጥናትና በማስተዋወቅ በ2002 በጀት አመት የተደረሰበትን ከማዕድን የሚገኝ ገቢ 2 በሚሊዮን ብር በ2007 ወደ 10 ሚሊዮን ማድረስ፣

***የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች***

- የግብርና ምርት ሊያሳድጉ የሚችሉ ማዕድናት፣ ለመስኖ እርሻ የሚውሉ የከርሰ - ምድር ውሃ ፍለጋና ጥናት እንዲሁም ለመሠረተ ልማት ማስፋፋት የሚውሉ የሥነ - ምድር መረጃ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርፆ በማካሄድ መረጃውን ለተገልጋዮች ማቅረብ፣
- በክልሉ የሚመረቱ ማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር ለውጭ ገባያ የሚያቀርቡ ባለሃብቶችን ማበረታታት፣
- በባህላዊ መንገድ የሚመረቱ የጌጣጌጥ ማዕድናት ልማትና ግብይት ህጋዊ መስመር በማስያዝ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ማገዝ፣
- የከበሩ ማዕድናት አዋጅን ተግባራዊ በማድረግ አፈጻጸሙን በቅርብ መከታተል፣
- የገበያ ትስስር መፍጠር፣ የዕቀድ አፈጻጸም ክትትል ማድረግና መልካም ተሞክሮዎችን ማስፋፋት፣
- የሴቶችን ተጠቃሚነት ባገናዘበ መልኩ የህብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀት፣
- ህገወጥ የማዕድን ምርትና ንግድ እንዲቆምና የተቀናጀና ተከታታይነት ያለው የማዕድን ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋትና ተከታታይነት ያለው ሥራ ማካሄድ፣
- የማዕድንና ኢነርጂ ሀብታችንን በሰፊው ለማልማትና ባለሃብቶችን ለመሳብ የሚችል የፕሮሞሽን ደኩመንት በማዘጋጀት የማስተዋወቅ ስራ ማከናወን

## 4.5. የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት

### 4.5.1. መንገድ

#### የትኩረት አቅጣጫዎች

በዘርፉ የተጀመረውን የዋና ዋና መንገዶች ግንባታ አጠናክሮ በመቀጠል በክረምት ከበጋ ያልተገናኙ መንገዶችን ማገናኘት፣ ለማህበረሰብ መንገዶች ትኩረት በመስጠት የገጠር ቀበሌ ማዕከላት ከዋና ዋና የክረምት ከበጋ መንገዶች ጋር እንዲገናኙ በዘርፉ ማድረግ የሚተኮርባቸው ናቸው።

#### ዓላማ

በሚቀጥሉት አምስት አመታት የመንገድ ዘርፉ የልማት ዕቅድ ዓላማ የክልሉን የመንገድ አውታር ይዞታን ማሻሻል እና የመንገድ አውታርን በማስፋፋት የመንገድ ልማት አጠቃላይ ልማትን በማፋጠን ረገድ ሚናውን እድወጣ ማስቻል።

#### ግቦች

- በሚቀጠሉት አምስት አመታት 4,000 ኪ/ሜትር አዲስ መንገድ ግንባታ በማካሄድ አሁን የተደረሰበትን የክልሉን 7617 ኪ/ሜትር የመንገድ ኔትወርክ በ2007 ወደ 11,617 ኪ/ሜትር ማሳደግና የበጋ ከክረምት መንገድ ጥግግትን አሁን ካለበት 48 ኪ/ሜትር በ 1000 ካሬ ኪ/ሜትር ወደ 74 ኪ/ሜትር በ1000 ካሬ ኪ/ሜትር ለማድረስ ታቅዷል፣
- በበጋ ከክረምት መንገድ ጋር የተገናኙ የገጠር ቀበሌ አስተዳደር ማዕከላትን በ2002 ከነበረበት 725 ወደ 3429 ማድረስ፣
- በጥሩ ሁኔታ የሚገኝ የበጋ ከከረምት የመንገድ መረብ አሁን ካለበት 65% በ2007 ወደ 75% ማድረስ፣
- የክልሉን የክረምት ከበጋ የመንገድ ጥገና አሁን ካለበት 90% በ2007 ወደ 95% ማሳደግ፣
- የዩኒቨርሳል የገጠር መንገድ በተመለከተ በሚቀጥሉት አምስት አመታት የመንገድ መሠረተ ልማት ኢንቨስትመንትን ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ዋና ከተማ ማዕከሎች በማገናኘት ላይ ያተኮረ ሥራ የሚሰራ ሲሆን 21 ሺ ኪ/ሜ መንገድ በመገንባት ሁሉም የገጠር ቀበሌዎች ደረጃውን በጠበቀና ክረምት ከበጋ በሚያገለግሉ መንገዶች ከዋና ዋና መንገዶ ጋር እንዲገናኙ ይደረጋል።
- በቅርብ ወደሚገኝ ክረምት ከበጋ የሚያስኬድ መንገድ ላይ ለመድረስ በ2002 የነበረው 10 ኪ/ሜትር ርቀት ወደ 6.7 ዝቅ ማድረግ
- በቅርብ ወደሚገኝ የክረምት ከበጋ መንገድ ለመድረስ ይፈጅ የነበረው 2 ሰዓት በ2007 ወደ 1:34 ዝቅ ማድረግ።

#### የማስፈጸሚያ ስልቶች

- የክልሉ መንገዶች ባለስልጣንና የወረዳ መንገድ ጽ/ቤቶችን አደረጃጀትና አስተዳደርን የማጠናከር ሥራ መስራት
- በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት
- የተቀናጀ የኔትወርክ ዕቅድን ማጠናከር፣ የመንገድ ጥገና ውጤታማነትን ማረጋገጥ
- በሰለጠነ የሰው ጉልበት በመጠቀም የአሰራር ዘዴን ማስፋፋት

- በመንገዶች ስራ የህብረተሰቡን ተሳትፎና የባለቤትነት ስሜት ማሳደግ፤

## 4.5.2. ኢነርጂ

***የትኩረት አቅጣጫ***

*የኢነርጂ ልማትን በሀገሪቱ በማስፋፋትና በማሳደግ ለሁሉም እንዲዳረስ ለማድረግ በተቀረጸው አገርአቀፍ የኤሌክትሪክ ሃይል የማዳረስ ፕሮግራም በቀጣይ አመታትም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። በተጨማሪም የባዮፊውል ልማትን በማስፋፋት የኤሌክትሪክ ፍጆታን ከአገር ውስጥ ታዳሽ ምንጮች ለማመንጨትና በሀገሪቱ በተቀየሰው የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ መሠረት ለተለያየ አገልግሎት የሚውል ሃይል ከባዮፊውልና ከመሠል ታዳሽ ምንጮች ለማምረት የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። በክልል ደረጃ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ስራዎች ቀጣይነት እንዲኖራቸው በማድረግ የአምራቾችንና የተጠቃሚዎችን አቅም በመገንባትና የልምድ ልውውጥን በማዳበር ቀደም ሲል የተጀመረውን የማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎ ብቃት የማሻሻልና የማሰራጨት ሥራዎች በስፋት የሚከናወኑ ሲሆን የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂን በክልሉ በስፋት ለማስተዋወቅና ጥቅም ላይ እንውሉ ለማድረግ የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።*

*በርቀት የሚገኙ የገጠር ከተሞችና መንደሮች የኤሌክትሪክ ኃይል በግለሰብ ወይም በማኅበር ተደራጅተው እንዲያገኙ ለማድረግ የገጠር የኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን የፀሐይና የነፋስ ሀብት አለኝታ ጥናት ፕሮጀክት በማካሄድ የፀሐይና የነፋስ ኢነርጂ ምንጮች ልማትና ቴክኖሎጂ ስርጭት እንዲስፋፋ ይደረጋል።*

***ዓላማ***

*ከሀገራዊው የኢነርጂ ዕቅድ ዋና ዋና ዓላማዎች ውስጥ የኢነርጂ ልማትን በማፋጠን የክልል የኢነርጂ ፍላጎትን ማሟላት፣ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትን ለማስፋፋት የሚያስፈልገውን የሃይል ምንጭ በየትኛውም ጊዜ በቂና አስተማማኝ እዲሆን ማድረግ፣ በቤተሰብና በተቋማት ደረጃ የባዮ - ጋዝ ማብላያ እና በፀሐይ ኢነርጂ የኤሌክትሪክ ሀይል የሚመነጩ ቴክኖሎጂዎችን በገጠሩ አካባቢ በስፋት በማመንጨት ህብረተሰቡ ለምግብ ማብሰያ የብርሃን አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ናቸው።*

***ግቦች***

***የኤሌክትሪክ ሃይል አገልግሎት አቅርቦት***

*በዘርፉ የሚሰሩ ሥራዎች በፌደራል መንግስት አማካኝነት ሲሆን ከክልሉ አንጻር የተቀመጡ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋናዋና ግቦች ተጥለዋል*

- *የክልሉ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ቤተሰብ ብዛት በማሳደግ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሽፋንን አሁን ከተደረሰበት* 22.28% *በ*2007 *መጨረሻ ወደ* 75% *ማሳደግ*
- *የኤሌክትሪክ አገልግሎት ያገኙ ቀበሌዎች ቁጥር በ*2002 *መጨረሻ ከተደረሰበት* 679 *በ*2007 *መጨረሻ ወደ* 2572 *ማድረስ*

***የኢነርጂ አማራጭ ልማት ማስፋፋት***

በባዮማስ ኢነርጂ ላይ በመስራት የሕብረተሰቡን የኢ.ርጂ አጠቃቀም በማሻሻል የማገዶ ፍላጎትን በመቀነስና አዳዲስ የኢነርጂ ምንጮችንና ቴክኖሎጂዎችን ሕብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል። ለዚህም በክልሉ በሚቀጥሉት አምስት አመታት የሚከናወኑ የሚከተሉት ግቦች ተጥለዋል

- በ2002 የነበረውን 71 በመቶ የአማራጭ ኢነርጂ (የተሻሻሉ መገዶ ቆጣቢ ምድጃዎች) ተጠቃሚ ቤተሰብ ሽፋን በ2007 መጨረሻ 95 በመቶ መማድረስ
- የባዮጋዝ ቴክኖሎጂን በማስፋፋት የተጠቃሚ ቁጥርን በትላልቅ ተቋማትና የንግድ ድርጅቶች ከ11 ወደ 41 እና በቤተሰብ ደረጃ ከ100 ወደ 3600 ማሳደግ፣
- ታዳሽ የኢነርጂ ምንጮችን (ከአነስተኛ የውሃ ሃይል፣ ጸሐይና ነፋስ) በመጠቀም የገጠር ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ በሆኑ የገጠረ ከተሞችና መንደሮች የሚኖሩ ቤተሰቦችን ቁጥር ከ 35 አባወራ ወደ 7715 እንዲሁም ተቋማትን ከ122 ወደ 342 ማሳደግ፣
- የባዮፊውል ቴክኖሎጂን በማላመድና በማስፋፋት ረገድ የባዮጋዝ ማብለያ ምድጃ ቴክኖሎጂዎችን ስርጭት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 1500 ማድረስ፣
- የተሻሻሉና ዘመናዊ የከሰል ማከሰያ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድና በማስፋፋት 100 ማድረስ፣

***የማስፈጸሚያ ስልቶች***

በዘርፉ በአምስት አመታት የታቀዱ የልማት ተግባራት ለማከናወን የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀምጠዋል

- የግል የሥራ ተቋራጮች በግንባታ እንዲሳተፉ በማድረግ በርካታ ከተሞችና የገጠር መንደሮች፣ ለመስኖ እርሻዎች እንዲሁን ለሌሎች የአገልግሎት የልማት ተቋማት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የቴክኒክና ሙያ ተመራቂዎችን በማደራጀት በገጠር ከተሞች የኤሌክትሪክ መብራት ሥራ ላይ በስፋት እንዲሰሩ ማድረግ፣
- በአማራጭ የኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ረገድ የፕሮጀክት አዋጭነት (Feasibility) እና የአተገባበር ስልት (Implementation Plan) የሚያሳይ ፕሮጀክት ሰነድ (Project Document) ማዘጋጀትና መጽደቅ፣
- በማላመድ፣ በማሻሻል ወይም አዲስ ዲዛይን በማድረግ የኢነርጂ ቴክኖሎጂ ምንጭ ማልማት፣
- የተለያዩ ናሙናዎች በማምረትና ፍተሻዎች በማከናወን የተገለጋዩን ጥያቄ የሚመልስ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ /ምንጭ ለሽግግር ዝግጁ ማድረግ፣
- በመስኩ ለመስራት ፍላጎት ያላቸውን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ግለሰቦች በማሳተፍ፣

- አምራቾችን የማሰልጠንና የማስተዋወቅ ሥራ መስራት፣ በሕብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ በስፋት በመስራት የቴክኖሎጂውን ፈላጊና ተጠቃሚ ማበራከት እንዲሁም ለአምራቾች የብድር አገልግሎት ማመቻቸት ሥራ ማስራት፣
- የሶላር ካምፓኒዎች የስርጭት ሥራን በዘላቂ እንዲሆን ለተጠቃሚዎች የአጠቃቀም መመሪያ ዶክመንትና ስልጠና መስጠታቸውንና ተጠቃሚዎች የባዮጋዝ ማብለያ መለዋወጫ ዕቃዎች በአካባቢያቸው በቀላሉ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸታቸውን ማረጋገጥ፣
- በኢነርጂ ልማት ዘርፍ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ሞልድ ወዘተ ማቅረብ፣
- በየቀበሌው የተሻሻሉ የማገዶ ቆጣቢ ምድጃ አምራቾች እንዲቋቋሙ ማድረግ፣
- በገጠር የኤሌክትሪክ አገልግሎትን ለማስፋፋት የኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎች ማህበራት እንዲቋቋሙ ከሚመለከተው አካል ጋር በጋራ ጥረት ማድረግ፣
- የኢነርጂ ሀብታችንን በሰፊው ለማልማትና ባለሃብቶችን ለመሳብ የሚችል የፕሮሞሽን ዶኩመንት በማዘጋጀት የማስተዋወቅ ስራ ማከናወን፣

### 4.5.3. ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት

#### የትኩረት አቅጣጨቀዎች

በቴሌኮሙኒኬሽን ረገድ አገራዊው የትኩረት አቅጣጫ የሚሆነው የተዘረጋውን ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን መረብ (Network) ጥራት ያለው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በሰፊው እንዲያስተናግድ ማስቻል እንዲሁም የአገልግሎት ጥራትን ማሻሻልና አገልግሎት ማስፋፋት ነው። ዘመናዊ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገጠሩን ጨምሮ ለሁሉም ሕብረተሰብ በአጭር ጊዜ እንዲዳረስ የUniversal Access Program ተነድፎ ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን የሚሰጠው አገልግሎት ስልክን በመደወል ላይ ብቻ ሳይገደብ ማህበራዊ አገልግሎቶችንና የልማት ስትራቴጂዎቻችንን ለመፈጸምና በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻል የሚያስችል መሆን እንዳለበት አገራዊ አቅጣጫ ተይዟል። በተጨማሪም በገጠር የሚገነቡ የቴሌኮሙኒኬሽን ማዕከላት የቴሌኮም አገልግሎት የሚሰጡ ብቻ ሳይሆን ከኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) እና ከሌሎች ፕሮግራሞች ጋር ተቀናጅቶ የገጠር ሕብረተሰብ ማዕከላት የሚሆኑበት አቅጣጫ ተይዟል።

#### ዓላማዎች

በዕቅድ ዘመኑ በአገር ደረጃ የተቀመጡ የቴሌኮሙኒኬሽን ዓላማዎች የተጀመሩ የኔትወርክ ኢንፍራስትራክቸር እና Applications ማጠናቀቅና ሥራ ላይ ማዋል፣ ፍላጎትን ያገናዘበ ኔትወርክ የማስፋፋት ሥራ ማከናወን ፣ ሞባይል፣ በኢንተርኔትና ዳታ የአገልግሎት ጥራትን መጠበቅና ማሻሻል፣ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ህገ ወጥ አሰራርን መከላከል፣ የወቅቱ የቴሌኮሙኒኬሽን ኢንዱስትሪ ዕድገት ውጤት የሆኑ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አገልግሎቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ ማመቻቸት፣ ሀገራዊ የፍሪኩዌንሲ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥጥርና የIP Address በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል እና የተገነባውን የኔትወርክ አቅም አሟጦ ስራ ላይ በማዋል ገቢን ማሳደግ ናቸው።

***ግቦች***

- የክልሉ የመደበኛ ስልክ ተጠቃሚ ደንበኞች ብዛት በ2002 ከነበረበት 695,427 ወደ 1,455,424 በማሳደግ የአገልግሎት ሽፋኑን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (2007) ከ19 በመቶ ወደ 40 በመቶ ማሳደግ፣
- በ 5 ኪ/ሜትር ርቀት መሠረታዊ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አሁን ካለበት 80 በመቶ ሽፋን በ2007 መጨረሻ ወደ 100 በመቶ ማድረስ
- የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ቀበሌዎችን ቁጥር አሁን ከተደረሰበት 2,743 ወደ ሁሉም ቀበሌዎች ማዳረስ፤
- የሞባይል ስልክ ተጠቃሚ ቁጥር በ2002 ካለበት 600,000 በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 6,185,580ማሳደግ

***የማስፈጸሚያ ስልቶች***

- የገጠር ቀበሌዎች የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦትና ሥርጭት ክትትል ሥራ ማጠናከርና እንዲሁም የአስተዳደርና የቴክኒክና ድጋፍ ስትራቴጂ መተግበር፣
- የኔትወርክ ፍሰትና ጥራትን አፈጻጸም መለካት የሚያስችሉ ስርዓቶችን መዘርጋት፣
- የቅሬታ መስተንግዶ አገልግሎት የሚሰጥበት አገልግሎት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፣
- የቴሌኮም አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና የኔትውርክ ብቃት ቁጥጥርን ማጠናከር፣
- በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ህግወጥ አሰራርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከሚመለከታቸው ጋር ለመስራት የሚያስል ሥርዓት መዘርጋትና ተባራዊ ማድረገ፣

## *4.5.4. የመጠጥ ውሃና መስኖ ልማት*

***የትኩረት አቅጣጫዎች***

ውሃ ጥቅም ላይ ሊውል ለሚችልባቸው የልማት መስኮች በተጠቃሚዎች መካከል ቅንጅትና ትስስር በመፍጠር ሁለገብ የውሃ ሃብት ልማትና ዘላቂ አጠቃቀም እንዲኖር ማስቻል፣ የወደፊቱን ትውልድ ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም ሥርዓት እንዲሰፍን ማድረግ፣ የአገሪቱ የውሃ ሃብት ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ ቀልጣፋና ተስማሚ በሆነ መልኩ ውሃን በማልማትና በመጠቀም ድርቅ የሚያመጣቸውን ክስተቶች መከላከል የውሃ ዘርፍ ፖሊሲ ዋና ዋና አቅጣጫዎች ናቸው።

የውሃ ሃብት አጠቃቀም፣ ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ ጎን ለጎን የሚሄዱ መሆናቸውን በመገንዘብ የመጠጥ ውሃ፣ የመስኖ ልማት፣ የማጠንፈፍ፣ የውሃ ነክ ስትራክቸሮች ተፋሰስ አስተዳደር እና የመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች በአንድነት እንዲካሄዱ ይደረጋል። የውሃ ሃብት አስተዳደር ከሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶች፣ ከተፋሰስ የውሃ ልማትና ከሌሎች የዘርፍ ልማት ግቦች ( ጤና፣ ማዕድን፣ ኢነርጂ፣ ግብርና፣ ወዘተ) ጋር የተጣጣመና የተቀናጀ ሆኖ ተፈጻሚ ይሆናል። በመጪዎች አምስት አመታት የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የመስኖና ድሬኔጅ ልማት፣ የከርሰ ምድርና የገጸ ምድር ውሃ ጥናት ዲዛይን በዘርፉ ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናሉ።

### ዓላማዎች

በክልሉ ያለውን ሰፊ የውሃ ሃብት ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ዘላቂና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በመጠቀምና በማልማት ለክልሉ ሕዝብ ንፁህ መጠጥ ውሃ በማዳረስ ጤናማና አምራች ዜጋ ማፍራት እንዲሁም የመስኖ ግንባታና የድሬኔጅ ልማትን በማካሄድ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ናቸው።

### ግቦች

**መጠጥ ውሃ**

- የክልሉን የከተማ ንጹህና ዘላቂ የመጠጥ ውሃ ሽፋንን(በ0.5 ኪ.ሜ ክልል ውስጥ በነፍስ ወከፍ በቀን 20 ሊትር) በማቅረብ ሽፋኑን በ2002 ከነበረበት 90% በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (በ2007) ወደ 100 በመቶ ማድረስና የገጠር ንፁህ የመጠጥ ውሃ ሽፋን (በ1.5 ኪ.ሜ ክልል ውስጥ በነፍስ ወከፍ በቀን 15 ሊትር) በ2002 ከነበረበት 60 በመቶ በ2007 መጨረሻ 100 በመቶ ማሳደግ፣
- አጠቃላይ የክለሉ የመጠጥ ውሃ ሽፋንን በ2002 ከነበረበት 64 በመቶ በ2007 መጨረሻ ወደ 100 ማሳደግ
- የተበላሹ የገጠር ውሃ ተቋማትን በ2002 ከነበረበት 18 በመቶ በ2007 በጨረሻ ወደ 10 ዝቅ በማድረግ ተቋማት በዘላቂነት እንዲያገለግሉ ማድረግ

የመሰኖ ልማትን በሚመለከት የመስኖ ልማቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ እንዲቻል

- አሁን ያለውን 12,393 ሄ/ር ለመስኖ ግንባታ ዝግጁ የሆነ ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን በዕቅድ ዘመኑ 57,131 ዲዛይን ሥራ በመስራት በ2007 መጨረሻ ወደ 69,524ሄ/ር ማድረስ፣ 27,389 ሄ/ር አነስተኛና 185,526 የመካከለኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ በማከናወን አሁን በመስኖ እየለማ ያለውን 32,726 ሄ/ር መሬት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 245,641ሄ/ር ማድረስ፣
- የከረሰ ምድር ውሃ ሃብት ልየታና ጥናትን ሽፋንን 70 % ማድረስ፣ የከረሰ ምድር ውሃ ሃብት ልየታና ጥናትን ሽፋንን 50 % ማድረስ

### ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

የመጠጥ ውሃ አቅቦትን በሚመለከት

- ፍላጎትን፣አቅምንና ቁጠባን መሠረት ያደረገ ውጤታማና አስተማማኝ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ፣
- ለገጠሩ ሕብረተሰብ የውሃ አቅርቦት ሽፋን እንዲስፋፋ ለማድረግ በአርሶ አደሩ ጉልበትና ዘላቂና አዋጪ የሆኑ ቀላል ቴክኖሎጂዎችን በጥቅም ላይ ማዋል፣

- *በነባር የውሃ ተቋማት ውስጥ የተቀላጠፈ አሰራር በመተግበር አዳዲስ የውሃ ልማት ፕሮጀክቶች ከመገንባታቸው በፊት ቁጠባን መሠረት ያደረጉ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችሉ ስልቶችን ማመቻቸት፣*
- *ነባር የውሃ ተቋማትን መንከባከብና ውሃን በቁጠባ በመጠቀም፣*
- *በቤተሰብ ደረጃ መሠረታዊ የውሃ ፍላጎቶችን ማሟላትና ከመሠረታዊ ፍላጎቶች ባሻገር የሚኖረው የውሃ ክፍፍልና አጠቃቀም ፍትሃዊ ቀልጣፋ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን በሚያመጡ መመዘኛዎች ላይ የተመሠረተ ኢንዲሆን ማድረግ፣*
- *ባልተማከለና በዝቅተኛ ደረጃ ያሉትን የውሃ አስተዳደር ተቋማት ጨምሮ ለተሻለና ለቀልጣፋ የውሃ ሃብት አስተዳደር አቅም ግንባታ ማካሄድ፣*

*የመሰኖና ድሬኔጅ ልማትን በሚመለከት*

- *አዳዲስ የመስኖ ልማቶችን መዘርጋትና በሥራ ላይ ማዋል፣*
- *የከርሰምድር ውሃ በሚገኝባቸው አካባቢዎች መካከለኛና ጥልቅ ጉድጓዶችን ቆፍሮ መጠቀም፣*
- *በመስኖ ውሃ አጠቃቀም ረገድ ውጤታማነትን ለማሻሻል የሚረዱ ቴክኖሎጂዎችና የአሰራር ሥልቶችን ተግባራዊ ማድረግ፣*
- *በተለያዩ ተፋሰሶች ውስጥ ያለውን የተዛባ የውሃ ግኝትና ስርጭት ለማስተካከል በአንጻራዊ ሁኔታ የሚከሰቱትን የድርቅና የጎርፍ ጉዳቶች ለመቀነስ በተፋሰሶች መካከል እንደ አስፈላጊነቱ የውሃ ሽግግር ማመቻቸት፣*
- *በአካባቢ ሃብትና ዕውቀት ላይ የተመሠረተ የውሃ ማግኛና አጠቃቀም ዘዴዎችን ማራመድና ማበልጸግ፣*

### 4.5.5. የትራንስፖርት አገልግሎት

**የትኩረት አቅጣጫ**

*የትራንስፖርት መሠረተ ልማት ከመገንባት በተጨማሪ ሌላው ትኩረት የሚሰጠው የትራንስፖርት አገልግሎት ቅልጥፍናን በማሳደግና በማቀናጀት የቅብብሎሽ ሥርዓት በመፍጠር የትራንስፖርት ወጪን መቀነስ ፣እንዲሁም በአገልግሎት አቅርቦት የግል ባለሀብቱን አቅም በመገንባት ጉልህ ሚና እንዲኖራቸው ማድርግ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ነው። ከዚህ በተጨማሪም ትራንስፖርት አግልግሎት ያለውን አደረጃጀትና አሰራር ቀልጣፋና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የአሠራር ስልቶችን አደረጃጀት መቀየስና ተግባራዊ ማድርግ፣ እንደዚሁም የገጠሩ ሕዝብ በጉዞ የሚያባክነውን ጊዜና ጉልበት ምርታማ በመሆኑ ስራዎች ላይ እንዲያውል ለሁሉም ቀበሌዎች በጋራ በጋና ክረምት የሚሰሩ የተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮች እንዲስፋፉ ማድርግ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።*

*ከዚህም ጋር ተያይዞ በክልሉ በተመረጡ ዋና ዋና ከተሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ያለው ኤኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚደገፍ የትራንስፖርት አግልግሎት ይህም የከተሞችን የመሬት አጠቃቀም እና የልማት ዕቅድን መነሻ አድርጎ በሚፈጠረው አዲስና ነባር የትራፊክ ፍሰት መሠረት ያደረገ የከተማዎችን*

*የብዙሃን መጓጓዣ* (Mass transit) *ትራንስፖርት መሰረተ ልማትና አገልግሎት ማስፋፋት ትኩረት የተሰጠው ነው።*

*በከተሞች ትራንስፖርት አንዱ ቁልፍ ችግር የማስፈጸም አቅም* (Institutional capacity) *አናሳ በመሆኑ የአመራሩን እና በዘርፉ ያለውን የሰው ኃይል አቅም ለማሳደግ ሌላው ትኩረት የተሰጠው ተግባር ነው። በክልላችን ያለው የትራፊክ አደጋ ክልሉ ካሉት\ በክልሉ ከሚንቀሳቀሱት ተሽከርካሪዎች ብዛት አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ሆኑ ይገኛል። በትራፊክ አደጋ ምክናያት በሰው ህይወትና በንብረት ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት የመቀነሱ ተግባር ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ ባለመሆኑ ከተሞችን ባሳተፈ መልኩ የተቀናጀ የትራፊክ ደህንነት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል አሠራር እና በመረጃ ቴክኖሎጂ የሚደገፍ ዘመናዊ የትራፊክ ማኔጅመንት ሥርዓት በመዘርጋት ትራፊክ ደህንነት ሥራዎችን ቀልጣፋ ማድርግ ትኩረት ተሰጥቶታል።*

**ዓላማዎች**

*ዘርፉ የሚጠይቀውን ደረጃና ተወዳዳሪነት ለማሟላት የሚያስችል ብቃት ያላቸው የግሉ ዘርፍ አግልግሎት ሰጪዎችና መንግስትዊ ሬጉላተሪ ተቋም መገንባት፤ በዘርፉ የላቀ አመራርና አሠራር ማስረፅ የሚያስችል የሠው ኃይል አቅም መገንባት፣ የህዝብ ትራንስፖርት አግልግሎት አስተማማኝና በዋጋ ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ፣ የገጠሩ ህብረተሰብ በጉዞ የሚያጠፋውን ጉልበትና ጊዜ በመቀነስ ለልማት እንያዉለው ማስቻል፣ የከተማ ትራንስፖርት አገልግሎትን ምቹ ደህንነቱ የተጠበቀ ፈጣን ፣ ተደራሽ አስተማማኝ እና የተቀናጀ ማድርግ፣ በመንገድ ላይ በተሽከርካሪ አደጋ ምክናያት የሚደርስ የሰው ሞትና የንብረት አደጋ መቀነስ፣ ክልላዊ የህዝብና የጭነት ትራንስፖርት መረጃ ማዕከል ማደራጀት እና የጭነት ትራንስፖርትን የሎጀስቲክ ጊዜ እና ወጪን መቀነስ የሚሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።*

**ግቦች**

*የትራንስፖርት አገልግሎትን በማስፋፋት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ*

- *የገጠሩን ማህበረሰብ የጊዜና ጉልበት ብክነት ለመቀነስ በዕቅድ ዘመኑ በገጠር ኮሚኒቲ መንገዶች ባሉባቸውና ምርታማ አካባቢዎች በሆኑት ለምርትና ለግብዓት ማጓጓዣ* 35,000 *የተሻሻሉ የመካከለኛ ሞተር አልባና አነስተኛ ባለሞተር የትራንስፖርት ቴክኖሎጂዎች በግል ባለሀብቱ በኩል በማስመረትና በማሰራጨት እስከ* 35,000 *አባወራ/እማወራ/ ተጠቃሚ እንዲሆንና ከዚህ ውስጥ* 30%*ቱ ሴቶች እንዲሆኑ ማድረግ፣*

- *ከከተማ ከተማና/ ከከተማ ገጠር ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት አሁን ካለበት* Available seat k.meter *በየዓመቱ በ*10% *ማሳደግና የተሽከርካሪዎችን አማካይ ዓመታዊ የመጓጓዝ አቅም አሁን ካለበት* 70 *ሺህ ወደ* 100 *ሺህ ኪ/ሜትር ማሳደግ፣ እንዲሁም አሁን ያለውን* 82 *የወረዳ ከተሞችን የመናኸሪያ አገልግሎት ማጠናከርና* 47 *አዲስ መናሃሪያዎችን በመገንባት የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣*

- በዋና ዋና የልማት ማዕከላት የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎትን አሁን ካለበት Available ton k.meter በየዓመቱ 5% በማሳደግና የጭነት ተሽከርካሪዎችን የመጓጓዝ አቅም ከ80 ወደ 100 ሺ ኪሎ ሜትር ማሳደግ፣
- በትራንስፖርት ችግር ምክንያት የህብረተሰቡን የስራ ጊዜ ብክነት ለመቀነስ የከተማ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎትን በማስፋፋት አሁን ካለበት Available seat k.meter በየዓመቱ 10% ማሳደግና አማካይ የቆይታ ጊዜ /Waiting time/ ከ15 ደቂቃ ወደ 5 ደቂቃ ዝቅ ማድረግ፣
- አሁን ያለዉን የመንግስት ተሽከርካሪዎች የትራንስፖርት ወጪ ብክነት 54% ወደ 10% እንዲሆም የግል ዘርፍ ተሽከርካዎችወጪን ከ38% ወደ 10%ዝቅ ማድርግ፣
- ቀልጣፋ የውሃ ላይ ትራንስፖርት በመስጠት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድርግ፣ አሁን ያለውን የጀልባ ቁጥር በ10% በማሳደግ ሁሉም የውሃ ትራንስፖርት አመቺ በሆኑ ወንዞችና ሀይቆች ላይ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ /ጣና ሀይቅ፣ ሀይቅ/ተሁለደሬ፣ አርዲቦ/ወረባቡ፣ አባይ ወንዝ፣ ተከዜ፣ ቆጋ፣ ጣና በለስ /
- የጣና ሃይቅ ትራንስፖርት ድርጅት ተወዳዳሪ፣ ለህብረተሰቡና ለቱሪስቱ ተደራሽና ትርፋማ አገልግሎት ሰጭ ተቋም እንዲሆን በማስቻል ድርጅቱ በ2001 ዓም ከነበረው ብር 972,916 ትርፍ በየዓመቱ በ10 በመቶ በማሳደግ በእቅድ ዘመኑ ብር 6.5 ሚሊዮን ማድረስ፣
- በትራንስፖርት አገልግሎቱ በሕይወትና በንብረት ላይ የሚያደርሰውን የትራፊክ አደጋ አስከፊ እየሁነ በመምጣቱ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቱ በመሥራት በትራፊክ አደጋ ምክንያት በ2001 በጀት ዓመት በየ10ሺ ተሽከርካሪ የነበረውን 355 ሰዉ ሞት መጠን በ92.4% በመቀነስ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 27 ዝቅ ማድረግ፣ በተጨማሪም የከባድና የቀላል የአካል ጉዳት እና የንብረት ውድመትን በዚሁ መጠን መቀነስ፣

**የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች**

- በዓለም አቀፍ ደረጃ ምርጥ የመንገድ ትራንስፖርት ተቋም የሚጠቀሙበት አዳዲስ የሬጉላተሪና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራሮችን ተግባራዊ ማድርግ፣
- በክልል በዞናችና በከተሞች ያለው የትራፊክ አደረጃጀት የተጣጣመ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖረው ማድርግ፣
- በየከተማው ጥቅም ላይ መዋል የሚገበው የመንገድ አይነት የኔትወርክ ባህርይና አጠቃቀም በቅድሚያ መለየት ፣
- የሕዝብ ትራንስፖርት ስምሪት ስርዓት በመዘርጋትና መተግበር፣
- የህዝብ ዕድገትና ትራንስፖርት እንቅስቃሴ የተከተለ መናኸሪያ ቦታ በከተሞች ፕላን ውስጥ እንዲካተት እና አገልግሎት እንዳይቋረጥ በከተማ አስተዳደሮች ትኩረት እንዲሰጥ ማድረግ፣
- በህዝብ ማመላለሻ የተሰማሩ ባለሃብቶች የንግድ ኩባንያ አሰራርን እንዲተገብሩና አዲስና ዘመናዊ ተሽከርካሪ እንዲያስገቡ ማበረታታት፣

- የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተስብ ክፍሎች ምቹ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ማቅረብ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣
- የአገልግሎት አጠቃቀም ከፍተኛ እንዲሆን ከግል ባሻገር በህብረት ስራ ማህበራት በወል ባለቤትነት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድርግ፣
- በገጠር ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ለሚሰማሩ አካላት ማበረታቻ መስጠት ፣
- አግባብ ያለው የምንገድ አጠቃቀም ስትራቴጅ ተግባራዊ ማድርግ ( የእግረኛና ሞተር አልባ ብስክሌት መንገድ ማመቻቸት፣ የእንስሳትና በአጠቃላይ መንገድ የሚሻሙ ተግባራትን መቀነስ)
- የትራፊክ ፍሰትን በዘመናዊ መንገድ በመምራት ( የትራፊክ ማኔጅመንት ማዕከል በማቋቋም እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መጠቀም) በአደገኛ ቦታዎች በተተከሉና በተንቀሳቀሽ ራዳሮች ወይም CCTV የፍጥነት ገደብ ቁጥጥር ማድርግ፣
- የመንገድ ድህንነተ ካውንስል በየደረጃው በማቋቋም የሚቀረጹትን ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በቅንጅት እንዲሰሩ ማድርግ፣
- የህዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችና ከፍተኛ ስጋት (High Risk) ያለባቸውን የጭነት ተሽከርካሪዎች የፍጥነት መገደቢያ ቴክኖሎጂ (Speed limit technology) እንዲጠቀሙ ማድርግ ፣

## 4.5.6. ሥራና ከተማ ልማት

**የትኩረት አቅጣጫዎች**

የከተማ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች ድህነትን መቀነስ ብሎም ማስወገድ፣ ከተማና ገጠሩን እንዲሁም ከተሞችን እርስ በእርሳቸው ትስስር እንዲኖራቸውና እንዲመጋገቡ ማድረግ፣ ህዝቡን በልማት ስራ በሰፊው ማሳተፍ፣ ሰፊና ቀጣይ የልማትና የመልካም አስተዳደር ህዝባዊ ንቅናቄ እንዲኖር ማድረግ፣ በህዝቡ ፍላጎትና አቅም ላይ የተመሰረተና በመንግስት አመራርና ተሳትፎ በቅንጅት የሚካሄድ ልማት ማጠናከር፣ ከልማታዊ ባለሀብት ጋር ጠንካራ አጋርነት መፍጠር፣ ያልተማከለ አስተዳደር በመዘርጋት ከተሞች ራሳቸውን የማስተዳደር ሰፊ ነፃነትና ስልጣን እንዲኖራቸው ማስቻል ናቸው።

የቤት ልማትን በተመለከተ የከተማ አስተዳደሮች ለቤት ልማቱ የሚሆን መሬትና መሰረተ ልማት ማቅረብ፣ ያረጁ ቤቶችና አካባቢዎች በባለንብረቶች እንዲሻሻሉና እንዲታደሱ የአካባቢውን መሰረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ለማሻሻል እገዛ መስጠት፣ ወጭ ቆጣቢና ከነዋሪው ህብረተሰብ አቅም ጋር የሚመጣጠኑ ቤቶችን በመገንባት በረጅም ጊዜ ክፍያ ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች የቤት ባለቤት እንዲሆኑ እና በከተማ አስተዳደሮችና በማህበራት የሚከናወኑ የቁጠባ ቤቶች ግንባታ ያረጁ አካባቢዎችን እየተካ የሚያድስና ከተማን የሚያሻሽል እንዲሆን ማድረግ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው።

በከተሞች የመሰረተ ልማትን በተመለከተ ፈጣንና ፍትሃዊ ልማትን ማረጋገጥ፣ ከተሞች ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ያላቸውን ሚና መሰረት በማድረግ መሠረተ ልማት መዘርጋት፣ መሠረተ-ልማት

*የማስፋፋቱ ስራ በመንግስት፣ በባለሀብቱና በህዝብ ቅንጅት እንዲፈጸም ማድረግ፣ በከተሞች የሚገነቡ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ሰፊ የስራ እድልና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በሚፈጥር መልኩ ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረግ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።*

*የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሰው ሀይልን በብዛት የሚጠቀም፣ ልማታዊ፣ ገበያ መር፣ ጤናማ ውድድር የሰፈነበትና የግሉ ዘርፍ ከፍተኛ ሚና የሚጫወትበት፣ ከሙስናና ከስነ-ምግባር ግድፈት የፀዳ፣ በኮንስትራክሽንና ተዛማጅ ስራዎች ለሚሰማሩ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ ትኩረትና ሁለንተናዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ የሚሰጥ፣ የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት በየደረጃው የሚያረጋግጥና የኮንስትራክሽን ዲዛይን አካል ጉዳተኞችን ያገናዘበ እንዲሆን ይደረጋል።*

***ዓላማዎች***

*የዘርፉ የሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ዕቅድ ዋና ዋና ዓላማዎች በከተሞች ያለውን የመልካም አስተዳደር ሁኔታ በማሻሻል ፈጣን፣ ፍትሀዊና ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ የከተማ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ፣ በከተሞች ዘላቂ ልማትንና የነዋሪዎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ውጤታማና ቀልጣፋ የመሬት አስተዳደር ስርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ፣ የከተማ-ገጠርን ትስስር የሚያጠናክርና የህብረተሰብ ፍላጎት የሚያረካ በጥናትና ምርምር የተደገፈ የከተማ ፕላን ማዘጋጀት፣ በከተሞች ደረጃውን የጠበቀና ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የሚመጥን የቤት ልማት ስራ በማከናወን የከተማ መተፋፈግንና እርጅናን ማስወገድ የመጠለያ ችግርንም መቅረፍ፣ ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ቀልጣፋና ፍትሃዊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ ማስቻል፣ ለስራና ለመኖሪያ ተስማሚ የሆነ ንጹህ የከተማ አካባቢ እንዲኖር ማድረግ፣ የህብረተሰቡን አጋርነትና ተጠቃሚነት በማረጋገጥ የልማቱ ዋነኛ ተዋናይ እንዲሆን ማድረግ፣ የቁጠባ ባህልን ማዳበርና ሰፊ የስራ እድልን መፍጠር፣ በመሠረተ-ልማት ግንባታና አስተዳደር የሰው ጉልበትን በስፋት በመጠቀም ሥራ አጥነትንና ድህነትን በመቀነስ የከተማ ነዋሪውን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፣ የዲዛይንና የኮንስትራክሽን ሥራዎች የጥራት ደረጃቸው ተጠብቆ እንዲከናወኑ ማድረግ፣ ኢንዱስትሪው ለስራ እድል መስፋፋት የጎላ ሚና እንዲጫወትና የአገር ውስጥ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና አቅራቢዎች እንዲስፋፉና አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ እና በአገር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ክልላዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲፈጠር ማድረግ የሚሉት ናቸው።*

***ግቦች***

***ከተማ ልማትን በሚመለከት***

- ❖ *ከተሞች ተመጋጋቢ ልማትና እድገት እንዲያመጡ ብቃታቸውን ማሳደግ*
- ✓ *በዕቅድ ዘመኑ ግልጽና ቀልጣፋ የሆነ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት* 100 *ከተሞችን ወደ ታዳጊ፣* 50 *ከተሞችን ወደ ንዑስ ማዘጋጃ፣* 15 *ከተሞችን ወደ መሪ ማዘጋጃ፣* 25 *ከተሞችን ወደ አነስተኛ ከተማ አስተዳደር፣* 5 *ከተሞችን ወደ መካከለኛ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም* 2 *ከተሞችን ወደ ሜትሮፖሊታን ከተማ አስተዳደር የደረጃ ሽግግር ለውጥ ማድረግና አደረጃጀት በመስራት ለነዋሪዎቻቸው ምቹ ሁኔታን መፍጠር*

- ✓ በከተሞች የተደራጀ የመሬትና መሬት ነክ መረጃ ስርዓት በመፍጠር በ2002 የነበሩትን 4 የዘመናዊ ካዳስተር ተጠቃሚ ከተሞች እስከ 2007 መጨረሻ 15 ከተሞችን ተጠቃሚ በማድረግ ቁጥራቸውን 19 ማድረስ፣ እንዲሁም 240 ከተሞች የተደራጀ የባህላዊ መሬትና መሬት ነክ መረጃ ስርዓትና የተሟላ የመሬት ቆጠራ መረጃ እንዲኖራቸው በማድረግ ለተጠቃሚዎች የተሟላ መረጃ እንዲኖሩ ማድረግ
- ✓ በዕቅድ ዘመኑ በ38ቱ ከተማ አስተዳደሮችና በ10ሩ ዞኖች ስር ባሉት ከተሞች 45,902 ሄክታር መሬት ለተለያየ አገልግሎት እንዲውል መዘጋጀት እና እስከ 2007 መጨረሻ በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች 2,800 ሄክታር መሬት በባንክ መያዝ
- ✓ ከዚህ ቀደም ፕላን ያልነበራቸውን 66 ከተሞች እና አዲስ የሚመሰረቱ 250 ከተሞችን ፕላን እንዲኖራቸው በማድረግ በፕላን የሚመሩ ከተሞችን በ2002 ከነበሩት በቁጥር 197 ከተሞች በ2007 መጨረሻ ወደ 513 ማሳደግ፣ ለ60 መካከለኛና ትላልቅ ከተሞች የክለሳ ፕላን ዝግጅት ማድረግ፣ በ38ቱ ከተማ አስተዳደሮች በ72 ያረጁና የተፋፈጉ አካባቢዎች የመልሶ ማልማት የአካባቢ ልማት ፕላን በማዘጋጀት ለቀጣይና ዘላቂ ልማት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ
- ✓ በከተሞች ያለውን የቤት ችግር ለመፍታት በ12 ከተሞች የተጀመሩትን 13,147 ቤቶች በማጠናቀቅ ለተጠቃሚዎች ማከፋፈል
- ✓ በከተሞች ያለውን የቤት ችግር ለመፍታት እስክ 2002 ለተጠቃሚዎች የተከፋፈሉትንና በግንባታ ላይ ካሉት 20050 ቤቶች በተጨማሪ በዕቅድ ዘመኑ 30,000 ቤቶች በመገንባት በክልሉ ውስጥ ያለውን የመኖሪያ ቤት እጥረት መቀነስ
- ✓ በ23 ከተሞች 291 ነባርና 748 አዲስ የሚደራጁ በድምሩ 1039 የግንባታ ግብዓት አቅራቢና የግንባታ አከናዋኝ ማህበራትን በማሳተፍ ለ25,000 ስራ አጥ ወገኖች የስራ እድል መፍጠር
- ✓ በዕቅድ ዘመኑ በቁጥር 38 ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ መገንባትና ከዚህም ውስጥ 5ቱን በከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት መገንባት፣ እንዲሁም በ23ቱ ከተሞች የፍሳሽ ቆሻሻ መድፊያ ቦታዎች መገንባትና ከዚህ ውስጥ አንዱ በከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት በማከናወን የከተሞችን ውበትና ጽዳት መጠበቅ
- ✓ በ12ቱ ከተሞች ዘመናዊ ቄራዎች መገንባትና ከነዚህ ውስጥ 5 ያህሉ በከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት መፈፀም
- ✓ በ38ቱ ከተሞች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የመሸጫ ቦታዎች ማዘጋጀትና ከዚህ ውስጥ 36 በክልል/ከተሞች እና 2 በከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማከናወን
- ✓ በዕቅድ ዘመኑ የከተሞችን ልማት ለማፋጠን ህብረተሰቡን ያሳተፈ ስራ ለመስራት እንዲያስችል በህብረተሰቡ ጉልበት፣ በገንዘብና በቁሳቁስ በጠቅላላው ብር 500 ሚሊየን የሚገመት የልማት ተግባራት ማከናወን
- ✓ የገጠር ቀበሌ ማዕከላት ሽንሽና ፕላን ብዛትን በቀበሌ ቁጥር በ2002 ካለበት 25 በዕቅድ ዘመኑ 3427 የሽንሽና ፕላን በማዘጋጀት በ2007 መጨረሻ ወደ 3452 ማሳደግ

- ✓ ዘመናዊ የግብይት ስርዓትን ለማከናወን እንዲያስችል በተመረጡ ከተሞች ዘመናዊ የከተማ ገበያ እስካሁን ምንም ያልነበረ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ 3 ዘመናዊ ገበያዎች እንዲኖሩ ማድረግ፣ እንዲሁም የለማ የገበያ ማዕከል ብዛት በ2002 ከደረሰበት 11 ወደ 38 ማሳደግ
- ✓ የከተሞችን ውበትና የኗሪዎችን የመዝናኛ ፍላጎት ለማሟላት በዕቅድ ዘመኑ በተለያዩ ከተሞች ደረጃቸውን የጠበቁ 10 የለሙ የከተማ መዝናኛ ማዕከላት እንዲኖሩ ማድረግ
- ✓ በከተሞች ከሚሰሩ የመኖሪያ ቤቶች ውስጥ የሴቶች ተጠቃሚነትን ተጠቃሚነት ከፍ ለማድረግ በ2002 ካለበት 21.6 በመቶ በ2007 መጨረሻ ወደ 50 በመቶ ማድረስ
- ✓ የከተሞችን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም በማሳደግ የከተሞችን ልማት ለማፋጠን በከተማ ስራ አመራር የድህረ ምረቃ ዲግሪ 500 ባለሙያዎችን በማስተማር በ2002 የነበረውን የዘርፉን የተማረ የሰው ቁጥር ማሻሻል
- ✓ የተጀመሩ የአግሮስቶን ፋብሪካ ግንባታዎችንና የተከላ ስራቸው የተጀመሩ ክሬሸሮችን በማጠናቀቅ ስራ ማስጀመር

የዲዛይን፣ ኮንስትራክሽንና የከተሞች መሠረተ ልማትን ለማሳደግ ከ2003-2007 የሚከተሉት ግቦች በዘርፉ የተቀመጡትን ዓላማዎች መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ተቀምጠዋል

- ✓ በዕቅድ ዘመኑ ለ250 ተወዳዳሪነት አቅም ያላቸው የስራ ተቋራጮች ፈቃድ፣ ለ250 መለስተኛ የግንባታ ባለሙያዎች የክህሎት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሁም ለ50 አማካሪዎች ፈቃድ መስጠት
- ✓ እስከ 2007 መጨረሻ 425 መካከለኛና አነስተኛ የስራ ተቋራጮችን ማደራጀትና 2 የተደራጁ የከተሞች አክሲዮን ማህበራት እንዲኖሩ ማድረግ
- ✓ በእቅድ ዘመኑ የ100 የግንባታ አገልግሎት አቅራቢዎችን፣ የ425 ተቋራጮችንና የ50 አማካሪዎችን አቅም መገንባት
- ✓ በዕቅድ ዘመኑ 1 የአካባቢ የግንባታ እቃዎች ምርምር ማዕከል ማቋቋም፣ 5 አዳዲስ ወጭ ቆጣቢ የግንባታ እቃዎች እንዲሁም 10 ወጭ ቆጣቢ የተሻገሩ የአዳጊ ቤቶች አገነባብ ቴክኖሎጅዎች ማዘጋጀትና ለሚመረቱ የግንባታ ዕቃዎች ምርምር የጥራትና ደረጃ ቁጥጥር ማካሄድ
- ✓ የከተሞችን የውስጥ ለውስጥ መንገድ ደረጃቸውን ለማሻሻል በ2002 ያለውን 38 ኪ.ሜ የኮብል ስቶን ንጣፍ በ2007 መጨረሻ 343 ኪ.ሜ ማድረስ
- ✓ በተለያዩ ከተሞች 300 ኪ.ሜ የተፋሰስ መስመር መዘርጋትና ከዚህም ውስጥ 200 ኪ.ሜ በከተሞች በራሳቸው ገቢ እንዲሁም 100 ኪ.ሜ በከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸም
- ✓ በዕቅድ ዘመኑ 1100 ኪ.ሜ አዲስ የጠጠር መንገድ ስራ፣ 1800 ኪ.ሜ የነባር ጠጠር መንገድ ጥገና፣ 850 ኪ.ሜ የመብራት መስመር ዝርጋታና 800 ኪ.ሜ የውሃ መስመር ዝርጋታ ስራዎች በማከናወን የከተሞችን ኗሪ ተጠቃሚ ማድረግ

**የማስፈጸሚያ ስልቶች**

ከላይ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈፀሚያ ስትራቴጅዎች መተግበር ይኖርባቸዋል።

**ከተማ ልማትን በሚመለከት**

- በተለያዩ ደረጃዎች ያለ የአቅም ውስንነትን ማሻሻል እንዲሁም በከተሞች መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ
- የቤት ግንባታ ወጭ ቆጣቢ እንዲሆን በሀገር ውስጥ የግንባታ እቃዎች ላይ እንዲመሰረት ማድረግ
- የግሉ ዘርፍ የቤት ልማት ህብረት ስራ ማህበራት እና የሪል እስቴት አልሚዎች በቤቶች ግንባታ በስፋት የሚሳተፉበትን የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠርና ድጋፍ ማድረግ
- የከተማ ነዋሪዎች በማህበር ተደራጅተው የጋራ መኖሪያ ህንጻዎችን እንዲገነቡ ማበረታታት
- የከተሞችን የፋይናንስ አቅምና አስተዳደርን ማሻሻል
- በመንግስት፣ በከተማ ነዋሪው እና በእርዳታ ሰጭዎች የተቀናጀ ድጋፍ የከተሞችን መሠረተ ልማት በማስፋፋትና በማሻሻል ለነዋሪዎቻቸው ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ
- የመሬት ልማትና አስተዳደር ግልጽ ተጠያቂነት የሰፈነበትና ወጭ ቆጣቢ እንዲሆን ማድረግ
- የመረጃ ሥርዓትን የተጠናከረ ማድረግ
- የከተማ መሰረተ ልማት አቅርቦትን የተሟላ እንዲሆን ማድረግ
- ያረጁ ቤቶችንና የተጨናነቁ አካባቢዎችን እንደገና ማልማት
- በከተሞች ስራ አጥነትንና ድህነትን ለመቀነስ መረባረብ

**የዲዛይን፣ ኮንስትራክሽንና የከተሞች መሠረተ ልማትን በሚመለከት**

- የተቋራጮችንና አማካሪዎችን አቅም ለማሳደግ የሚያግዙና የፍቃድ ስርዓቶችን የሚመለከቱ መስፈርቶችን መፈተሽና የማሻሻያ ስራ አጠናክሮ ማስቀጠል።
- የአገር ውስጥ የስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች አቅማቸውን በመገንባት የዓለም አቀፍ ግኘ የሚጠይቁ የተወሰኑ ፕሮጀክቶች ላይ የሚሳተፉበትን አካሄድ መከተል
- የአካባቢ የግንባታ ዕቃዎችን በቴክኖሎጅና ምርምር በመታገዝ ማጎልበትና በግንባታ ውስጥ የመጠቀም ስልት መከተል
- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የቁጥጥር ስርዓት ማጠናከር
- በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ አካላት/ድርጅቶች ብዛትና አቅምን ማሳደግ
- የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ምርምርና የቤቶች ግንባታ አማራጭ ቴክኖሎጅ አቅም እንዲጠናከር ማድረግ

## 4.5.7. ባህልና ቱሪዝም

**የባህል ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች**

የባህል ፖሊሲ በክልሉ ብሔር ብሔርሰቦችና ሕዘቦች የቋንቋ፣ የባህል፣ የታሪክና የተፈጥሮ ቅርሶች፣ ስነጥበባትና ዕደጥበባት፣ በኩልነት እንዲታዎቁ በሳይንሳዊ ዘዴ እንዲመዘገቡና እንዲጠኑ ፣ እንክብካቤና ጥበቃ እንዲያገኙ፣ የባህል ተቋማትና ማዕከላት እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ዜጎች በማናቸውም የባሕል እንቅስቃሴዎች በነጻነትና በኩልነት እንዲሳተፉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታዎችን እንዲፈጠር ትኩረት ይሰጣል።

**የባህል ዘርፍ ዓላማዎች**

የባህል ዘርፍ በሚቀጥሉት አምስት አመታት ዋና ዋና ዓላማዎች የክልሉ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ማንነት የሚገለጹባቸው ቋንቋዎች፣ ቅርሶች፣ ታሪኮች፣ የሥነ ጥበብና ዕደ ጥበብ ውጤቶች፣ ሥነ ቃሎች፣ ወጎች፣ እምነቶችና ሌሎች ባህላዊ ገጽታዎች በእኩልነት እንዲታዎቁ፣ እንዲከበሩና በእንክብካቤ ተይዘው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ማድርግ እና በሳይንሳዊ ዘዴ እየተጠኑ የሚበለጽጉበትን ለልማት ጠቀሜታ የሚውሉበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በባህል መስክ ለተሰማሩ የፈጠራና የምርምር ባለሙያዎች ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የብሔር ብሔርሰቦችና ሕዝቦች ባህል ከዘመኑ ትምህርት፣ ሳይንስና ቴክኖለጂ ጋር በተጣጣመ መልኩ ለማሳደግና ባህሉን ጠንቅቆ የሚያውቅ ፣ የሚጠብቅ ፣ በባህሉና በማንነቱ የሚኮራ ጠንካራ ዜጋ ለመፍጠር  በባህል መስክ በየደረጃው የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ለማመቻቸት፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ደረጃ በደረጃ ማስወገድ የሚሉት ናቸው።

**የባህል ዘርፍ ግቦች**

- በክልሉ ያሉት የባህል ሙዚየም ብዛት እሰከ 2002 ዓ.ም ድረስ 2 ብቻ ሲሆኑ በአምስት ዓመት ውስጥ ተጨማሪ 10 የባህል ሙዚየም በመገንባት 2007 ዓ.ም መጨረሻ 12 ማድርስ፣
- እስከ አሁን የተገነቡ የኪነጥበብ ማዕከላት በክልሉ 11 ሲሆኑ በአምስት ዓመቱ ውስጥ 89 የኪነጥበብ ማዕከላት በመገንባት 100 ማድርስ፣
- በክልሉ ከአሁን በፊት በቅርስ ዳሰሳና ጥናት በቁጥር 298 ጥናቶች የተደረጉ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ ተጨማሪ ጥናቶችን በማድርግ ወደ 500 ጥናቶች ክፍ ማድርግ፣
- የቅርስ እንክብካቤና ጥገና የተደረገላቸውን 106 ቅርሶች በደንብ በማያዝ በተጨማሪ 114 ቅርሶችን ጥገናና እንክብካቤ በማድርግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 220 ማሳደግ፣
- በዕቅድ ዘመኑ ውስጥ ምዝገባ የተደረገላቸውን 1,193 ቋሚ ቅርሶችና 21,102 ተንቀሳቀሽ ቅርሶች ቁጠራ በማካሄድና በክልሉ በሁሉም ቦታዎች ያልተመዘገቡ ቅርሶችን ሙሉ በሙሉ እንዲመዘገቡ ማድርግ፣
- ከዚህ በፊት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረገ የባህል ትውውቅ ያልነበረ ሲሆን በቀጣይ ዕቅድ ዘመን በዓለም አቀፍ ደረጃ በዓምት አንድ ጊዜ በማካሄድ በዕቅድ ዘመኑ 4 ጊዜ የባህል ትውውቅ እንዲኖር ማድርግ፣

- በባህል ማዕከላት በህዝብ ቤት መጽሃፍትና በንናባብ ቤቶች ግንባታ፣ በቅርስ ጥገናና እንክብካቤ፣ በሙዝየም ግንባታ፣ በማህበረሰብ አቀፍ ቱሪዝምና በጥብቅ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት ግንባታ 80 ከመቶ በህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲሸፈን ማድርግ፣
- የባህል ተቋማትን የማስፋፋት፣ የባህል ዕሴቶችን የማልማትና የኪነ ጥበባት ፈጠራን ለማሻሻል አሁን ካለው 55 የህዝብ ቤተ መጽሃፍትን በተጨማሪ 45 የህዝብ ቤተ መጽሃፍት ግንባታዎችን በማካሄድ ቁጥሩን ወደ 100 ማሳደግ፣ እንዲሁም በክልሉ በገጠርና ከተማ ቀበሌዎች አሁን ያሉትን 151 የንባብ ቤቶች ቁጥር በማጉልበትና አዳዲሶችን በመገንባት ወደ 800 በማድረስ የተጠቃሚውን ቁጥር 1.5 ሚሊዮን ወደ 3 ሚሊዮን ማድርስ፣
- አንድ የአማራ ክልል ህዝቦች ብሔራዊ ሙዜየም መገንባት
- የባህል ተቋማትን ለማስፋፋት፣ የባህል ዕሴቶችን ለማልማትና የኪነ ጥበባት ፈጠራን ለማሻሻል የባህል ሙዚቃ ቡድናችን መሳደግ፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ በአራቱም የኪነጥበብ ዘርፍ ፌስትቫሎችንና ውድድሮችን ማካሄድ፣

**የባህል ዘርፍ የማስፈጸሚያ ስትርቴጂዎች**

- የባህል ኢንዱስትሪው እንዲጠናከር ለባህላዊ እሴቶች ጥበቃና እንክብካቤ እድገት ጥናትና ማስተዋወቅ ትኩረት ስጥቶ መሥራት፣
- በባህል ሙያ ዘርፎች የሙያ ደረጃና የምዘና መስፈርቶችን በማዘጋጀት ብቁ የባህል ባለሙያዎችን በማፍራት በዘርፉ የሚደረጉ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማበረታታት፣
- የባህል ተቋማትን እንዲስፋፉ መመሪያዎችን በማወጣት ለባህል ሙያ ተቋማት ደረጃ መስጠትና ሙያተኞችን ለማሳደግ ክልል አቀፍ የሽልማት ድርጅት ማቋቋም፣
- የባህል ተቋማትንና ማህብራትን ኢኮኖሚያዊ ተሣትፎና ተጠቃሚነት የሚጎለብትበትን የፖሊሲና የህጋዊ ማዕቀፎች ማሻሻልና አዳዲሶችን ማዘጋጀት፣
- ጠቃሚ የባህል እስቶችን በማጎልበት ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን በማስወገድ ረገድ በህብረተሰቡ ውስጥ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ፣

**የቱሪዝም ዘርፍ**

**የቱሪዝም ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች**

የቱሪዝም አቅጣጫዎች ለቱሪዝም ልማት ሊውሉ የሚችሉ የክልሉን ሰው ሰራሽ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ሀብቶች እንዲሁም የዱር እንስሳትና ሌሎች የተፈጥሮ ፀጋዎች በመለየት በግል በለሀብቱ ባካባቢው ህብረተሰብ ተሳትፎና በመንግስት ዕገዛ መሪነት ዘላቂ የቱሪዝም ልማት በማካሄድ ለክልሉና ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ገቢና ሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዎች መሰገኘት ነው።

**የቱሪዝም ዘርፍ ዓላማዎች**

የቱሪዝም ዘርፍ የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ ዓለማዎች በአለም አቀፍ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ፍክክር ውስጥ ተወዳዳሪ ሁኖ በመዝለቅ በተለይም በአፍሪካ ተመራጭ መዳረሻ ሆኖ መገኘት፣ ለክልሉና

ለአገሪቱ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ የኢኮኖሚ ጠቀሚታዎች በማሳደግ የክልሉንና የአገሪቱን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ የክልሉና የአገሪቱን መልካም ገጽታ የሚገነባ ኃላፊነት በተሞላበት አኳኋን የሴክተሩን ልማት በዘላቂነት የሚያስቀጥልና የህዝቡን ባህልና የአኗኗር ዘይቤ እንዲሁም የተፈጥሮ አካባቢያዊ ሁነቶች ሳያናጋ ማደግ የሚችል የቱሪዝም ኢንዱስትሪ መገንባት ናቸው።

**የቱሪዝም ዘርፍ ግቦች**

ቱሪዝም ሀብት ልማትን ማስፋፋት የሚከተሉት ግቦች ተቀምጠዋል

- በዕቅድ ዘመኑ የ8 ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎችን ደረጃ በማሻሻል እና በአዲስ የተለዩና የለሙ 11 መዳረሻዎች ለቱሪስት ክፍት በማድርግ የክልሉን የቱሪስት መዳረሻዎች ቁጥር 19 ማድርስ፣
- የተቋቋሙ የጥብቅ ሥፍራዎች ብዛት አሁን ያሉት 4 ሲሆኑ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 11 ማድርስ፣ በዚህም ባሉት ጥብቅ ስፍራዎች ያለውን የቀይ ቀበሮ ቁጥር ከ41 ወደ 80 ማሳደግ፣ በየዓመቱ 4 ጊዜ በጥብቅ ስፍራዎች የዱር እንስሳት በሽታ አሰሳና ቁጥጥር ማካሄድ
- ክልሉን የሚጎበኙ የውጭ አገር ቱሪስቶች ቁጥር ብዛት 86,000 የደረሰ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የውጭ አገር ቱሪስቶች ቁጥር 167,000 ማድረስ፣ እንዲሁም የሃገር ውስጥ ቱሪስት ቁጥር 708,000 የደረሰ ሲሆን ይህንን ቁጥር 1,916,000 ማድርስ፣
- የቱሪስት የቆይታ ጊዜ በአማካይ 10 ቀን የነበረ ሲሆን በአማካይ ወደ 15 ቀናት ከፍ ማድርግ ፣
- ከቱሪስት የሚገኘው ገቢ እስከ 2002ዓ.ም ድረስ 200 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን ፣ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች የተለያዩ ግቦችና ተግባራትን በመፈጸም ከቱሪስት የሚገኘውን ገቢ በ2007 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 800 ሚሊዮን ማድርስ፣
- በክልሉ ከተፈጠረው የሥራ ዕድል የቱሪዝም ድርሻ በመቶኛ ዝቅተኛ የነበረ ሲሆን ክልሉ ካለው ዕምቅ የቱሪስት ሃብት አንጻር ዘርፉን በማሳደግ፣ ከሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች ውስጥ 10% ድርሻ እንዲኖረው ማስቻል፣
- ደረጃ የተሰጣቸው የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ብዛት 10 ብቻ ሲሆኑ በዕቅድ ዘመኑ ውስጥ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ 1380 ማድረስ፣
- በክልሉ ደረጃ የወጣላቸው የኮንፈረንስ ቱሪዝም ከተሞች እሰከ አሁን ምንም ያለነበረ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ በክልሉ የሚገኙ 5 ከተሞችን በመምረጥ የኮንፈረንስ ቱሪዝም ከተሞች ማድረግ፤
- በቱሪዝም ልማት የሴቶች ተሳትፎ እስከ 2002 ዓ.ም 5 ሺህ ብቻ የነበረ ሲሆን በአምስት አመት ውስጥ ወደ 9,103 ከፍ ማድርግ ፣

**የቱሪዝም ዘርፍ የማስፈጸሚያ ስትርቴጂዎች**

- ነባርና አዳዲስ የቱሪዝም መስቦችንና ምርቶችን በዓይነትና በጥራት ማልማት፣
- ለቱሪዝም ልማት ወሳኝ የሆኑ የመሰረተ-ልማት አውታሮችንና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ማስፋፋት፣
- በዓለም አቀፍ የቱሪዘም ገብያ ፉክክር ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ጠንካራ የገብያ ትስስር በመፍጠር የማስታዋዎቅ ሥራ መስራት፣

- በቱሪዝም ልማት ውስጥ የሚሳተፉ ተዋናዮች መካከል ትብብራዊ ግንኙነት ማጠናከር፣
- በቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚታየውን የአቅም ውሱንነት ማስወገድ፣
- በክልሉ ውስጥ በዱር እንስሳት ይዞታቸው የተሻሉትን ወካይ ምህዳረ-ቀጠናዎችን መከለል፣ ቀደም ብለው የተቋቋሙትንም የጥበቃ ቦታዎች በባለድርሻዎች ተሣትፎ ከልሎ ህጋዊ ማድርግ፣ ህገ ወጥ የዱር እንስሳት ዝውውርን መግታት፣
- የዱር እንስሳትን ሃብት በዘላቂነት ለቱሪዝም፣ ለአደን፣ ለንግድ፣ ለእርባታና ለምግብነት በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል ክልሉም ሆነ አገሪቱ ከመስኩ የምታገኘውን ገቢ ማሳደግ፣
- በለሀብቱ በቱሪዝም ሃብቶች ላይ የጥበቃና እንክብካቢ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ በማበረታታት ዘርፉን ማሳደግ፣
- ህብረተሰቡን ስለ ዱር እንስሳት እና ሌሎች የቱሪዝም መስህብ ሃብቶች ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ላይ ያለውን ውቀት በማዳበር ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ማካሄድ፣
- የዱር እንስሳት እና ሌሎች የቱሪዝም መስህብ ሃብቶች ልማትና ጥበቃ የመረጃ አውታር በማቋቋምና በማደራጀት ጥቅም ላይ ማዋል፣

# ክፍል አምስት

## 5. የማህበራዊ ዘርፍ

## *5.1. ትምህርት*

### የትኩረት አቅጣጫ

- ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት አገልግሎትን ለሁሉም ለማደረስ በትምህርት መስክ የተቀመጡ የሚሊኒየም የልማት ግቦችን ለማሳካት የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ እንደቀጥልና ግቦቹም እንዲሳኩ ይደረጋል ።ዋናው ትኩረት የመደበኛ ትምህርት ጥራት ማሻሻል ላይ ይሆናል ። ይህንኑ ለማሳካት የተቀረጸው የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በመገምገምና በማሻሻል በይበልጥ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ስትራቴጅ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ ሰፊና ጥራቱን የጠበቀ ስርዓት እንዲሆን ይደረጋል። የሙያ ምደባ ምዘናና የካሪኩለም ቀረጻ ስርዓትን በመፍጠርና በማጠናከር ስርዓቱ የቀጣይ ቴክኖሎጅ ሽግግር መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ይደረጋል። የሙያና የቴክኒክ ማሰልጠኛ ተቋማት ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጅ ማእከላት ሆነው እንዲአገለግሉ ይደረጋል።
- የግሉ ዘርፍ ለወደፊቱም በትምህርት መስክ ጉልህ ሚና ያለው በመሆኑ ይህ እንዲቀጥል በተለይ ከትምህርት ጥራት የፖሊሲ አኳያ ተገቢው ክትትል ይደረጋል ፣
- በአጠቃላይ ትምህርት መስክ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማስፋፋት፣ ጥራቱን የጠበቀ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ ፍትሐዊና ተደራሽ የወጣቶችና የጉልማሶች ተግባር ተኮር የትምህርትና የሕይወት ክህሎት ፕሮግራም መዘርጋት እንደሁም በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል ያለው የትምህርት ተሳትፎ ልዩነት ማጥበብ እና በሁሉም ደረጀ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ በእቅድ ዘመኑ ትኩረት የሚሰጠው ጉደይ ነው። ይህንን ለማሳካትም የትምህርቱ ጥራት ማሻሻያ ፖኬጅ ተግባራዊ ይደረጋል ።
- ጥራቱን የጠበቀ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓት በመዘርጋት የመንግስት ኢንቨስትመንትን በማጠናከርና የትብብር ስልጠናን በተሟላ መልኩ ተግባሪዊ በማድረግ የአገሪቱን የሰለጠነ የሰው ሀይል ፍላገት እንዲሟላ ያደርጋል ። የሙያ ምደባ ዝግጅት ፣ የብቃት ማረጋገጫ ፣ የሙያ ምዘና የምስክር ወረቀት አሰጣጥና የካሪኩለም ቀረጻ ስርዓትን በመፍጠርና በማጠናከር ስርዓቱ የቀጣይ ቴክኖሎጅ ሽግግር መሳሪያ ሆኖ እንዲአገለግል ይደረጋል ። ከሙያ ቴክኒክ ማሰልጠኛ ተቋማት በተጨማሪ ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች የቴክኒክ ማዕከላት ሁነው እንዲያገለግሉ ይደረጋል። የግል ዘርፉ አስተዋጽኦ ከትምህርት ጥራት አኳያ እንዲሻሻል ተገቢው ክትትል ይደረጋል ።
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ስትራቴጅ አካቶ ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ ማዘጋጀት ፣ ለመምህራን ትምህርት ኘሮግራሞች በልዩ ፍላጉት ላይ ሙያዊ ድጋፍ መስጠትና የልዩ ፍላጉት ትምህርት መምህራንን በተጠናከረ ሁኔታ ማሰልጠን፣

የድጋፍ መስጫ ማእከላትን ማቋቋም፣ የዳሰሳና የመለያ መሳሪያ ማዘጋጅት እንደሁም ህብረተሰቡ በልዮ ፍላጎት ትምህርት ላይ ያለውን ግንዛቤና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ከትምህርት የተገለሉ ህጻናትን የትምህርት ተደራሽነት የማሳደግ ተግባራት ይከናወናሉ ።

## ዓላማዎች ግቦችና የማስፈጸሚያ ስትራቴጅዎች

## I. አጠቃላይ ትምህርት

**ዓላማ ፦** ዕድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ ሁሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በጥራት በማዳረስ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በጥራት በማስፋፋትና ገበያው የሚፈልገውን መካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይል በማፍራት፣ በሴቶችና በወንዶች፣ በገጠርና በከተማ መካከል ያለውን የትምህርት ተሳትፎ ልዩነት በማጥበብና ፍትሐዊነትን በማረጋገጥ እንዲሁም የጎልማሶች ትምህርትን በማስፋፋት የተማረ አምራች ዜጋ በመፍጠርና በክልሉ ልማት ተሳታፊ በማድረግ ድህነትን ማስወገድ ፡

### ዋና ዋና ግቦች

- **በሁሉም የአጠቃላይ ትምህርት እርከኖች**
  - የትምህርቱን ጥራት ለማስጠበቅ የወጡትን የትምህርት ጥራት ማስጠበቂያ ፓኬጆች ተግባራዊ በማድረግ አምራች ዜጋ መፍጠርና የትምህርቱን ተገቢነት ማረጋገጥ፦
    - የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ፓኬጅንና የምዕተ ዓመቱን ግብ አቀናጅቶ የሚመራና የሚያስፈጽም ክልላዊ የአመራር ኃይል በየደረጃው መፍጠር መቻል
    - በክልሉ ውስጥ ያሉ ምርጥ ተሞክሮች እየተቀመሩ፣ በሁሉም የክልላችን የትምህርት ተቋማት የሚተላለፍበት የማስፋት ሥርዓት ዘርግቶ ውጤታማ መሆን ክልላዊ የትምህርት አመራር ባህል መጀመር ማስቻል
    - ሁሉም ትምህርት ቤቶች አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችና ሳተላይት መማሪያ ክፍሎች ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ የትምህርት አካባቢ ማድረግ፣
    - በክልሉ በማስተማር ላይ ከተሰማሩት መምህራን በትምህርት ደረጃ ማሻሻያ ስልጠና ፕሮግራሞች በስፋት በማሳተፍ ተገቢው አካዳሚክ እውቀት፣ሙያዊ ስነ ምግባርና አውንታዊ አመለካከት ያላቸውን መምህራን ማፍራት ፣
    - በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣውን የሥርዓተ ትምህርት መነሻ በማድረግ ክልላዊ ስትራቴጂ ማዘጋጀትና መተግበር፤
    - የኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጅ ዋና ዋና ግብአቶች ተሟልተው ትምህርቱ በቴክኖሎጅ ተደግፎ በተጠናከረ መልኩ መስጠት፣
    - የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ሥርዓትን ማጠናከር፣

## ❖ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት/1-8/

- ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2001 ከነበረበት 98.4% ወደ 110% በማሳደግ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ዜጋ ማዳረስ፣
- ንጥር የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2001 ከነበረበት 89.4 ወደ 99 በመቶ በማድረስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ማዳረስ፣
- ንጥር ቅበላ በ2001 ካለበት 100% እስከ 2007 ዓ.ም ባለበት በማስቀጠል እድሜው ለትምህርት የደረሰ ሁሉ ትምህርት ቤት እንዲገባ ማድረግ ፣
- የሴቶችና ወንዶች ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ልዩነትን/GPI/ በመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል በ2001 ዓ.ም ካለበት 0.98 ወደ 1.0 በ ማድረስ ፍትሐዊነትን ማረጋገጥ፣
- በሁሉም የትምህርት ዓይነት የተማሪ መጽሐፍ ጥምርታን በ2002 ዓ.ም ካለበት 1፡2 ወደ 1፡1 ማድረስ፣ የሰለጠኑ መምህራን ድርሻ \1-4\ በ2002 ካለበት ከ2.2 ወደ 80 በመቶ ማሳደግ፣ የሰለጠኑ መምህራን ድርሻ\1-5\ በ2002 ካለበት ከ66.4 ወደ 100 % ማሳደግ የትምህርቱን ጥራት ማሳደግ ፣
- የተማሪ ማቋረጥ ምጣኔን በ2000 ካለበት 13.8 ወደ 3 በመቀነስ የትምህርት ብክነትን በመከላከል ለትምህርቱ ጥራት ማስጠበቂያ ማዋል ፣
- በ2002 የነበረውን 1፡50 የተማሪ ሴክሽንና 1፡50 የተማሪ መምህር ጥምርታዎች ባሉበት በማስቀጠል የትምህርቱን ብቃትና ጥራት ማሳደግ፣

## ❖ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

- ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2001 ከነበረበት 38.4 ወደ 60 በመቶ በማድረስ የትምህርት ሽፋኑን ማሳደግ ፣
- የሴቶችና ወንዶች ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ልዩነትን በ2001 ዓ.ም ካለበት 0.91 ወደ 1.0 በማድረስ ፍትሐዊነትን ማረጋገጥ፣
- በሁሉም የትምህርት ዓይነት የተማሪ መጽሐፍ ጥምርታን በ2002 ካለበት 1፡1 እስከ በ2007 ባለበት ማስቀጠል ፣
- በ2002 የነበረውን 1፡67 የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ ወደ 1፡40 እንዲሁም 1፡41 የነበረውን የተማሪ መምህር ጥምርታን ወደ 1፡40 ማድረስና የሰለጠኑ መምህራን ድርሻ በ2002 ካለበት ከ86.7 ወደ 100% በማሳደግ የትምህርቱን ጥራት ማሳደግ፣

## ❖ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

- የተማሪ ቁጥር በ2002 ካለበት ከ67,595 ወደ 120,000 በማድረስ ወደ ከፍተኛ ተቋማት የሚገቡ ወጣቶችን ቁጥር ማሳደግ ፣
- የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ በ2002 ካለበት ከ1፡54 ወደ 1፡40 ማድረስና የሰለጠኑ መምህራን ድርሻ በ2002 ካለበት ከ96.4 ወደ 100 % በማሳደግ የትምህርቱን ጥራት ማሳደግ
- የሴቶችን ድርሻ በ2002 ዓ.ም ካለበት 27.9 ወደ 35 በማድረስ ፍትሐዊነትን ማሳደግ፣

### ❖ የቅድመ መደበኛ ትምህርትና ተግባር ተኮር የጉልማሶች ትምህርት

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2002 ካለበት ከ1.82% ወደ 20% በማሳደግ ለትምህርቱ ጥራት አስተዋጽኦ ማድረግ፤
- የተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት /ከ15-64 ዓመት ያለውን ጎልማሳ ያካተተ /ተሳትፎ ቁጥር በ2002 ካለበት ከ107,769 ወደ 8540244 በማሳደግ የተማረ ዜጋ መፍጠርና ልማቱን ማፋጠን ፣

## የማስፈፀሚያ ስትራተጂዎች

### ሀ \ቅድመ መደበኛ

- የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ማስፋፋት ፣
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት የፖሊሲ ማእቀፍ ስትራቴጂዎችና ሥርዓተ ትምህርቱን ተግባራዊነት ማረጋገጥ ፣
- ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ተማሪዎች ስታንደርድ ማውጣትና በስታንዳርዱ መሠረት መጫዎቻና መማሪያ ማቴሪያሎች እንዲሟሉ ማድረግ፣
- ለቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ስልጠና ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ፣

### ለ\ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት\1-8\

- አደሱን ስርዓተ ትምህርት ተግባራዊ ማድረግና የመማሪያ መጽሐፍትና የመምህር መምሪያዎች በበቂ ሁኔታ በወቅቱ ለትምህርት ቤት ማሠራጨት
- የትምህርት ቤቶች ቅርበት እርስ በርስ ትስስር ማጠናከር በትምህርት ቤቶችና በተማሪዎች መኖሪያ መካከል ያለውን ርቀት መቀነስ፣
- በሥራ ላይ የሚገኙትን የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማእከላት ወደ መደበኛ የመጀመሪያ ደረጅ ትምህርት ቤቶች ማሳደግና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ተጨማሪ ማዕከላትን መክፈት እና በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላትና በመደበኛ ትምህርት ቤቶች መካከል ጠንካራ የሽግግርና ትስስር ስርዓት መፍጠር፣
- ክልላዊ ብሔራዊ ፈተናዎችንና የትምህርት ቅበላ ጥናቶችን ከአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ጋር በማጣጣም ማካሄድ፣
- የተማሪዎችን የሳይናንስና ሂሳብ ትምህርት ችሎታ ለማሳደግ የሳይንስ ትምህርቶች ስትራቴጂ መተግበር፣
- የመጀመሪያ ደረጃ መምህራንና የትምህርት አመራር ባለሙያዎችን የትምህርት ደረጃ ማሳደግ፣
- የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎና ትምህርታቸውን ተከታትለው የማጠናቀቅ ምጣኔ ለማሳደግ በሚደረጉ እርምጃዎች ትምህርት ቤቶች ተጠያቂ የሚያደርግ ስርዓት መዘርጋት፣
- የሴት መመህራንና የሴት አመራር ባለሙያዎችን ቁጥር መጨመርና ለሴት ተማሪዎች ተሳትፎ መጨመር በሞዴልነት እንዲሠሩ ማበረታታት፣
- የልዩ ፍላጎት ትምህርትን ማጠናከር

## ሐ . የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

- የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትም/ መሰናዶ ትምህርትን ማስፋፋት ፣
- ለሴት ተማሪዎችና ለገጠር ወጣቶች ትኩረት የሚሰጥ ፍትሐዊ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ማስፋፋት ፣
- በ3 አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማካይ እርቀት ላይ አንድ ሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ቤት በመክፈት እንዲሁም በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቅጥር ግቢ የ2ኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ክፍሎችን በመክፈት ርቀትን መቀነስና የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎን ማሳደግ ፣
- ለተጋላጭ ወጣቶች የስኮላርሽፕ ልዩ ድጋፍ መሰጠት፣
- የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ሴት ተማሪዎች ተሳትፎንና ትምህርታቸውን ሳያቋርጡ የማጠናቀቅ ምጣኔ ለማሳደግ ትምህርት ቤቶችን መሰረት ያደረገ የተጠያቂነት ስርዓትና ስታንዳርድ መዘርጋት፣
- የግል ባለሀብቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበረሰቡ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እንዲከፍቱ ማበረታታትና ድጋፍ መስጠት፣
- መምህራን የትምህርት አመራር ባለሙያዎችን የአፈጻጸም አቅምና ብቃት እንዲሁም የትምህርት ደረጃ በቅድመ ሥራና ሥራ ላይ ትምህርትና ስልጠና ማሳደግ፣ የመምህርነት የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና የሙያ ፈቃድ እድሳት ስርዓትን መዘርጋት፣ ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራምን አጠናክሮ መቀጠል ፣
- የተማሪዎችን የሳይንስና ሂሳብ ችሎታ ለማሳደግ የሳይንሰና ሂሳብ ትምህርቶች ስትራቴጂን ለመተግበር ፣
- የትምህርት አመራር መረጃ ሥርዓት እና የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ማሻሻልና ማጠናከር ፣
- ለመማር አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ቤት ግብዓቶችን በስታንዳርዱ መሠረት ማሟላትና ምቹ የትምህርት አካባቢ መፍጠር ፣

## መ. የጎልማሶች ትምህርት

- ለጎልማሶች ተግባር ተኮር ትምህርት ፕሮግራም ተግባራዊነት ሰፊ የአህዝቦት ስራ በመስራት የማህበረሰብ ንቅናቄ በማካሄድ የህዝብ ባለቤትነት ስሜት መፍጠር ፣
- የጎልማሶችን ፍላጎት፣ ተሞክሮና እውቀት መሠረት ያደረገ የጎልማሶች ስርዓት ትምህርት መተግበር ፣
- የተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት አመቻቾች፣ ሱፐርቫይዘሮችንና የጎልማሶች ጉዳይ ፈጻሚ አቅም መገንባት ፣
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቅንጅት በመፍጠር የጎልማሶች ትምህርት ዘላቂነትን ማረጋገጥ ፣

## II. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በሚመለከት

### ዓላማ፣ ግቦችና የማስፈጸሚያ ስትራቴጅዎች

**ዓላማ ፦** የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን በብቃት ለመምራት ተገቢውን ተቋማዊ አደረጃጀትና አስፈላጊውን የሰው ሃይል አቅም በመገንባት ፣ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ የፋይናንስ ስርዓትና የሥራ አመራር መዋቅር በመዘርጋት፣ የትምህርቱን ጥራት በማሻሻልና ከገበያው ፍላጉት ጋር በማጣጣም ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል የሚሆኑበትን አሰራር በማጠናከር ሴቶችንና የገጠሩን ነዋሪ ህዝብ የሙያ ክህሎት ባለቤት በማድረግ አምራችና ሥራ ፈጣሪ ዜጋ በማፍራት ልማቱን ማፋጠን ።

### ዋና ዋና ግቦች ፦

- የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ብዛት በ2002 ከነበረበት 62 በ2007 ዓም ወደ 130 ፣ የግል ቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ከ47 ወደ 72 ፣ የፖሊ ቴክኒክ ተቋማትን ምንም ካልነበረበት በ2003 በጀት ዓመት 12 ተቋማት አገልግሎት እንደሰጡ ማድረግና በ2007 ቁጥራቸውን ወደ 18 በማሳደግ የቴክኒክና ሙያ አቅርቦትን በክልሉ ማስፋት፣
- ዓመታዊ የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት የተማሪ ቅበላ በ2002 ከነበረበት 86,922 በ2007 ዓም ወደ 382,188 ማድረስ፣ የግል ተቋማት ቅበላን ከ30,807 ወደ 88,126 በማሳደግ የተጠቃሚውን ፍላጎት ማርካት፣
- በመንግስት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት የመምህራንን ብዛት በ2002 በጀት ዓመት ካለበት 2489 ወደ 4054 በማድረስ የትምህርቱን ጥራት ማሳደግ፣
- የሙያ ብቃት ምዘና አልፈው የምስክር ወረቀት የሚያገኙ ከመንግስት ቴክኒክና ሙያ የዓመቱ ተመራቂ ሰልጣኞች ቁጥር በ2002 ካለበት 20% በ2007 ዓ.ም ወደ በ75% ማሳደግና የግል ቴክኒክና ሙያ የዓመቱ ተመራቂ ሰልጣኝ ቁጥር በ2002 ካለበት18% በ2007 ወደ 68% ማሳደግ፣
- ዕውቅና የተሰጣቸው የመንግስት የምዘና ማዕከላትን ቁጥር አሁን ካለው 11 በ2007 ዓም ወደ 65 ማድረስ፣ ከኢንዱስትሪው ዕውቅና የተሰጣቸው የምዘና ማዕከላትን ብዛት አሁን ካለው 16 በ2007 ወደ 137 ማድረስ፣
- ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ የመንግስት ቴ/ሙ/ተቋማትን ከ26 ወደ 130 ፣ እንዲሁም የግል ተቋማትን ከ47 ወደ 72 ከፍ ማድረግ ፣
- በመንግስት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከተመረቁት ውስጥ በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው ሆነ በቅጥር ስራ የሚፈጥሩ ሠራተኞች በ2002 ከነበረው 9 % ወደ 56% በማድረስ አምራች ዜጋ ማድረግ፣
- ቴክኖሎጅዎችን ለማሸጋገር የሰለጠኑ አባዥዎች ብዛት 12,000 ወደ 39,908 እንዲሁም የተዘጋጀው ቴክኖሎጅ ተጠቃሚ የሆነውን የህዝብ ብዛት ቁጥር ከ50,000 ወደ 2,122,500 በማሳደግ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ፣

- ከመንግስት ቴ/ሙ/ተቋማት ውሰጥ በቅጥር ወይም ስራ ከፈጠሩት ውሰጥ ከ10 ሺ.ህ- 50ሺ.ህ ብር ካፒታል የፈጠሩ በ2002 ከነበረው 291 ምሩቃን በ2007 ወደ 19,149፣ ከብር 50ሺ.ህ-100 ሺ.ህ በ2002 ከነበረው 112 ወደ 7,365 እንዲሁም ከብር 100ሺ.ህ በላይ ከ23 ወደ 1,473 ምሩቃን ማድረስ፣
- በግል ተቋማት ከሰለጠኑት ተመራቂዎች ውሰጥ በሰለጠኑበት ሙያ ወደ ስራ የተሰማሩ በመቶኛ በ2002 ከነበረው ከ0% ወደ 70% ማድረስ፣
- በትብብር ስልጠና ያለፉትና የተደገፉ ሰልጣኞች በመቶኛ በ2002 ከነበረው 40% በ2007 ወደ 100% ማሳደግ

## የማስፈፀሚያ ስትራቴጅዎች

- ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል በማድረግ ማጠናከር፣
- ተቋማት በሙያ ደረጃዎች መሰረት ሥልጠና መስጠት በሚችሉበት ደረጃ ለማብቃት የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት መዘርጋት፣ ተገቢውን ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠርና በመምህራን ዘንድ የታዩ ክፍተቶችን በማጥናት ስልጠና ማካሄድ፣
- የሰልጠና ገበያ ፍላጎት ጥናት ስርዓት መዘርጋትና በየጊዜው የሙያ ደረጃዎችን ማሻሻልና ሰልጠናዎችን ማካሄድ ፣
- ሁሉም ባለድርሻዎች የቴ/ሙ /ት/ስልጠና ስርዓት ትምህርት ቀረጻ ፣ በስልጠናና በምዘና ተግባራት ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉበትን አሰራር ማጠናከር ፣
- የሴቶችንና የገጠሩን ነዋሪ ህዝብ ማዕከል ያደርጉና ተፈላጊ የሆኑ ሙያዎችን በመለየት ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸትና የሴቶችን አቅም በማጎልበት በቴክኒክና ሙያ አሰልጣኝነትና ማኔጅመንት ላይ ያላቸውን ድርሻ ማጎልበት ፣
- ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ሴክተሮች ልዩ ትኩረት መስጠትና የግል የቴ/ሙ/ት/ስልጠና ተቋማትን ማገዝ ፣
- የቴ/ሙ/ት/ስልጠና ማኔጅመንት ላይ የህብረተሰቡ ተሳትፎ መኖሩን ማረጋገጥ፣ አማካሪ ቦርድን ማቋቋምና ማጠናከር፣
- የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን መጠቀም ፣ የወጪ መጋራትን ሲስተም በመፍጠር መተግበርና የስልጠና ማቴሪያሎችን ውጤታማ በሆነ መልኩ መጠቀም ፣
- የቴ/ሙ/ት/ስልጠና ከስራ ቦታና ሁኔታ ጋር የሚጣጣምበት መንገድ ማመቻቸትና የትብብር ስልጠናን ማጠናከር ፣

# 5.2. ጤና ጥበቃ

## የትኩረት አቅጣጫዎች

- የመሠረተ ጤና አገልግሎት በሁሉም ገጠሮችና ከተሞች እንዲዳረስ ይደረጋል ፡፡በዚህ ላይ በመመስረት የህዝቡን የጤና ደረጃ ለማሻሻልና ግቦቻችንን ለማሳካት ፣ የሕ/ተሰቡን የተደራጀ

ተሳትፎ ማዕከል በማድረግ የመሰረተ ጤና አገልግሎት ስርዓት ጥራት ይሻሻላል፡፡ ተቋሞቹ በሰው ኃይልና በቁሳቁስ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት መጠናከራቸው በማረጋገጥ እና የስርዓቱን አሰራርና አደረጃጀት በየጊዜው በማሻሻል ከህዝቡ በሽታን የመከላከል እንቅስቃሴ ጋር ተቀናጅቶ እንደሄድ ይደረጋል ፡፡

- የጤና ኬላዎችና የጤና ጣቢያዎችን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ለሁሉም ማዳረስ ፣ በሆስፒታል ላይ የተመሰረተ የህክምና አገልግሎትን ለማስፋፋትና የአገልግሎት ጥራቱን ለመጠበቅም እርምጃ ይወስዳል ፡፡ ዘመናዊ የሕክምና አገልግሎት ፋይናንስ ስርዓትን ለመጀመርና በሂደትም በይበልጥ ለማጠናከር የሚያስችሉ እርጃዎችም ይወሰዳሉ ፡፡
- የግሉ ዘርፍ በጤናው መስክ የሚጫወተውን ገንቢ ሚና ይበልጥ እንዲጠናከር ይደረጋል ፡፡ በዚህ መሠረት የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ የግል ተቋማት አገልግሎታቸው ሁሉንም ወገኖች የሚያረካ ተገቢ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል ፡፡ ጥራቱ ተወዳዳሪ የሆነ የሆስፒታል አገልግሎት እንዲስፋፋ ማድረግ የሚበረታታ ይሆናል ፡፡

### ዓላማዎች፣ ግቦችና የማስፈጸሚያ ስትራቴጅዎች

**ዓላማ ፦** የህጻናት ሞትን በመቀነስ፣ የእናቶችን ጤና በማሻሻል ፣ እንደ ኤች አይ ቪ ኤድስ ፣ወባና ቲቢ የመሳሰሉተን ተላላፊ በሽታዎችን ስርጭት በመቀልበስ ጤናማና አምራች ዜጋ በመፍጠር የክልሉን ልማት ማፋጠንና የምዕተ ዓመቱን ግቦች ማሳካት ።

**ዋና ዋና ግቦች ፦**

❖ ***የጤና መሰረተ ልማትን ማሻሻል /መሠረታዊ የጤና አገልግሎት/***

- የጤና ጣቢያዎችን ቁጥር በ2002 ዓ.ም ከነበረበት 520 ወደ 820 በማድረስ የተጠቃሚውን ቁጥር ከ63 በመቶ ወደ 100 በመቶ ከፍ ማድረግ
- የገጠር ሆሲፒታሎችን ቁጥር ከ10 ወደ 44 እንዲሁም የሪፈራል ሆስፒታሎችን ቁጥር ከ 3 ወደ 6 ማሳደግ
- በክልሉ 30 አጠቃላይ ሆስፒታሎችን በመገንባት በህክምና መሳሪያዎች ማደራጀትና አገልግሎት ማስጀመር።
- የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎችን ቁጥር **ከ0% ወደ 100% ድረስ** በማደራጀት ተጠቃሚዉን ህብረተሰብ 1፡100,000 ጥምርታ ማረጋገጥ።

❖ **የጤና ኤክስቴንሽን**

- 1293 የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ማሰማራትና አቅማቸውን ማሳደግ
- የጤና ኬላዎችን ቁጥር በ2002 ከነበረበት 2941 ወደ 3978 በማድረስ የተጠቃሚውን ቁጥር ከ93% ወደ 100% ከፍ ማድረግ
- የመፀዳጃ ቤት ሽፋንን ከ2002 ከነበረው 86% ወደ 100% እና የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀምን በ2002 ከነበረው 36% ወደ100% ማድረስ፤
- በጤና ኤክስቴንሽን የተመረቁ አባወራዎች አሁን ካለበት 68% ወደ 100% ማድረስ

❖ **የእናቶችና ህጻናት ጤና አገልግሎት**

- በህይወት ከሚወልዱ 100ሺ እናቶች የሚደርሰዉን የእናቶች ሞት ቁጥር አሁን ካለበት 590 ወደ 260 መቀነስ።
- የጨቅላ ህጻናት ሞት በ2002 ከነበረበት 39/1000 በ2007 ወደ 15/1000 መቀነስ
- የወሊድ መቆጣጠሪያ አቅርቦት በ2002 ከነበረበት 23 በመቶ በ2007 ወደ 100 በመቶ ማድረስ
- የቅድመ ወሊድ አገልግሎትን አሁን ካለበት 67% ወደ 95% ከፍ ማድረግ።
- በሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎች የሚሰጥ የወሊድ አገልግሎት አሁን ካለበት 25% ወደ 80% ማድረስ።
- የድህረ ወሊድ አገልግሎትን አሁን ካለበት ከ38% % ወደ 90% ማድረስ።
- 8,638 አዋላጅ ነርሶችን አሰልጥኖ በማስማራትና የእናቶችን ሞት መቀነስ
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚን ከ32% ወደ 75% ማሳደግ
- ከ1 ዓመት በታች የህፃናት ሞትን በህይወት ከሚወለዱ 1000 ህፃናት ዉስጥ ከ77 ወደ 31 መቀነስ።
- ከ5 ዓመት በታች የህፃናት ሞት ምጣኔ በ1 ሺ አሁን ካለበት 101 ወደ 67% ዝቅ ማድረግ፤
- የፔንታ3 የህፃናት ክትባት ሽፋንን አሁን ካለበት 81% ወደ 95 % ከፍ ማድረግ፣
- የኩፍኝ ክትባትን አሁን ካለበት 80% ወደ 95% ከፍ ማድረግ።
- ክትባት የጨረሱ ህፃናትን ሽፋን አሁን ካለበት 70% ወደ 85% ከፍ ማድረግ።

❖ **ተላላፊ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር**

- ለ169,600 ኤች አይ ቪ /ኤድስ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ፀረ ቫይረስ መድሐኒት መስጠት
- በየቤታቸው ሁለት የወባ መከላከያ አጎበር የሚጠቀሙ ቤተሰቦችን 100% ሽፋን ማቆየት
- የሳንባ ነቀርሳ በምርመራ የማግኘት አቅም በ2002 ከነበረበት 27% ወደ 70% **ማድረስ**
- ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፈዉን ኤችአይቪ ኤድስ ለመከላከል መድሃኒት የሚጀምሩ እናቶችን አሁን ካለበት 8% ወደ 77% ማድረስ።
- በጤና ተቋማት በላቦራቶሪ የሚረጋገጡ የወባ ህሙማንን ቁጥር አሁን ከሚገኝበት ከ35% ወደ 4% ዝቅ ማድረግ።
- የኤአርቲ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ቁጥር አሁን ካለበት 127 ወደ 261 ከፍ ማድረግ

**የማስፈጸሚያ ስልቶች**

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን አጠናክሮ መቀጠል ፣
- የጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች በመገንባት ፣በመስፋፋት፣ በማጠናከር፣ እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በማካተት ጥራቱን የጠበቀ ተወዳዳሪ የሆነ የህክምና አገልገሎት ለሕብረተሰቡ ማዳረስ፣

- ጠቅላላ ሐኪሞች ፣ የጤናመኮንኖች፣ አዋላጅ ነርሶችን አሰልጥኖ በማሰማራት በሁሉም ጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች ጥራቱን የጠበቀ የድንገተኛ ቀዶ ጥገና ህክምና መስጠት፣
- የግሉ ዘርፍ በጤናው መስክ የሚጫወተውን ገንቢ ሚና ማጠናከር፣
- የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓተ ላይ የጥራት ቁጥጥር ማድረግ ፣
- የመድሐኒቶችና ሌሎች የህክምና ቁሳቁሶች ማምረቻ ተቋሞች በክልላችን እንዲስፋፉ አስፈላጊው ማበረታቻና ማትጊያ ይሰጣል ፣
- ለጤናው ዘርፍ የሚያስፈልገው ፋይናንስ ከመንግስት፣ በቀጥታ ከተጠቃሚዎች በአገልግሎት ወቅት ከሚሰበሰብ ክፍያ ፣ ከልማት አጋሮች እና ከጤና መድን ምንጮች ይሸፈናል ፡፡ ከማህበራዊ የጤና መድን ጎን ለጎን በገጠሩና በከተማው መደበኛ ባልሆነ ክፍለ ኢኮኖሚ የተሰማራውን የህብረተሰብ ክፍል ያቀፈ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድን መተግበር ፡፡
- ዘጠና በመቶ ለሚሆነው የሕጻናት ሞት አስተዋጽኦ በሚያደርጉ ዋና ዋና በሽታዎች /የሳምባ ምች ፣ ወባ፣ ተቅማጥ...ወዘተ /ላይ ያተኮረ ሥራ መስራት ፣
- ጤናማ እርግዝና እና ወሊድ እንዲኖር ፣ የቤተሰብ ምጣኔ አቅርቦትና አጠቃቀም በማስፋፋት ከስነተዋልዶ ጋር የተያያዙ ህመሞችን እና ለሞት የሚያበቁ በሽታዎችን መቆጣጠር
- በተለያዩ ተቋማት የሚሰጠውን የጤና አገልግሎትና አቅርቦት መወሰን፣
- በሁሉም ወረዳዎች የህብረተሰብ አቀፍ የሥርዓተ ምግብ አገልግሎት መስጠት፣
- ጥራቱን የጠበቀና ደረጃው የተሟላ የጤና አገልግሎት አቅርቦት እንዲኖር በማስቻል የጤናው ዘርፍ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ብቃት ያለውና ስብጥሩን የጠበቀ የሰው ሀብት እንዲኖር ማድረግ፣
- የግል ባለሀብቶች ጋር በተቀናጀ መልክ በመስራት ሕብረተሰቡ ጥራትና ብቃት ያለው የጤና ባለሙያ ስልጥናና አገልግሎት የሚያገኝበት ሁናቴ የማመቻቸትና የመፍጠር ስራዎች ይሰራሉ፣
- የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍልሰትን ለመቀነስና ጥራት ያለው አገልግሎት ለህ/ተሰቡ ለማዳረስ የባለሙያ ማበረታቻ የሚያገኙባቸው መንገዶች ማመቻቸት ፣ የፕራይቬት ዊንግ በማቋቋም ባለሙያዎችን ማበረታታት እንዲሁም በገጠር አካባቢ ለሚሰሩ ባለሙያዎች የተለየ ትኩረት መስጠት የሚሉት የሚጠቀሱ ናቸው ፡፡

## 5.3. ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ

### የትኩረት አቅጣጫዎች

በሚቀጥሉት አምስት አመታት ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች:-

አረጋውያን በዕድሜያቸው ያካበቷቸውን ልምዶችና እውቀቶች ለክልሉ ልማትና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እንዲያውሉት ለማድረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ አረጋውያን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነታቸው እንዲሁም ጤንነታቸው እንዲጠበቅ የሚያስችሉ የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎቶች ከሚሰጡ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣ በህብረተሰቡ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና

*ማህበራት የሚሰጡ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ማስፋፋት፣ አካል ጉዳተኞች ችሎታቸውን በመጠቀም በክልሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሳተፉ ማበረታታት፣ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው በፈጠረው አመች ሁኔታ ከትምህርት የተገለሉትንና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህፃናት የትምህርት እድል ለመስጠትና ከዚህም አኳያ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የተቀረጸው የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጅ ተግባራዊ ማድረግ፣ አካል ጉዳተኞች ከሌሎች ጋር በእኩል በስራ ላይ መቀጠር መብታቸውን በማረጋገጥ ከኢኮኖሚው እድገት ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ በስራና በመኖሪያ አካባቢ፣ በመዝናኛ ስፍራዎች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በጤና ተቋማት እንዲሁም በሌሎችም ስፍራዎች የአካል ጉዳተኞችን እንቅስቃሴ የሚገድቡ መሰናክሎችን ማስወገድ እንዲሁም አዳዲስ ግንባታዎች የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ ግምት ውስጥ ያስገቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚሉት ናቸው።*

**ዓላማዎች**

*የአምስት ዓመቱ የዘርፉ እቅድ አላማዎች የማስፈፀም አቅምን ማሳደግ፣ ደህንነቱና ጤንነቱ የተጠበቀ የስራ አካባቢ መፍጠር፣ የአሰሪና ሠራተኛ መብቶችና ግዴታዎች እንዲከበሩ ማድረግ፣ የስራ ስምሪት አገልግሎትን ማስፋፋት፣ የማህበራዊ ችግሮችንና መንስኤዎችን በመከላከልና በሙብት ጥሰቶች ላይ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ የህብረተሰቡን ማህበራዊ ደህንነት መጠበቅ፣ በማህበራዊ ችግሮች ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል እንዲሁም የማህበራዊ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸውን በጥናት በመለየት የሚተገበሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት የሚሉት ናቸው።*

**ግቦች**

- ✓ በ610 ድርጅቶች የሙያ ደህንነት ጤንነትና የስራ አካባቢ አጠባበቅ ስልጠና በመስጠት የሥራ ላይ አደጋንና የሙያ በሽታን መከላከል፣ በ559 ድርጅቶች 143 የሴፍቲኔት ኮሚቴ ማቋቋምና 416 ኮሚቴዎችን በማጠናከር ጤንነቱ የተጠበቀ የስራ አካባቢ መፍጠር
- ✓ በክልሉ በሚገኙ ድርጅቶች የስራ ቦታዎች ላይ 32,570 የሙያ ደህንነት፣ ጤንነትና የስራ አጠባበቅ እንዲሁም ለ23,254 የመሠረታዊ ስራ ሁኔታዎች የመጀመሪያ፣ የመከታተያ እና አቤቱታ ቁጥጥሮች በማካሄድ የተፈጻሚነት ደረጃቸውን አሁን ካለው እንደቅደም ተከተላቸው 74.4 በመቶ ወደ 90 በመቶ እና ከ64 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሳደግ
- ✓ በክልል ደረጃ 1 የሙያ ደህንነት፣ ጤንነትና የስራ አካባቢ አጠባበቅ ቤተ ሙከራ በማደራጀት በቤተ ሙከራው የሚገኙ ውጤቶችን በመቀመር ለተጠቃሚዎች ምቹ ሁኔታን መፍጠር
- ✓ በዕቅድ ዘመኑ በ615 ድርጅቶች የሁለትዮሽ የማህበራዊ የምክክር ባህልን በማጎልበት አለመግባባቶችን በሠላም መንገድ እንዲፈቱ በማስቻል ባህሉ ደረጃ በደረጃ የሚጎለብትበትን ሁኔታ መፍጠር
- ✓ እስከ 2007 መጨረሻ 9,0988 አሠሪዎች፣ ሠራተኞችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ዙሪያ ግንዛቤያቸውን በማሳደግ የግንዛቤ ክፍተቶችን ማጥበብ

- ✓ በዕቅድ ዘመኑ 110 አዲስ የሠራተኛና 20 የአሰሪ ማህበራት እንዲቋቋሙ፣ 126 ነባር የሠራተኛና 9 የአሰሪ ማህበራት እንዲጠናከሩ እና 93 አዲስ የህብረት ስምምነቶች እንዲመዘገቡና የስራ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ 120 የህብረት ስምምነቶች እንዲታደሱ በማድረግ በማህበር የመደራጀት ነጻነትና የህብረት ድርድር የማድረግ መብት እንዲከበር ማስቻል
- ✓ የሰው ኃይል ፍላጎት ጥናቶችን በማካሄድና ለ55,620 ሥራ ፈላጊዎች የስራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ለ240,128 ስራ ፈላጊዎች የምክርና አመራር አገልግሎት በመስጠት የክልሉን የሥራ አጥነት ችግር ማቃለል
- ✓ የወጡ አዋጆች፣ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎች፣ የድርጊት መርሀ ግብሮችና ኮንቬንሽኖች ተግባራዊነታቸውን ማረጋገጥና ለ2,364,594 ህብረተሰብ ለ23,040 የአመራር አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በመስጠት የህብረተሰቡን ማህበራዊ ደህንነት ማስጠበቅ
- ✓ በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ከሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ 11,236 የማቋቋም፣ 207,240 የድጋፍና እንክብካቤ እንዲሁም 60,789 የአካል ተሐድሶና የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ኑሮአቸውን ማሻሻል
- ✓ በዕቅድ ዘመኑ 11,355 አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞችና ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት ማህበራት እና የእድር አመራሮች ስልጠና በመስጠት የአመራር አቅማቸውን ማሳደግ
- ✓ በዕቅድ ዘመኑ የልማት ቀጠናዎችን መሰረት ያደረጉ 10 ጥናቶችን በማካሄድ ማህበራዊ ችግር ፈች እንዲሆኑ ማድረግ
- ✓ በዞን ተጠሪ ጽ/ቤቶችና በሜትሮፖሊታን ከተሞች 13 የመረጃ ማዕከል በማደራጀት ለመረጃ ፈላጊዎች ፈጣን አገልግሎት መስጠት
- ✓ ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ህፃናት፣ አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች ማህበራት፣ OVC ግብረሃይልና CRC ኮሚቴ በማቋቋምና በማጠናከር መብቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን ማስከበር

**የማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ➢ የማህበራዊ ደህንነት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶችን ለማጠናከር ህብረተሰቡን ማሳተፍ
- ➢ በማህበራዊ ደህንነት ልማት ዘርፍ በባለድርሻ አካላት መካከል ትብብርና ቅንጅት መፍጠር
- ➢ የማህበራዊ ደህንነትን በተመለከተ ጥናትና ምርምር ማካሄድ
- ➢ የማህበራዊ ደህንነት ጉዳይ የሚመለከታቸውን አካላት አቅም መገንባት
- ➢ የህብረተሰቡን ዕውቀትና ግንዛቤ ለማሳደግ የመረጃና ትምህርት አገልግሎቶችን ማስፋፋትና የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ማከናወን

# ክፍል ስድስት

## 6. አቅም ግንባታና መልካም አስተዳደር

### 6.1. አቅም ግንባታ

**የትኩረት አቅጣጫዎች**

*የአቅም ግንባታ ዘርፍ ቀጣይ የአምስት ዓመታት እቅድ ዝግጅት መነሻ ሀገራዊ ራእያችንን ለማሳካት በሀገር ደረጃ የታለሙ ግቦችና ዓላማዎች፤ እንዲሁም በሚቀጥሉት አምስት አመታት እንዲሳኩ የሚፈለጉ ዓላማዎችና በግምገማው የተለዩ ክፍተቶች በሙሉ የእቅድ መሠረታዊ መሻዎች ናቸው። ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገትን በማረጋገጥ ማህበራዊ ልማትን በማፋጠንና ዲሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግስት እውን በማድረግ ረገድ አበረታች ሥራዎች መከናወናቸው የሚታወስ ነው። በቀጣይም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማትን እውን ለማድረግ በታሳቢነት የተያዙትን የክልሉን ዋና ዋና ዓላማዎች መሰረት በማድረግ የቀጣዩ አምስት ዓመት* /2003-2007/ *የልማት እቅድ አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-*

**ሀ/ ጠንካራ የማስፈፀም አቅም ያለው መንግስታዊ መዋቅር መፍጠር**

*በመተግበር ላይ ያለው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች በተሟላ መልኩ እንዲተገበርና ለውጡ ስር እንዲሰድ ማድረግ፣ ሲቪል ሰርቪሱን በሰው ሃይል በመገንባት በአመለካከት፣ በእውቀትና በክህሎት የመንግስትን ፖሊሲና ስትራቴጂዎች በበቃት መፈጸም የሚችልና የሕዝብ አገልጋይ የሆነ የልማት ሰራዊት መፍጠር፣ ለውጡ ውጤታማነትንና ቅልጥፍናን ያረጋገጠ እንዲሁም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ያሰፈነ ማድረግ፣ የመንግስት ሠራተኞች የተሰጣቸውን የሥራ ሃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ቀጣይ ሥልጠናና የምክር አገልግሎት መስጠት፣ የተቋማትን የማስፈፀም አቅም በማጐልበት ሂደት ለቀጣይ እርምጃ የሚያገለግሉ በሥራ አመራር ዙሪያ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን የተገኙ ውጤቶችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮ በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲስፋፉ ማድረግ፣ በአፈጻጸም ውጤታማነትንና ቅልጥፍናን ያረጋገጠ መንግስታዊ አገልግሎት እንዲሰፍን የውጤት ተኮር ሥርዓትን* /BSC/ *በኮሙኒኬሽን ሥራዎች ደግፎ መዘርጋት ጠንካራ የማስፈፀም አቅም ያለው መንግስታዊ መዋቅር ከመፍጠር አኳያ በትኩረት የሚሠራባቸው ይሆናሉ።*

**ለ/ ግልጽነትን ማስፈንና ሙስናን ከምንጩ ማድረቅ**

*የግብር ሥርዓቱን በማሻሻልና ይህንኑ በመጠቀም የማንኛውም ዜጋ ገቢና ንብረት በወቅቱና በትክክል የሚታወቅበት ሕጋዊ እውቅናና ጥበቃ የሚያገኝበት ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት እንዲፈጠር ማድረግ፣ የከተማ መሬት በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት የሚመዘገብበትና የሚታወቅበት፣ በመሬቱ ላይ ማን ምን መብት እንዳለው የተሟላና ወቅታዊ መረጃና ሕጋዊ እውቅና የሚሰጥበት ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ፣ ሙስናንና ኪራይ ሰብሳቢነትን ከምንጩ ለማድረቅ ዜጐች ሙስናንና ኪራይ ሰብሳቢነትን እንዲጠየፉ የተቀናጀ የስነ ዜጋና ስነ-ምግባር ትምህርት ላይ በሰፊው እነዲሰራ ማድረግ፣ ግልጽነት በሰፈነበት*

ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ማእቀፍ በየደረጃው ያሉ የፖለቲካ መሪዎች ገቢያቸውና ንብረታቸው እንዲመዘገብና እንዲታወቅ፣ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ገቢም ሆነ ንብረት ቢገኝባቸው አጣርቶ ለሕግ የማቅረብና የማስተማር ሥራ በተጠናከረ መልኩ እንዲካሄድ ማድረግ፣ ማንኛውም ዜጋ ሕጋዊ ያልሆነ ገቢን ወይም ንብረትን የማግኘት ስራ ሲሰራ፣ ተገቢውን ግብርና ቀረጥ ሳይከፍል ሲቀር፣ ተገቢ ያልበሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲንቀሳቀስ ቢገኝ ህግን መሠረት ያደረገ ትምህርት እንዲያገኝ ማድረግ ግልጽነትን በማስፈን ሙስናን ከምንጩ ለማድረቅ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

**ሐ/ የሕዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ**

አካባቢያዊ መልካም አስተዳደርን ለልማት ግቦች መሳካት አጋዥ ማድረግ፣ ሴቶችን በቀበሌና ወረዳ በብቃት በማሳተፍ እንዲሁም በራሳቸው ሀብት እንዲያፈሩ፣ እንዲወስኑና እንዲጠቀሙ በማደራጀት እኩልነት እነዲኖር ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ ሕብረተሰቡን በማሳተፍና በማንቀሳቀስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትና የጤና ተቋማት እንዲቋቋሙ በማድረግ ለልማት ግቦች ማሳካት አስተዋጽዖዎችን ማሳደግ፣ ሕዝቡ በተለያዩ የሙያና የብዙሃን ማህበራት ተደራጅቶ መብትና ጥቅሙን ለማስከበር እንዲንቀሳቀስ አመቺ የሆነ የሕግ ማእቀፍ በይበልጥ እንዲጠናከር ማድረግ፣ መንግስት በፖሊሲዎችና እቅዶች አቀራረጽና አፈጻጸማቸውን በመገምገም መስክ የተደራጁ የሕዘብ ማህበራትን በሰፊው የሚያሳትፍበት ስርዓት ቀርጾ በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣ ማህበራቱ ጠንካራ የዴሞክራሲ ማስተማሪያ መድረኮች ሆነው እንዲያገለግሉ፣ ሀሳብን በነፃ የመግለጽ ነፃነት ከመቻቻል ባህል ጋር በማጣመር፣ የሕግ የበላይነትን፣ ዜጐች መብትና ጥቅማቸውን ለማስከበር ተደራጅተውና ጠንክረው ከመንቀሳቀስ ጋር በማጣመር እንዲንቀሳቀሱ መንግስት ያልተቆጠበ ድጋፍ እንዲሰጥ ማስቻል የህዝብ ተሳትፎን ከማረጋገጥ አንጻር ትኩረት በመስጠት ተፈፃሚ የሚደረጉ ይሆናሉ፡፡

**መ/ የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ማካተትና መተግበር**

የሥርዓተ ፆታን በተመለከተ በቀጣዩ የእቅድ ዘመን ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሴቶችን አቅም በትምህርትና ስልጠና በመገንባት በአመራርና በውሳኔ ሰጪነት ቦታ ያላቸውን ተሳታፊነት ወደ ተሻለ ደረጃ ማድረስ ሲሆን በሲቪል ሰርቪሱ በሚሰጡ ትምህርትና ስልጠናዎች ውስጥ በፊት ከነበረው ዝቅተኛ ደረጃ በመነሳት ለከፍተኛ አመራር ከሚሰጠው ትምህርትና ስልጠና ውስጥ 50 በመቶ ሴቶች እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በቀጣይም የሴቶቹን ቁጥር ሚዛናዊ ለማድረግ የተሳትፎው ድርሻ እየጨመረ የሚሄድ ሲሆን በልማት እቅዱ ዘመን ስርዓተ ጾታን በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ክንውን ክትትልና ግምገማ ውስጥ ትኩረት በመስጠት የማካተት ተግባር ይከናወናል፡፡

ኤች አይቪ ኤድስን በተመለከተ ሲቪል ሰርቪሱ ስለ በሽታው በቂ ግንዛቤ ኖሮት ራሱን እንዲጠብቅ፣ የበሽታውን ስርጭት እንዲገታና በበሽታው የተጠቁትንም ሰራተኞችንና በዚሁ በሽታ ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናት ድጋፍ እንዲደደርግ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ተግባራት ይተገበራሉ፡፡

የአካባቢ ጥበቃና ሥነ ህዝብን በተመለከተ በዓለም ላይ የተከሰተው አየር ንብረት መዛባት ባስከተላቸው ተጽእኖዎችና በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችና አውደጥናቶች በእቅድ ዘመኑ

ይከናወናሉ። በስነ ህዝብ ፖሊሲ አፈጻጸም ዙሪያ ልዩ ልዩ መድረኮችን በማመቻቸት የሲቪል ሰርቪሱን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያስችሉ ስራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚከናወኑ ይሆናል።

ወጣቶችን በተመለከተ በእቅድ ዘመኑ ወጣት ምሩቃንን በማብቃት የተሻለ ብቃት ያላቸውን ወደ መካከለኛ አመራር እንዲመጡ የሚያስችል ስርዓት ተግባራዊ ይደረጋል። አዳዲስ ምሩቃንን ወደ ሲቪል ሰርቪሱ በቅጥር ማስገባት በሚቻልበት መንገድ ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ወጣቶች በሲቪል ሰርቪሱ ያላቸውን ድርሻ ለማሳደግ ጥረት ይደረጋል።

አካል ጉዳተኞችን በሚመለከት በህግ የተደነገጉላቸውን መብቶች መሰረት በማድረግ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የተመቻቸ የሥራ ከባቢ እነዲፈጠርልቸውና የሥራ መርጃ መሳሪያዎች እንዲሟሉላቸው የሚያስችል አዎንታዊ እርምጃ ይወስዳል።

**ዓላማዎች**

የአቅም ግንባታ ንዑስ ዘርፈ የሚቀጥሉት አምስት ዓመታት እቅድ ዓላማዎች የሲቪል ሰርቪሰሱን የተቀናጀ አቅም በማሳደግና በማጐልበት የመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በበቃት እነዲፈፀሙ ማስቻል፣ በሲቪል ሰርብስ ማሻሻያ ፕሮግራም የትግበራ ሂደት እስካሁን የተገኙ ውጤቶችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር በክልል ደረጃ እንዲስፋፉ ማድረግ፣ የውጤት ተኮር ሥርዓትን /BSC/ በኮሙኒኬሽን ሥራዎች ደግፎ መተግበርና ጠንካራ የማስፈፀም አቅም ያለው መንግስታዊ መዋቅር መፍጠር ናቸው።

**ዋና ዋና ግቦች**

- የመንግስት ተቋማትን ቅልጥፍናና ዉጤታማነት /አደረጃጀትና አሰራር/ ማሻሻል
- የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራረን በሁሉም የምንግስት ተቋም ማረጋገጥ
- የህብረተሰብ ተሳትፎና ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓትን ማጎልበት
- አመራሩን በአጭር ጊዜና በረዝም ጊዜ ስልጠናዎች አቅሙንና ተነሳሽነት በማሳደግ የሚመራዉን ተቋም ተልኮ ሙሉ ለሙሉ እንዲያሳካ መስቻል
- የክልሉን መካከለኛ አመራርና ፈጻሚ /የለውጥ ሰራዊት/ ተነሳሽነትና ብቃት ማጐልበት
- የአቅም መገንቢያ አቅሞችን ብቃት በማሳደግና አዳዲሶችን በማቋቋም የለውጥ ደጋፊነት ሚናቸውን ማጎልበት
- ለውጡን በኢንፎርሜሽን ኮምንኬሽን ቴክኖሎጂ በመደገፍ የመጠቀም አቅምን ማሳደግ
- ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ

**የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች**

- የበላይ አመራሩ ለዉጡን ለዉስጥ ሰራተኛዉና ለተጠቃሚ ዜጋዉ/ ደንበኛዉ/ በማስረጽ የለዉጥ ፈጻሚና አጋዥ ሀይል ይፈጠራል
  - ➢ የለዉጡን ምርጥ ተሞክሮ በመቀመርና በማስፋት ሁሉንም ተቋማት ወደ ሚኒመም ሥታንዳርድ እንዲመጡ ማድረግ

- በየአመቱ በመንግስት ተቋማት ላይ የህዝብ ይሁንታ ቅኝት በመስራት የሚገኘዉን ዉጤት እንደግብዓት በመጠቀም የላቀ መሻሻል ዉስጥ መግባት
- የተቋማት ዉድድር፣ሽልማትና እዉቅና መስጫ ስረዓትን በመዘርጋት አመራሩና ሰራተኛዉን ማብቃት፤

## 6.2. የፍትህ ዘርፍ

### የትኩረት አቅጣጫዎች

በክልሉ ሰላማዊና የተረጋጋ ዲሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግሥት መፍጠርና በቀጣይ ለሚደረገው የኢኮኖሚ እድገት ምቹና ሰላማዊ ሁኔታን በማመቻቸት የዲሞክራሲ ተቋማትን ማጠናከር፣ የሲቪል ሰርቪሱንና የህዝብ ማህበራትን ማጠናከር፣ የዜጐች የመረጃ ሥርአት መዘርጋት፣ በዋነኛነት በፍትህ አሰጣጥ ሥርአቱ የተረጋገጡና እውነተኛ ማስረጃዎችን ከማግኘት አንፃር የሥርአቱን ውጤታማነት ማጠናከር፣ ህጐችን በማሻሻል የህጐች አፈፃፀምና አተረጓጐም ከህገ መንግሥቱ ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የዳኝነት ሥርአትንና የፍርድ ቤት ነፃነትን፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣ የህግ አስከባሪ ተቋማት በሰው ሀይል በእውቀት ክህሎትና በቁሳቁስ እንዲጠናከሩ ማድረግ፣ የህብረተሰቡ ሕገ መንግሥታዊ ግንዛቤና ንቃተ ህግ እንዲጐለብት የተቀናጁ ሥራዎችን መሥራት እና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህልና ልምድ እንዲዳብር ማድረግ በሚቀጥሉት አምስት አመታት ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው።

### አላማዎች

በፍትህ ዘርፍ የሚቀጥሉት አምስት አመታት የዘርፉን ተልእኮ ማሳካት የሚችል የበላይ አመራርና ሠራተኛ በመፍጠር፣ ህገ መንግሥታዊ ሥርአቱን ማስረጽና የህግ የበላይነት ማረጋገጥ፣ ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ ፍትህ መስጠት፣ የፍትህ አካሉን ነፃነት ግልጽነትና ተጠቃቂነት ማረጋገጥ፣ የዜጐችን ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥና ማጠናከር ናቸው።

### የፍትህ ዘርፍ ዋና ዋና ግቦች

#### የሰው ሀይል ብቃትን ማጐልበትን በተመለከተ

- በሁሉም የፍትህ አካላት ለዳኝነትና ለአቃቤ ህግነት ተመልምለው የሚገቡ የቅድመሥራ ስልጠና ይወስዳሉ።
- በዘርፉ የሚገኙ ባለሙያዎች በአመለካከት፣ በስነምግባር፣ በእውቀት፣ በክህሎት ያለባቸውን ውስንነቶች ቀጣይነት ባለው ስልጠና አቅማቸው በመገንባት ጠንካራ ድጋፍ እንዲሆኑ ይደረጋል፡
- የክልሉ የስልጠና ማእከል ደረጃውን የጠበቀና ፋሲሊቲው የተሟላ በማድረግ የባለሙያዎችን አቅም በተሟላ መንገድ መገንባት፣
- የፍትህ ሥርአቱን ባለሙያዎች አቅም የሚገነቡ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በመስራት በጥናትና ምርምሩ ውጤቱ መሠረት ያሉ ክፍተቶችን በመሙላት ብቁ ባለሙያዎችን ማፍራት፣

- *ጠበቆች በስነምግባር፣ በአመለካከት በእውቀትና በክህሎት ዳብረው ለፍትህ ሥርአቱ አጋዥ እንዲሆኑ ማድረግ፣*

**የፍትህ ሥርአቱን ተደራሽነት፣ ተጠያቂነት፣ ግልጽነት፣ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ማሻሻል፣**

- *በፍትህ አስተዳደር ውስጥ ያሉ ችግሮችን በመለየት በጥናትና ምርምር የተደገፈ የህግ ረቂቅ ማዘጋጀትና የማሻሻያ ሃሣብ ማቅረብ የሚያስችሉ ጥናቶች ማካሄድ፣*
- *ለህብረተሰቡ የንቃተ ሕግ ትምህርት በመስጠት ህግ አክባሪና አስተባባሪ እንዲሆን ማድረግ፣*
- *የወንጀልና የወንጀል ስጋቶችን በመቀነስ የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት መጠበቅ፣*
- *የወንጀል ምርመራና ውሣኔ አሰጣጥን ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ፣*
    - *በፍርድ ቤት መዛግብት የማጣራት አቅም* 98% *በማድረስ የፍትህ ሥርአቱን ውጤታማነት ማሳደግ፣*
    - *የሚሻሩና የሚሻሻሉ የይግባኝ መዛግብት* ከ24% *ወደ* 6% *ዝቅ በማድረግ ውጤታማነትን ማሳደግ፣*
    - *የዳኝነት አገልግሎት ጊዜን ለመቀነስ የመዛግብት ቆይታን* ከ180 *ቀናት ወደ* 70 *ቀናት ማድረስ፣*
    - *የፍርድ ምርመራ ሥራን የቅሬታ ሥራንና የቅሬታ አፈታት ሥርአትን ማሻሻል፣*
- *ውጤታማ የሆነ የሰነዶች ማስረጃ ምዝገባ፣ ማረጋገጥ፣ የምክር አገልግሎት በመስጠትና አያያዙንም ዘመናዊ በማድረግ የህዝብና የመንግሥት ንብረት ማስከበር፣*
- *የመንግሥት አቃቤ ህግ የማሸነፍ አቅም በወንጀል* ከ82.02% *ወደ* 95%*፣ በፍትሃብሄር የማሸነፍ አቅም* ከ87.02% *ወደ* 90% *ከፍ በማድረግ የስርአቱን ቅልጥፍና ማሳደግ፣*
- *ለአማራጭ ሙግት መፍቻ ከቀረቡት ጉዳዮች እልባት የሚያገኙ ጉዳዮች የኘላዝማ ችሎት* ከ62 *ወደ* 100*፣ ተዘዋዋሪ ችሎት* ከ343 *ወደ* 501 *ከፍ በማድረግና የክላስተር ችሎትን* ከ1 *ወደ* 6 *በማሳደግ፣ የፍትህ ሥርአቱን ተደራሽነት ማሻሻል፣*
- *ከቀረቡት ጉዳዮች በድርድር እልባት እንዲያገኙ ከተደረጉት ጉዳዮች ገቢ የሚሆነው የገንዘብ መጠን* ከ95% *ወደ* 100% *ከፍ በማድረግ በክርክር የሚወጣውን ጊዜና ሀብት በመቆጠብ የሥርአቱን ውጤታማነት ማሳደግ፣ ፣*

**የዳኝነት ነፃነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማሳደግ፣**

- *የህፍት አካሉ ነፃነቱ ተጠብቆ ተጠያቂ የሚሆንበት ሥርአት በመመስረት ፍትህን ማስፈን።*
- *የዳኞች ሹመት በብቃት ላይ የተመሰረተና የሴቶችና የብሄር ብሄረሰቦች ውክልና ያረጋገጠ በማድረግ ፍትሀዊና ውጤታማ የፍትህ ሥርአት ማጠናከር።*
- *የዳኞች ሥራ አፈፃፀም መመዘኛ ሥርአቱ ተዘርግቶ፣ የተጀመረው ግምገማ ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግና የማጥራት ሥራውን በማጠናከር ግልጽና ተጠያቂነት ያለው የፍትህ ሥርአት እንዲዘረጋ ማድረግ፣*

- ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ለሚቀርቡ የዲሲፕሊን ጉዳዮች አፋጣኝ ውሣኔ እንዲያገኙ የሚያስችል ሥርአት በመዘርጋት የፍትህ ሥርአቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግና ተጠያቂነትን ማስፈን፣
- የፍርድ ሂደት በተሟላ መልኩ በግልጽ ችሎት በማከናወን ግልጽነትን ማሳደግ፣
- የፍ/ቤት ሠራተኞች በአገልጋይነት መንፈስ ለተጠቃሚ ምቹ በሆነ ሁኔታ ተገልጋዮች ሣይፈሩ፣ ሳይሸማቀቁ፣ ሰብአዊ ክብራቸው ሳይነካ በተገቢው እንዲስተናገዱ ለማድረግ የተጀመሩ ሥራዎች በክልሉ ተስፋፍተው ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ የፍትህ ሥርአቱን ተጠያቂነትን ያሰፈነ ማድረግ፣

**ታራሚዎችን ማነጽን በተመለከተ**

- ሀገራዊ የታራሚዎች አያያዝና ጥበቃ ስታንዳርድን መሠረት በማድረግ የክልሉን ስንታንዳርድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ማንኛውም ታራሚ የስነዜጋ፣ የሥነምግባር፣ የአካዳሚክና ሙያ ስልጠናዎችን እንዲያገኝ ማድረግ ፣
- የማረሚያ ቤት ቆይታቸውን ጨርሰው የሚወጡ ታራሚዎች ከህብረተሰቡ ጋር ተዋህደው የሚሰሩበትን ሁኔታ የሚከታተል ሥርአት በመዘርጋት የታራሚዎች አያያዝ ምን መሆን እንደሚገባው መረጃ ማግኘትና በተገኘው መረጃ መሠረት ውጤታማ ማድረግ፣
- የማረሚያ ቤቶች ገጽታ ማሻሻያ ሥራዎች በመስራት ማረሚያ ቤቶች እስር ቤቶች ሳይሆኑ የመልካም ሥነምግባር ማነጫና ማስተማሪያ ናቸው የሚል አመለካከት በህብረተሰቡ ውስጥ መፍጠር፣

**ሰላምና ፀጥታን ማስከበር**

- በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ አለመግባባትና ግጭቶችን ሙሉ በሙሉ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት አቅምን የሚያሳድጉ የሰላም እሴትና የመቻቻል ባህል ግንባታ ተግባራት ማከናወን ቁሳዊና ሰብአዊ ጥፋት ከማድረሳቸው በፊት እንዲፈቱ ማድረግ፣
- የፀረ ሰላም ኃይሎችን እንቅስቃሴ በማምከን የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ማረጋገጥ፣
- ግጭቶችን በተመለከተ ጥናት በማካሄድ በዘላቂነት እንዲፈቱ የማድረግ አቅም በመገንባት በተደጋጋሚ የሚፈጠሩ ችግሮች መንስኤዎችና መፍትሄዎችን በማጥናት ሰላምን ማስፈን፣
- በሀይማኖት ተቋማትና ተከታዮቻቸው መካከል መቻቻልና መከባበር የሚያዳብሩ እና በጐ እሴቶችን የሚያጐለብቱ ተግባራት በማከናወን ግጭቶችን መከላከል።

**የወንጀልና የትራፊክ አደጋ ክስተቶችን መቀነስ**

- አጠቃላይ ወንጀል በገጠር ከአንድ ሺህ ሰው ከ2.6 ወደ 1.6፣ በከተማ ከ6 ወደ 3 ወንጀለኛ ዝቅ ማድረግ፤ ዋና ዋና ወንጀል በገጠር ከአንድ ሺህ ሰው ከ1.15 ወደ 1፣ በከተማ ከ4 ወደ 1.5 ወንጀለኛ ዝቅ በማድረግ የክልሉን ህዝብ ሰላም ማጠናከር፣

- *ህገወጥ የአደንዛዠ እጽ ዝውውር አሁን ካለበት 32 ወደ 22 ዝቅ በማድረግ ህጋዊነትን ማጠናከር፣*
- *ከግንዛቤና ከቁጥጥር እጥረት የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋ አሁን ካለበት በአመት* 1806 *ወደ* 1500 *ዝቅ በማድረግ በሰው ህይወትና ንብረት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት መቀነስ፣*
- *አሁን ያለውን* 90 *በመቶ የቀበሌ ኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ሽፋን በሁሉም ቀበሌዎች በማዳረስ ግጭቶች የከፋ ጉዳት ሳያደርሱ እዛው እንዲፈቱ ማስቻል፣*
- *በፀጥታ ሥራው ላይ የህብረተሰብ ተሳትፎ ቁጥር ከ*1.423 *ሚሊዮን ወደ* 3.06 *ሚሊዮን ከፍ በማድረግ ህገወጥነትን መቀነስ፣*
- *የግል አቤቱታዎችን የማጣራት አቅም አሁን ካለበት* 90% *ወደ* 97% *እንዲሁም የመንግሥት ክስ የማጣራት አቅም ከ*70% *ወደ* 95% *በማሳደግ የሥርአቱን ውጤታማነት ማሳደግ፣*
- *የትጥቅና ጦር መሣሪያ አያያዝና አስተዳደርን በማሻሻል የፀጥታ ሥራውን ማጠናከር።*

## *የማስፈፀሚያ ስትራተጂዎች*

- *የማስፈፀም አቅምን በመገንባት ተቋማዊ ለውጥ ማምጣት፣*
- *በጥናትና ምርምር በተደገፈ መልኩ የሕግ ረቂቅ ዝግጅትና ኮዲፊኬሽንና የኮንሶሊዴሽን ሥራ ማከናወን።*
- *ሕገመንግሥታዊ ሥርአቱን እና የህዝብ ጥቅምን አደጋ ላይ በሚጥሉ የወንጀል ተግባራቶች ላይ ቅድሚያ ሰጥቶ የመከላከል ሥራ መስራት፣ የተፈፀሙ ወንጀሎችንም ተከታትሎ ወንጀል አድራጊዎችን ተገቢ ቅጣታቸውን እንዲያገኙ የማድረግና አፈፃፀሙን መከታተል የሚያስችል አሰራር ማስፈን፣*
- *የወንጀል ሰለባዎች የደረሰባቸው ጉዳት የሚካካስበት ሥርአት መዘርጋት።*
- *ታራሚዎች የእርምት ጊዜአቸውን ጨርሰው በሚወጡበት ጊዜ ሰላማዊ፣ ሰብአዊ መብት አክባሪ፣ ህግ አክባሪና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ሙያ ያላቸው ሆነው ታርመው እንዲወጡ በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የተለያዩ የአካዳሚክና የሙያ ትምህርት ስልጠና የሚያገኙበት ሥርአት መዘረጋት፣*
- *የሕግ ጥናትና ምርምር በማድረግ፣ በሰብአዊ መብት አጠባበቅ የህብረተሰቡን እውቀትና ግንዛቤ በማዳበር፣ የሕግ የበላይነትን በማጠናከር፣ ለመልካም አስተዳደርና ለልማት እገዛ ማድረግ፣*
- *የህብረተሰቡን ንቃተ ህግ ደረጃ በደረጃ በማሻሻል ህግና ሥርአት የሚያከብርና የሕግ ማስከበር ሥራውን በንቃት የሚደግፍ የህዝብ አቅምና አደረጃጀት መፍጠር፣*
- *ሲቪል ማህበራትና ባለድርሻ አካላት በሀገሪቱ የመልካም አስተዳደርና ልማት ግንባታ ያላቸውን የባለድርሻነት ሚና የሚያጐለብት ሥርአት መፍጠር፣*
- *ለሴቶችና ህፃናት፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ የተጋለጡ ዜጐችን ሕጋዊ መብትና ጥቅሞችን መከበራቸውን የማረጋገጥ አሰራር መፍጠር፣*

- በጥብቅና ሙያ የሚሰማሩ ባለሙያዎችን በቃትና ሙያዊ ሥነምግባራቸውን ያከበሩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሥርአት መዘርጋት፣

## 6.3. ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር

### የትኩረት አቅጣጫዎች

ዲሞክራሲያዊና መልካም አስተዳደርን በክልሉ ለማስፈን በቀጣዮቹ አምስት አመታት /2003-2007/ ሰላምን፣ ልማትን፣ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ለማስፈን የሚያግዙ ህጐችን ማውጣት፣ በህጐች አፈፃፀም ዙሪያ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ ነፃና ፍትሃዊ ዲሞክራሲያዊ ሰላማዊ በህዝብና በፖለቲካ ድርጅት ተአማኒነት ያለው ምርጫ ማካሄድ፣ የሁሉንም ዜጐች የሰብአዊና የአስተዳደር በደሎችን መከላከልና ማረም፣ የሴቶችን መብት ማስከበር፣ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመፍጠር መስራት፣ የህገ መንግሥት፣ የሰብአዊና የዲሞክራሲ ባህል እንዲጐለብትና እንዲዳብር ማድረግ፣ የህዝብ ውክልናን ማረጋገጥ፣ የኦዲት ሥርአት ጥራት፣ ሽፋንና ክትትልን በማጠናከር ተጠያቂነትን ማስፈን፣ ኢንቨስትመንትን ከመሳብና ከማስፋት አንፃር የግሉ ክፍል ኢኮኖሚ የሚመራበት የኦዲትና የሂሣብ አያያዝ ደረጃ ማውጣት፣ በሰብአዊ መብት ዙሪያ መንግሥትን ማማከርና የሰብአዊ መብት ጥናትና ምርምር ማካሄድ እና የፕሬስ ነፃነት፣ ነፃና የተሻሻለ አስተማማኝ የመረጃ አቅርቦት የሚሉት የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

### አላማዎች

በዘርፉ የሚቀጥሉት አምስት አመታት እቅድ አላማዎች የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ዘርፍ ተቋማትን ማጠናከርና አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ እንዲፈጠር እስተዋጽኦ ማድረግ፣ ም/ቤቶችን ለህዝብ ቅርብ ማድረግ፣ ጠቃሚ ሕጐችን ማውጣትና የክትትልና ቁጥጥር ሥርአቶችን መዘርጋት፣

### ግቦች

#### የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ሴክተር ተቋማትን ማጠናከር

- በየተቋማቱ የሚገኙ ፈፃሚዎች በክህሎትና በአመለካከት የተሻሉ እንዲሆኑ የረጅምና የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች እንዲያገኙ ይደረጋል።
- ለተቋማቱ አሰራር አጋዥ የሆኑ መመሪያዎች፣ ደንቦችና የአሰራር ማንዋዋሎች እንዲሁም ለህገ መንግሥት አስተምህሮ የሚሆን ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ይዘጋጃሉ።
- ከፌደራል መንግሥትና ከወረዳ አስተዳደር ም/ቤቶች ጋር መረጃን በሚፈለገው መንገድ ለመለዋወጥና መረጃን ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ እንዲያስችል ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ስርአት ይፈጠራል።
- በክልሉ መንግሥትና በወረዳ አስተዳደሮች መካከል ቋሚ አስተዳደራዊ ግንኙነት ተቋማዊ አደረጃጀትና የአሰራር ሥርአት መዘርጋት፣

- *በመንግሥት ግንኙነትን በፌደራሊዝም ዙሪያ በየደረጃው ያለውን የአመራር አካልና የህብረተሰቡን ግንዛቤ ከፍተኛ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ።*
- *ህገ መንግሥቱን በሰብአዊ መብትና ዲሞክራሲያዊ ንቃተ ህሊናን ለማሳደግ የሚረዱ ሥራዎች ከመስራት አንፃር*
  - *የሥነ ዜጋ ትምህርትን ለተማሪዎች እንዲሰጥ በማድረግ የዲሞክራሲ ባህልን እንዲለማመዱ የተግባር ልምምድ በትምህርት ቤቶች እንዲጀመር በማድረግና ማስፋፋት በሂደቱ ውስጥ እንዲጐለብቱ ማድረግ፣*
  - *ግጭት በተከሰተባቸውና ሊከሰትባቸው የሚችሉ ቦታዎችን በመለየት ለሴቶችና ወጣቶች የአስተምህሮት ሥራዎችን በመስራት ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና እሴቶችን እንግዲያጐለብቱ ማድረግ*

## *አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ከመፍጠር አንፃር*

- *በክልሉ ብሄር ብሄረሰቦች ግንኙነት ላይ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን በመለየት የትምህርት፣ የመሰረተ ልማት ስርጭትና የሚዲያ ሽፋን ፍትሃዊነት ይረጋገጣል።*
- *የበጀት ክፍፍል ፍትሀዊነትን ለማሳደግና ማከፋፈያ ቀመር ለማዘጋጀት ህብረተሰቡን ያሳተፈና ተቀባይ ነት ያለው የበጀት ማከፋፈያ ሥርአት ይዘረጋል።*
- *ከአጐራባች ክልሎች እንዲሁም በክልሉ ወረዳዎች የሚፈጠሩ የድንበር ግጭቶችን ለመፍታት የክልሉን ብሎም የወረዳዎች ካርታ በማዘጋጀት መከላከልና ግጭቶችም ሲፈጠሩ ባህላዊ ዘዴዎችን በማጥናት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።*
- *የብሄር ብሄረሰቦች ቀን ህዳር 29፣ የባንዲራና የዲሞክራሲ ቀናት በስርአት ለመምራት ደንብና መመሪያ ተዘጋጅቶ በመመሪያው መሠረት በአላቱ እንዲከበሩ ይደረጋል።*

## *የህዝብ ውክልናን ለመወጣትና የህዝብ ሀብትን ተጠያቂነት ባለው መልኩ ለማስተዳደር ጠቃሚ ሕጐችን ከማውጣትና የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎችን በተመለከተ*

- *በክልሉ ምክር ቤትና በክልሉ ካቢኔ ልማቱን የሚያግዙ ህጐች፣ ፖሊሲዎችና አዋጆች እንዲወጡ ይደረጋል ።*
- *የህጐችን ተፈፃሚነት ለማረጋገጥና ህዝቡን የልማት ተጠቃሚ ለማድረግ ሰብአዊ መብት፣ እንባ ጠባቂ፣ የክልሉን ኦዲት በማስተባበር የተጠናከረ የቁጥጥርና ክትትል ሥራዎች ይከናወናሉ።*

## *ም/ቤቶችን ለህዝብ ቅርብ ከማድረግ አንፃር*

- *ክልሉ የሚከተላቸው የትኩረት አቅጣጫዎች በም/ቤቱ ውሳኔ መሠረት ይሆናል፣*
- *የምክር ቤቱ እንቅስቃሴ ለህብረተሰቡ በተለያዩ ዘዴዎች ለህዝብ እንዲደርስ ይደረጋል፣*
- *የፌደራልንና የአቻ ክልሎችን መረጃ በማግኘትና ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመቅሰም የመረጃ ልውውጥ ሥርአት እንዲኖር ይደረጋል።*

## የህዝቡን ተሳትፎ ከማረጋገጥ አንፃር

- በየደረጃው የሚገኙ ም/ቤቶች በም/ቤቶችና በፖለቲካ የሴቶችን ተሳትፎ ያሳድጋሉ ፣
  - በምክር ቤቶች የሴቶች ተሳትፍ አሁን ካለበት 17% ወደ 60% ከፍ እንዲል ይደረጋል፣
  - በክልል ምክር ቤት የሴቶች ተዋጽኦ አሁን ካለበት 31.29%፣ በወረዳ 33.5%፣ በቀበሌ 22.4%፣ በብሄረሰብ ዞኖች 27.3% የነበረው በሁሉም እርከኖች ወደ 50% ከፍ ማድረግ፣
  - በፖለቲካ አመራሮች ላይ የሴቶች ተሳትፎ በክልል 6.88%፣ በዞን 3.9%፣ በወረዳ 17%ና በቀበሌ 18% ከነበረበት በሁሉም እርከኖች ወደ 50% በመቶ ከፍ ማድረግ።
- በምክር ቤቶች የሚወጡ አዋጆች፣ የበጀት እቅዶች፣ ፖሊሲዎችና የተለያዩ ተግባራት ህብረተሰቡንና የሲቪክ ማህበራት ሙሉ በሙሉ ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልክ ተግባራዊ ይደረጋሉ ።
- የብሄረሰብ ምክር ቤቶችና ልዩ ድጋፍ የሚሹ አካባቢዎች ላይ የፖለቲካ ተሳትፎአቸውን የሚያሳድጉ ሥራዎች ይሰራሉ።
- የወረዳና የቀበሌ ም/ቤቶች ህብረተሰቡን የሚያሳትፉ መድረኮች ያመቻቻሉ፣
- ህግ አውጪ አካላት ማህበራትን የሚያጠናክሩ ሕጎች ያወጣሉ፣ በወጡ ፖሊሲዎችና እቅዶች ላይ የተለያዩ ማህበራት በየደረጃው ተሳትፎ ያደርጋሉ።

## የማስፈፀሚያ ስትራተጂዎች

- የማስፈፀም አቅምን በመገንባት ተቋማዊ ለውጥ ማምጣት፣
- ከፌደራል መንግሥት፣ ከወረዳ አስተዳደር ም/ቤቶችና ለህብረተሰቡ መረጃን በሚፈለገው መንገድ ለመለዋወጥና ለማድረስ እንዲያስችል ዘመናዊ የመረጃ አቅርቦትና ተደራሽ ነት ስርአት ማስፈን።
- የህብረተሰቡን ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰቦችንና እሴቶችን ለመገንባት የሥነምግባርና የሥነ ዜጋ ትምህርትን በስፋት ማሰራጨት፣
- በክልሉ ወረዳዎችና በአጎራባች ወረዳዎች ግንኙነት ላይ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን በጥናት መለየት፣
- ህብረተሰቡን ያሳተፈና ተቀባይነት ያለው ፍትሀዊ የበጀት ክፍፍል ሥርአት መዘርጋት፣
- ግጭቶችና አለመግባባቶች እንዳይከሰቱና ከተከሰቱም በሁዋላ በሰላማዊ መንገዳ እንዲፈቱ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማዳበርና የምክክር መድረኮችን በመፍጠር ሰላምን የሚያሰፈን አሰራር መዘርጋት፣
- ለልማትና ለዲሞክራሲያዊ ሥርአት ግንባታ ማስፈፀሚያ የሚሆኑ መመሪያዎችና ደንቦች በማዘጋጀት  አፈፃፀማቸውን መከታተልና መቆጣጠር።

- የመረጃ ምንጮችን ማጐልበት፣ ተደራሽነቱን ማስፋትና ጥራት ያለው የመረጃ ፍሰት ሥርአት መፍጠር፣
- ህብረተሰቡ በልማትና ዲሞክራሲያዊ ሥርአት ግንባታው ተሳታፊና ባለቤት እንዲሆን አማራጮችን መፍጠር/ማመቻቸት፣
- የተጠናከረ የክትትል የግምገማና የድጋፍ አሰጣጥ ስርአት መዘርጋት፣

## 6.4. ብዙሀን መገናኛ

**የትኩረት አቅጣጫዎች**

- የመገናኛ ብዙሃንን አገልግሎት በዓይነት፣ በጥራትና በቁጥር ማስፋፋትና የስርጭት ቋንቋን ማሳደግ እንዲሁም ከማስፋፋቱ ጎን ለጎን በስራ ላይ የሚገኙ መገናኛ ብዙሃን ህግና አሰራርን አክብረው መስራታቸውን መከታተል ናቸው።

**ዓላማ**

- በመገናኛ ብዙሃን አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የህብረተሰቡን ፍላጎት ማርካት ነው።

**ግቦች**

- የልማት ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ስርዓት ግንባታን ለማጠናከር ኪራይ ሰብሳቢነትንና ሙስናን ለመታገል ምቹ ሁኔታን መፍጠር
    - የመደበኛ ሬዲዮ አገልግሎት ሽፋንን/ተደራሽነት በ2002 ከነበረበት 40 በመቶበዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 100 በመቶ ማድረስ
    - የመደበኛ ሬዲዮ አገልግሎት ቋንቋን በ2002 ከነበረው በቁጥር 4 ቋንቋ በ2007 ወደ 5 ማሳደግ
    - የመደበኛ ሬዲዮ አገልግሎት የአየር ጊዜ በሳምንት በሰዓት በ2002 አማርኛ 60 ሰዓት፣ አዊኛ 1 ሰዓት፣ ኸምጠኛ 1 ሰዓት፣ ኦሮሞኛ 1 ሰዓትና እንግሊዘኛ 0 ሰዓት የነበረውን በ2007 ዓ.ም እንደየቅደም ተከተላቸው 119፣ 14፣ 14፣ 14 እና 7 ማድረስ
    - የኤፍ.ኤም ሬዲዮ አገልግሎት የስርጭት የአየር ጊዜ በ2002 በሳምንት በሰዓት 42 የነበረውን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 168 ሰዓት በማድረስ የአገልግሎት ሽፋኑን/ተደራሽነቱን በ2002 ካለበት 2 በመቶ በ2007 ወደ 75 በመቶ ማድረስ
    - የቴሌቪዥን አገልግሎት የስርጭት ቋንቋን ቁጥር በ2002 ከነበረው 1 ቋንቋ በ2007 ወደ 5 በማሳደግ የቴሌቪዥን አገልግሎት ሽፋኑን አሁን ካለበት ወደ 100% ማድረስ
    - የቴሌቪዥን አገልግሎት የስርጭት የአየር ጊዜ በ2002 በሳምንት በሰዓት አማርኛ 7 እንዲሁም ምንም የአየር ሰዓት ያልተመደበላቸውን አዊኛ፣ ኸምጠኛ፣ ኦሮሞኛ እና እንግሊዘኛ በ2007 በቅደም ተከተላቸው መሠረት 56፣ 7፣ 7፣7 እና 7 ማድረስ
    - የህትመት ሚዲያ ስርጭት ሽፋን/ተደራሽነትን በሚመለከት በቅጅ መጠን በ2002 የነበረውን አማርኛ 5000 ቅጅ እና ምንም ያልነበረውን አዊኛ፣ ኸምጠኛ፣ ኦሮሞኛ እና እንግሊዘኛ በ2007 እንደየቅደም ተከተላቸው ወደ 10,000፣ 3000፣ 3000፣ 3000 እና 1000 ማድረስ

- የህትመት ሚዲያ አገልግሎት በቋንቋ ዓይነት በ2002 የነበረውን 1 ቋንቋ በዕቅድ ዘመኑ ወደ 5 ማሳደግ እንዲሁም በሚዲያ የህብረተሰብ እርካታን በ2002 ከነበረበት 30 በመቶ በ2007 ወደ 85 በመቶ ማድረስ
- ሬዲዮ ያላቸው ቤተሰቦችን ብዛት በ2002 ከነበረበት 0.72 ሚሊየን በ2007 መጨረሻ ወደ 2 ሚሊየን ማሳደግ

## 6.5. ኮሙኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ

የትኩረት አቅጣጫ

- የማስፈጸም አቅም ግንባታ፦ ፈጻሚው ኃይል የተቀመጡትን የመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም ክልላዊ እቅዶች ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ማድረግ የሚችልበትን የአመለካከት፣ የአሠራርና የአደረጃጀት ብቃት እንዲዳብር ማድረግ
- በዋና ዋና የልማትና መልካም አስተዳደር ተግባራት የክልሉን ልማት በማፋጠን ህዝቡን ተጠቃሚ ማድረግ ፣
- ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የክልሉን ገጽታ ግንባታ ማጎልበት፣
- የመገናኛ ብዙሃንን ማስፋፋትና ህግና አሰራርን ተከትለው መስራታቸውን ማረጋገጥ
- ክልሉ የራሱ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ማሰራጫ ማዕከል እንዲኖረው ማስቻል፤

**ዓላማ**

ወቅታዊና ትክክለኛ ኢንፎርሜሽን ያለው ሁለገብ ተሳትፎ የሚያደርግ ህዝብ በመፍጠር ልማቱን ማፋጠን

**ግቦች**

- ከ5ዓመት በኋላ የክልላችንን ኢኮኖሚ ለማሳደግ በአመራርና ፈጻሚ አካላት የሚታዩ የአመለካከት ችግሮችን በመፍታት የልማት ተነሳሽነት ማሳደግ ፣
- በክልሉ የልማት፣ የዴሞክራሲና መለካም አስተዳደር የተኩረት አቅጣጫዎችና የትኩረት ማስኮች እንዲሁም የአፈጻጸም ስልቶች ላይ ግልጽነት በመፈጸጠር እቅዱ በጥራት እንዲፈጸም ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር፣
- በዕቅዱ ላይ የጋራ አመለካከትና እምነት በሁሉም የክልሉ ህ/ተሰብ ዘንድ እንዲፈጠር የኮሙዩኒኬሽንና የሚዲያ አካላትን አቅም ማጎልበት፣
- በገጠርም ሆነ በከተማ የማስፋት ስትራቴጅ ቁልፍ የአፈጻጸም ስትራቴጂ በመመስረት የኬሙኒኬሽን ስራው እንዲመራ ማድረግ፣
- በገጠርም ሆነ በከተማ የሚታዩ አደናቃፊ አመለካከቶችን በመለየት፣ በመለካትና ትክክለኛ አመለካከት በማስጨበጥ አሰፈጻሚ እና ፈጻሚ አካላት መካከል የጋራ መግባባት ማሻሻል ፣

# ክፍል ሰባት

## 7. የባለብዙ ዘርፎች ዕቅድ

### 7.1. ሥርአተ ጾታና የህፃናት ጉዳይ

**የትኩረት አቅጣጫዎች**

*የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ ዋነኛ መሠረት የሀገራችን ሕገ መንግሥት ሲሆን አላማው ሴቶች በህብረተሰቡ ውስጥ በማንኛውም መስክ ሰብአዊና የንብረት ባለቤትነትና ተቆጣጣሪነት መብታቸው እንዲከበርና እኩልነታቸው በተግባር እንዲረጋገጥ፣ በኢኮኖሚ በማህበራዊና በፖለቲካ እኩል ተሳታፊ፣ ተጠቃሚና ውሳኔ ሰጪ የሚሆኑበት የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጠርና ሕጋዊ ድጋፍም እንዲያገኙ ማድረግ፣ በተለይም የገጠሯ ሴት መሠረታዊ የሆኑ ልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ የሥራ ማቃለያ ቴክኖሎጂዎችን የምታገኝበትንና ተጠቃሚ የምትሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው። እንዲሁም በጾታ ላይ የተመሰረተ ባህላዊና ልማዳዊ አድሏዊ አስተሳሰብ ደረጃ በደረጃ ማጥፋትና ሴቶች በየደረጃው የውሳኔ ሰጪነት ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ ነው።*

*በሌላ በኩል የሕፃናት ፖሊሲን በተመለከተ በልማት እቅዱ ዘመን ለመቅረጽ የሚያስችል ተግባራዊ እንቅስቃሴ ይደረጋል። በህፃናት ዙሪያ የወጡ ህጐች፣ ደንቦች ስምምነቶች ተግባራዊ እንዲሆኑና በህፃናት ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማትን ለመደገፍ ትኩረት ይሰጣል።*

**አላማ**

*የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ የህፃናትና የሴቶችን መብት ማስከበርና ደህንነታቸውን ማስጠበቅ፣ አለም አቀፍና በሀገር ደረጃ የወጡ ስምምነቶች፣ ኮንቬንሽኖች፣ ፖሊሲዎች፣ ሕጐች፣ የድርጊት መርሃ ግብሮችንና ፓኬጆች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ የሴቶችንና የህፃናትን መብቶች ማስከበር ነው።*

**ግቦች**

**የሴቶችና የህፃናት መብቶችን ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ማስቻል**

- *ሀገር አቀፍ፣ አህጉራዊና አለም አቀፍ ፖሊሲዎች፣ ህጐችና ስምምነቶች ለማስከበር የሚያስችል ተቋማዊ አሰራር በመፍጠርና በማጠናከር የሴቶችንና የህፃናትን ጥቅም ማስከበር፣*
- *የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት የሚገድቡ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ያለእድሜ ጋብቻ* ከ40% *ወደ* 10%*፣ የሴት ልጅ ግርዛት* ከ30% *ወደ* 5%*፣ ግግ ማስፈልፈል* ከ38% *ወደ* 15%*፣ እንጥል ማስቆረጥ* ከ43% *ወደ* 15%*ና የውርስን ጋብቻ* በ95% *በመቀነስ ጾታዊና የህፃናት ጥቃትን በማስወገድ የሴቶችንና የህፃናት መብት ማስጠበቅ።*

- የተዛባውን የሥርአተ ጾታ ግንኙነትና አስተሳሰብ ለማስተካከል አሰገድዶ መድፈር 95%፣ ጠለፋ 95%፣ የቤት ውስጥ ጥቃትን 90% በመቀነስና ጾታዊ ትንኮሳ ወደ10% ዝቅ በማድረግ የሴቶችን ጥቃት መቀነስ፣
- በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ዙሪያ ከዚህ በፊት ትምህርት ይሰጠው የነበረውን 30% የህብረተሰብ ክፍል ወደ 95% በመቶ ከፍ በማድረግ ትምህርት ካገኙት ውስጥ የ70% አመለካከት እንዲቀየር በማድረግ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መቀነስ፣
- ለጉዳት ተጋላጭ ለሆኑ ህፃናትና ሴቶች ድጋፍና እንክብካቤ በማድረግ አገር ተረካቢና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ማስቻል።
- ለትምህርትና ቅስቀሳ ይገኝ የነበረውን ብር 2 ሚሊዮን ወደ 7 ሚሊዮን በማሳደግና አፈፃፀሙንም 95% በማድረስ የሴቶችንና የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማዳበር፣

## ከባለድርሻ አካላትና አጋር አካላት ጋር ቅንጅት መፍጠር

- ሁሉምተቋማት የሥርአት ጾታን ጉዳይ በተግባሮቻቸው እንዲያካትቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በሴቶች ዙሪያ የወጡ ህጐችና ደንቦች ተግባራዊ የማድረግ አቅማቸውን ወደ 90% ከፍ ማድረግ፣
- ስለ መደራጀት በክልሉ ትምህርትና ስልጠና የሚያገኙ ሴቶችን ቁጥር ከ35% ወደ 90%፣ ትምህርት ካገኙት ውስጥ የተደራጁ ሴቶችን ከ24.6% ወደ 90% ከፍ በማድረግና የነበሩትን 1,530 ማህበራት ወደ 3,780 ከፍ በማድረግ የሴቶችን የመደራጀት ፍላጐትና ገንዛቤ በማሳደግ ተጠቃሚነታቸውን ከፍ ማድረግ፣
- የተፈጠሩ የሴቶች አደረጃጀቶችን ለማጠናከር ከዚህ በፊት ድጋፍና ክትትል የሚደረግላቸውን 459 ቡድኖችና ማህበራት ቁጥር ወደ 3,470 ከፍ በማድረግ የማህበራቱን አቅም ማጐልበት፣
- በህፃናት መብቶች ማስከበር ላይ የሚሰሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ መስራት፣

## በሴቶች ዙሪያ ያሉ ችግሮችን በመለየት የተለያዩ የገቢ ምንጮችን በማፈላለግ የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ

- በሴቶች ዙሪያ ያሉ ችግሮችን ለመለየት የሚደረጉ ጥናቶችን ቁጥር ከ2 ወደ 5፣ የተቀረጹ ፕሮጀክቶችን ወደ 500 እና ተጠቃሚ የነበሩ ሴቶችን ቁጥር ከ9,878 ወደ 47,175 ከፍ በማድረግ ሴቶችን በኢኮኖሚው ተጠቃሚ ማድረግ፣
- ሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ የተለያዩ ምንጮችን በማፈላለግ የሚገኘውን ብር 12 ማሊዮን ወደ 40 ሚሊዮን በማሳደግና አጠቃቀሙንም ወደ 95% በማሳደግ የሴቶችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣
- የሥራ አጥ ሴቶች ቁጥርን ከ23.4% ወደ 5% ዝቅ ማድረግ፣
- የፋይናንሻል ተቋማት እና የሴቶች ተጠቃሚዎች የጋራ ማእቀፍ በመፍጠር ሁሉም እንዲጠቀሙበት ይደረጋል።

**የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች**

- በሁሉም ዘርፎች የሴቶችና የህፃናት ጉዳይ ለማካተት የሚያስችል ተቋማዊ አቅም ማጠናከር፣
- የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም በሥርአተ ጾታና ህፃናት መብቶች ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማዳበር የባህርይ ለውጥ ማምጣት፣
- ፖሊሲ፣ ሕግ፣ ፓኬጅና የማስፈፀሚያ ሥርአቶች እንዲወጡና እንዲጠናከሩ ማድረግ፣
- የሴቶችና የህፃናት ጉዳይ አደረጃጀቶችን አቅም የሚጠናከርበር አሰራር መዘርጋት፣
- በሁሉም መስኮች በእድሜና በጾታ የተለየ በቂ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ሥርአት መዘረጋት
- ከባለድርሻዎችና አጋር አካላት በቅንጅት መሥራት የሚያስችሉ የአሰራር ማንዋሎች ማዘጋጀት፣

## 7.2. ሥነህዝብና ልማት

**የትኩረት አቅጣጫዎች**

የሰው ሀብት ግንዛቤ አግኝቶ በአግባቡ ካልተመራና ከኢኮኖሚ እድገቱ ጋራ ካልተጣጣመ ለልማት የሚውለው ሀብት ለመሠረታዊ ፍጆታ ሊውል ስለሚችልና የህዝብ አካባቢያዊ ሥርጭትም በአካባቢ ደህንነትና በመሬት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ስለሚያሳድር ከፍተኛ ትኩረት የሚያሻው ዘርፍ ነው፡፡

በክልላችን የሚታየው የህዝብ እድሜ ስብጥር ወደአምራች ሀይሉ የሚጨመረው ቁጥር ከፍተኛ ነው፣ በ2002 በተደረገው ትንበያ ከክልሉ ህዝብ 52 በመቶው አምራች ሀይል በመሆኑ ይሄን ሀይል ምርታማ ማድረግ ለኢኮኖሚ እድገቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚኖረው በመሆኑ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት የተቀመጡት እቅዶች የሥነህዝብ ፖሊሲውን ውጤታማ እንዲያደርጉ ማስቻልና የሥነህዝብ ዋና ዋና ባህሪያት ከኢኮኖሚው አቅም ጋር ማጣጣም የእቅድ ዘመኑ መሠረታዊ አቅጣጫ ነው፡፡

**አላማዎች**

የህዝብ ቁጥር እድገት ምጣኔን ከክልሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ልማትና አጠቃቀም አቅም ጋር በማጣጣም የሕዝቡ የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል ማድረግ ነው፡

**ግቦች**

**ስነህዝብና ልማት**

- በስነህዝብ ዙሪያ ወቅታዊ መረጃዎች እንዲሰበሰቡና በጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ
- የሥነህዝብ ምክር ቤቶችን በክልል በወረዳና በዞን በማቋቋምና በመደገፍ የሥነህዝብ ሥራዎችን ውጤታማ ማድረግ፣
- የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ሕብረተሰቡ በሥነህዝብ ጉዳዮች ላይ ያለውን እውቀትና ግንዛቤ በማዳበር የሥነህዝብ ጉዳዮችን ውጤታማ ማድረግ፣
    - በክልሉ ውሰጥ በ2002 የነበረውን 1.8 የህዝብ ቁጥር እድገት ምጣኔን በማሻሻል ከኢኮኖሚ ልማት ጋር ማጣጣም፣

- **አንዲት ሴት በአማካይ የምትወልዳቸው ልጆች ብዛት በ2002 ካለበት 4.18 በ2007 ወደ 3.8 በመቀነስ ፡፡**
- **የቤተሰብ እቅድ ተጠቃሚ ብዛት ከነበረበት 20.5% ወደ 65% በማድረስ ፡፡**
- **የህዝብ እድሜ ቀመር በአምራች እድሜ/15-64/ ያለው በ2002 ካለበት 11,275,706 በ2007ወደ 12,729,208 ከፍ ማድረግ፣**

**የማስፈፀሚያ ስትራተጂዎች**

- **የማስፈፀም አቅምን በመገንባት ተቋማዊ ለውጥ ማምጣት፣**
- **የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም በስነህዝብ ጉዳዮች ዙሪያ ህብረተሰቡ ግንዛቤውን እንዲያዳብር ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣**
- **በስነህዝብ ዙሪያ ወቅታዊ መረጃዎች እንዲሰበሰቡና ጥቅም ላይ እንዲውሉ እንዲሁም ከዚህ ጋር ተዛማጅ በሆኑ ጉዳዮች ጥናትና ምርምር የሚደረግበት የሚያስችል ሥርአት መዘረጋት፣**
- **ከባለድርሻዎችና አጋር አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን ለማጠናከር የሚያግዙ አሰራሮችን መፍጠር**
- **በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃዎች የቤተሰብ ኑሮ ዘዴ ትምህርት**/population Family Life Education/ **ተጠናክሮ እንዲሰጥ ማድረግ**
- **በሥነህዝብ ጉዳይ ላይ የሚሰሩ አካላትን አቅም መገንባት የሚያስችል አሰራር መዘርጋት፣**

## *7.3. ወጣቶችና ስፖርት*

### ወጣቶች

**የትኩረት አቅጣጫ**

**የትኩረት አቅጣጫዎቹ ወጣቶች በዲሞክራሲያዊ ስርዓትና መልካም አስተዳደር ግንባታ እንዲሁም በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በተደራጀ አኳኋን የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉና ከውጤቱም በተገቢው መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማብቃት፣ የወጣቶችንና የወጣት አደረጃጀቶችን አቅም መገንባት፣ የማስተባበር የአጋርነትና የሜንስትሪሚንግ ተግባርን ማከናወን፣ የወጣቶች ንቅናቄና ተሳትፎን ማጎልበትና የወጣት ተኮር ጥናቶች፣ መረጃዎችና የኮሚዩኒኬሽን ስራዎች ላይ ትኩረት መስጠት ናቸው፡፡**

**ዓላማዎች**

**የማስተባበር፣ የአጋርነትና የሜንስትሪሚንግ ስራዎችን በማጠናከር የወጣቶች ጉዳይ በሁሉም ተቋማት ተካተው እንዲሰሩ በማድረግ የወጣቶችን ተሳትፎ ማረጋገጥ፣ እንዲሁም የወጣቶችን ሁለንተናዊ ብቃት በማሳደግ በክልሉ የልማት፣ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴ ውስጥ ግምባር ቀደም ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ናቸው፡፡**

**ግቦች**

- ሁለንተናዊ የወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ
  - ✓ በ2002 በክልሉ የሚገኙትን 217 የወጣት ተኮር ተቋማትን/ማዕከላትን በ2007 መጨረሻ ወደ 1,717 ማሳደግና በቁሳቁስ የተሟሉ ማዕከላትን ብዛት በ2007 መጨረሻ ወደ 1,031 ማዕከላት በቁሳቁስ ድጋፍ የተሟሉ እንዲሆኑ በማድረግ ለወጣቶች የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ በማስቻልና የወጣቶችን ክህሎት በማሳደግ ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭነታቸውን መቀነስ
  - ✓ ተደራጅቶ የመንቀሳቀስ ጥቅምን በወጣቱ ዘንድ በማስረጽ ወጣቶች በራሳቸው ነጻ ፍላጎት በመመስረት እንዲደራጁ በማድረግ በ2002 የነበሩ 1,396,646 የተደራጀ የወጣት ቁጥር በ2007ወደ 3,689,352 ከፍ ማድረግ
  - ✓ በ2002 በ9 አጋር አካላት ስትራቴጅዎች ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ውስጥ ተካተው የሚተገበሩትን ወጣት ተኮር ተግባራት በ2007 በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ በክልልና በየደረጃው ባሉ መ/ቤቶች ኤጀንሲዎችና ድርጅት አጋር አካላት ስትራቴጅዎች፣ ፕሮግራሞችና እቅዶች ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ የወጣቶችን ጥቅም ማስጠበቅ
  - ✓ እስከ 2002 መጨረሻ 12.8 ሚሊየን ብር ያህል ወጣት ተኮር ሃብት ከተለያዩ ምንጮች የተገኘ ሲሆን እስከ በዕቅድ ዘመኑ የተለያዩ የወጣት ተኮር ፕሮጀክቶችን በመስራትና ሌሎች የገቢ አማራጮችን በመጠቀም በ2007 መጨረሻ ገንዘብ የመሰብሰብ አቅምን ብር 253.2 ሚሊዮን ማድረስ
  - ✓ በዕቅድ ዘመኑ ለ1,326,272 ወጣቶች የስራ ፈጣሪነት አመለካከትና አስተሳሰብ ለማምጣት የሚያስችል ስልጠና በመስጠት የየአካባቢያቸውን የሃብት ጸጋ አውቀውና የስራ ክቡርነትን ተገንዝበው ወደ ስራ እንዲሰማሩ ማስቻል
